አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ከ1998-2003 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች ግምገማ


በ

አበበች ገብሩ


ግንቦት 2004 ዓ.ም

**የፈተና ቦርድ አባላት**

የአማካሪ ስም ፊርማ

Getachew Adugna

የፈታኝ ስም ፊርማ

[illegible]

[illegible]

# ምስጋና

ከሁሉም በላይ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው የጥናቱን ረቂቅ እያነበቡ በማረም የማያቋርጥ ድጋፋቸውን ለሰጡኝ አማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው አጁኛ ምስጋናዬ ጥልቅና ልባዊ ነው። እንዲሁም ሁሌም በሐሳብና በሞራል ድጋፍ ያልተለዩኝ መምህሬ አቶ ጌታቸው እንዳላማውን በጣም አመሰግናለሁ።

ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጨረስ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በሀሳብና በሞራል በመደገፍ የበርካታ ሰዎች ውለታ አለብኝ። ከእነዚህም ውስጥ ፈተናዎቹን እንዳገኝ በግላቸው ቀና ጥረት ያደረጉልኝ የአሰላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቤተ መጽሐፍት ሠራተኛ የሆነችው ወ/ሮ ፋንታዬ እና መ/ር ምሬሣ፣ ቃለ መጠይቁን የመለሱልኝ የክልሉ ፈተና ክፍል ተወካይ፣ ጥቂቶቹ ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በማሰባሰብ ያበረከቱልኝ አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ በጣም ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

በሀሳብና በሞራል እየደገፉ እስከ ጥናቱ መጨረሻ ድረስ ከጎኔ ያልተለዩት ጓደኞቼ እንዲሁም የእኔን ስኬት ለማየት ዘወትር የሚናፍቁት ቤተሰቦቼና ባለቤቴ የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

የትምህርት ወጪዬን በመሸፈን ይህን ትምህርት እንድማር እድሉን ላመቻቸልኝ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ በትዕግስት ለፃፉልኝ ጓደኞዬ ሐረገወይን ታደሰ እና አርማዬን አደራ ከልቤ አመሰግናለሁ።

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምስጋና ........ I
ማውጫ ........ II-IV
የሠንጠረዥ ማውጫ ........ V
አጠቃሎ ........ VI
**ምዕራፍ አንድ**
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ ዓላማ ........ 3
1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 3
1.4.የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.5. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ........ 4
1.6. የቁልፍ ቃላት ፍቺ ........ 5
1.7. በጥናት ውስጥ የዓመተ ምህረት አጠቃቀም ........ 6
**ምዕራፍ ሁለት**
የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........ 7
2.1 የቋንቋ ፈተና ምንነት ........ 7
2.2 የቋንቋ ፈተና ዓላማ ........ 8
2.3. ቋንቋን ማስተማርና መፈተን ያላቸው ዝምድና ........ 8
2.4. የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች ........ 10
2.4.1.የብቃት መለኪያ ፈተና ........ 11

2.4.1. የድክመትና ጥንካሬ መለኪያ ፈተና ....................................................11

2.4.2. የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ....................................................12

2.4.3. የችሎታ መለኪያ ፈተና ....................................................12

2.4.4.1 የችሎታ መኪያ ፈተናዎችና የመርሃ ትምህርት ዝምድና ....................14

2.4.4.2 ናሙና ....................................................15

2.4.4.3. የችሎታ መለኪያ ፈተና ጥያቄዎች አዘገጃጀት....................................16

2.5. የጥሩ ፈተና መስፈርቶች ....................................................17

2.5.1. ተገቢነት ....................................................17

2.5.1.1 የይዘት ተገቢነት ....................................................18

2.5.1.2. የላህያዊ ተገቢነት ....................................................20

2.5.2 ህያውነት ....................................................20

2.5.3 ተተግባሪነት ....................................................21

2.6..የፈተና አዘገጃጀት ዝርዝር መርሆች....................................................22

2.7.ሰዋስውን ማስተማርና መፈተን ....................................................23

2.7.1..ሰዋስውን ማስተማር ....................................................24

2.7.2. ሰዋስውን መፈተን ....................................................25

2.7.3. የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ ....................................................26

2.8. የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን የገመገሙ ቀደምት ጥናቶች....................................28

ምዕራፍ ሦስት

የአጠናን ዘዴ ....................................................31

3.1. የጥናቱ ዘዴ....................................................31

3.2. የመረጃ ምንጮች ....................................................31

3.2.1.ፈተናዎች........................................................................32
3.2.2.መርሃ ትምህርት ..................................................................32
3.2.3.በክልሉ የፈተና ዝግጅት ክፍል ተወካይ.......................................32
3.3. የናሙና አመራረጥ.......................................................................32
3.3.1.የፈተናዎች አመራረጥ...........................................................32
3.3.2. የክልልና የክፍል ደረጃ አመራረጥ..........................................33
3.4.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ................................................33
3.4.1. የሰነድ ፍተሻ ....................................................................34
3.4.2. ቃለ-መጠይቅ.....................................................................34
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ...............................................................35
ምዕራፍ አራት
የመረጃ አቀራረብ፣ አተናተንና አተረጓጎም ..........................................36
4.1 የፈተናው ተገቢነት .....................................................................36
4.2. የጥያቄዎች አዘገጃጀት...............................................................53
4.2.1 ባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች አዘገጃጀት...................................53
4.2.2 አጠቃላይ መርሆች ...................................................................60
ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያ እና አስተያየት.................................................................64
5.1. ማጠቃለያ.................................................................................64
5.2. አስተያየት ................................................................................65
ዋቢ ጽሑፎች .....................................................................................67
አባሪዎች
አባሪ አንድ .........................................................................................72
አባሪ ሁለት ........................................................................................94
አባሪ ሦስት .........................................................................................95

## የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ አንድ፡- ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ መርሃ ትምህርቶች ውስጥ የተነደፉት የሰዋስው ይዘቶችና የተመደባለቸው ክፍለ ጊዜ ብዛት በመቶኛ፡......................38

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የሰዋስው ይዘቶች በ1998 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና............41

ሠንጠረዥ ሦስት፡- የሰዋስው ይዘቶች በ1999 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና..........43

ሠንጠረዥ አራት፡- የሰዋስው ይዘቶች በ2000 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና..........45

ሠንጠረዥ አምስት፡-የሰዋስው ይዘቶች በ2001 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና.........46

ሠንጠረዥ ስድስት፡- የሰዋስው ይዘቶች በ2002 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና........48

ሠንጠረዥ ሠባት፡- የሰዋስው ይዘቶች በ2003 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና ..........................................................50

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው ሲቀርቡ በነበሩ የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ ሰዋስውን ለመመዘን የቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢ የመመዘኛ መሳሪያ መሆናቸውን መመርመር ነበር። በጥናቱ ከ1998-2003 ዓ.ም የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማጠቃለያ ፈተናዎችን በዋና የመረጃ ምንጭነት በመውሰድ ከፈተና አዘገጃጀት መርሆችና ከጥሩ የፈተና ባህሪያት (የይዘት ተገቢነት) አንፃር ለመመርመር ተሞክሯል። በዚህ የግምገማ ሂደት የማጠቃለያ ፈተናዎች ተገቢ መርሆችን ተከትለው መዘጋጀታቸው፣ ለደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር መዛመዳቸው እንዲሁም በመርሃ ትምህርቱ የተነደፉትን የሰዋስው ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው መወከላቸውን በመመርመር በስድስቱም ዓመት የማጠቃለያ ፈተናዎች የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች 99.4% በመርሃ ትምህርቱ በተነደፉ የሰዋስው ይዘቶች ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ተረጋግጧል። አንዳንድ የሰዋስው ይዘቶች በፈተናው ያለመካተታቸውና የተካተቱትም የሰዋስው ይዘቶች ቢሆኑ እንደየትኩረት ደረጃቸው በበቂ የጥያቄ መጠን ያልተወከሉ መሆናቸው ተረጋግጧል። የፈተና አዘገጃጀት መርሆችን በተመለከተ በአንዳንድ የማጠቃለያ ፈተናዎች አሉታዊ ቃላትንና ሐረጋትን በተገቢው መንገድ ያለመጠቀም እና ሁሉም መልስ ነው የሚሉ አማራጮችን በተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ መጠቀም የሚነሱ ችግሮች ቢሆኑም በአብዛኛው ግን የማጠቃለያ ፈተናዎቹ ተገቢ የአዘገጃጀት መርህን የተከተሉ መሆናቸው ታይቷል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ፈተና በቋንቋ ትምህርት ታሪክ ከረጅም ዘመናት ጀምሮ የመማር ማስተማሩ አካል ሆኖ ሲሰራበት የነበረና አሁንም እየተሰራበት ያለ፣ የአንድን ተማሪ የቋንቋ ዕውቀትና ችሎታ፣ ድክመትናጥንካሬ፣ፍላጎትና የእለተ ተዕለት መሻሻል ወዘተ በመለካት ውሳኔዎች ለማሳለፍና ቀጣይ ተግበራትን ለማከናወን የሚያስችሉ መረጃዎችን የሚሰጥ መሳሪያ ነው (Ur፣ 1996 እና Hughes፣1989)::

ቋንቋን ማስተማርና ቋንቋን መፈተን ግንኙነታቸው የጠበቀና እርስ በርስ የሚደጋገፉ ተግባራት ናቸው(Heaton፣1975)። የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ ማድረግ ሲሆን ይህ የሚረጋገጠው ደግሞ በቋንቋ ፈተናዎች ነው፡፡ በመሆኑም ማስተማሩና መፈተኑ የትምህርቱ አካል ሆነው ሳይነጣጠሉ ይከናወናሉ (Brown ፣ 1980)::

የቋንቋ ፈተናዎች አላማ እንደ ፈተናዎቹ አይነትና ይዘት የተለያየ ነው፡፡እንደ Bachman (1990)፣ Heaton (1990) እና Weir (1993) ገለፃ እጅግ በርካታ የፈተና ዓይነቶች ከመኖራቸው አንፃር ዓላማቸውም እንደ ቁጥራቸው ብዙ ነው በማለት ዋና ዋና ያሏቸውን ብቻ ይጠቅሳሉ፡፡ የቋንቋ ፈተናዎች አላማ የተማሪዎችን አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ በመለካት ለእነሱ የሚመጥነውን ቀጣይ የጥናት መስክ ማመልከት፣ ተማሪዎች ለተወሰኑ ጊዜያት የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደጨበጡ ማረጋገጥ፣ የተማሪዎችን ድክመትና ጥንካሬ ማሳየት፣ በቋንቋ ትምህርት ፕሮግራሙ ላይ ማሻሻያና ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መረጃ መስጠት፣ የትምህርቱ አላማዎች በተማሪዎች ዘንድ ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆኑ ማመልከት ወዘተ. ናቸው፡፡

እነዚህ ፈተናዎች የታለመላቸውን አላማ ከግብ ያደርሱ ዘንድ ደግሞ በወጉ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ በወጉ የተዘጋጀ ፈተና ለመማር ማስተማሩ ሂደት ጠቀሜታው የላቀ ሲሆን ይህ ካልሆነ ግን ከፈተናዎቹ የሚገኘው መረጃ የተዛባ ስለሚሆን ጎጂ ተጽዕኖ ይኖረዋል (Madsen፣1983)፡፡ Saxም(1974) ይህንን ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ ፈተና የመማር

ማስተማሩ አካል ሆኖ የትምህርቱ አላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ እገዛ ማድረግ የሚችለው ስልታዊ በሆነ መንገድ ሲከናወን ነው። ስልታዊ ሲባልም የፈተናው ዝግጅት፣ አፈታተኑንና የእርማት ሂደቱን ሳይንሳዊ በሆነ ህግና ደንብ የሚገዛ መሆኑን ያመለክታል በማለት ይገልጻሉ።

ከላይ የቀረቡት ሀሳቦች እንደሚያስረዱት በየጊዜው የሚሰጡ ፈተናዎች የታለመላቸውን ግብ እንዲመቱ ብቃታቸው በየጊዜው ሊረጋገጥ ይገባል። ከትምህርቱ ጋር ያላቸው ዝምድና፣ ተገቢ የአዘገጃጀት መርህን ተከትለው መዘጋጀታቸው፣ በጥቅሉ አንድ ፈተና ማሟላት የሚገባውን የጥሩ ፈተና ባህርያት ማሟላቱ ወዘተ እየተመረመረ ድክመትና ጥንካሬያቸው እየተለየ መሻሻል የሚገባው አሰራር መሻሻል ይገባዋል።

ይህ ጥናትም በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ከ1998 - 2003 ዓ.ም አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅተው በቀረቡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎችን ከይዘት ተገቢነትና ከፈተና ዝግጅት መርሆች አንጻር ይመረምራል።

እስካሁን በአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ላይ የተሰሩ በርከት ያሉ ጥናታዊ ፅሁፎች ይገኛሉ። እነዚህ ጥናታዊ ፅሑፎች በአብዛኛው የሚያተኩሩት በቃላት አፈታተንና በፈተናዎቹ ውስጥ በቀረቡት ጥያቄዎች አጠቃላይ ይዘትና አቀራረብ ግምገማ ላይ ነው። ከእነዚህም ውስጥ አበበ (1975 ዓ.ም)፣ ተስፋዬ (2000 ዓ.ም)፣ በለጠ (1995 ዓ.ም)፣ ትንሳኤ (1988 ዓ.ም) ፣ ራሔል (2001 ዓ.ም) እና ኤደን (2002 ዓ.ም) ጥቂቶቹ ናቸው።

ይህ ጥናት ከላይ ከተጠቀሱት በተለየ ሁኔታ ትኩረት የሚያደርገው በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ከ1998 ዓ.ም- 2003 ዓ.ም አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲዘጋጁ የነበሩትን የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ሰዋስውን መሰረት ባደረጉ ጥያቄዎች ላይ ነው።

ይህንን ጥናት ለማጥናት ያነሳሳት ነገር እስካሁን በዘርፉ በተሰሩ ጥናቶች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች ላይ ጥናት ባለመደረጉና በክልል ደረጃም ቢሆን የተዘጋጁ ፈተናዎችን ያጠና ባለሙያ አለመኖሩ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት አድርጓል።

1. የሰዋስው ጥያቄዎቹ መርሃ ትምህርቱን መስረት አድርገው ተዘጋጅተዋል?
2. ጥያቄዎቹ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ያሉ ይዘቶችን እንደየትኩረት ደረጃቸው የወከሉ ናቸው ወይስ አይደሉም?
3. ጥያቄዎቹ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የሚዘጋጁበትን መርህ ተከትለው የተዘጋጁ ናቸው?

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች ከ1998 - 2003 ዓ.ም በተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎችን አቀራረብ መመርመር ነው፡፡ ይህንን አጠቃላይ ዓላማ መሰረት በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

1. ከ1998 - 2003 ዓ.ም በተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ጥያቄዎች መርሀ ትምህርቱን መሠረት አድርገው መዘጋጀታቸውን መመርመር፣
2. የሰዋስው ጥያቄዎቹ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ያሉ ይዘቶችን እንደየትኩረት ደረጃቸው መወከል አለመወከላቸውን መገምገም፣
3. ጥያቄዎቹ ተገቢ የችሎታ መለኪያ ፈተና የአዘገጃጀት መርህን ተከትለው መዘጋጀት አለመዘጋጀታቸውን መመርመር፣

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

በየጊዜው የሚዘጋጁ ፈተናዎች አቀራረብ መንገድ መፈተሽ የማስተማሪያ መሣሪያዎችንና ዘዴዎችን ከማሻሻሉም በላይ ፈተናዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ አዎንታዊ እንዲሆን ያግዛል፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ጥናትም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፤

1. ፈተናዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ድጋፍ ሰጪ ይሆኑ ዘንድ ፈተና የሚያዘጋጁ ባለሞያዎች ጥያቄዎችን በጥንቃቄ እንዲያዘጋጁ አቅጣጫ ያሳያል፤
2. የሚመለከታቸው አካላት የማጠቃለያ ፈተናዎቹን ጠንካራና ደካማ ጎን ተገንዝበው ቀጣይ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ያግዛል፤

3. በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች በፈተናዎች ውስጥ ተመጣጣኝ ውክልና እንዲያገኙ ጥቆማ ይሰጣል፤
4. ወደፊት በዚህ ርዕስ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደ መነሻ በመሆን ያገለግላል።

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ዋና ትኩረት በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የሚዘጋጁ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የሰዋስው ጥያቄዎች ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን የይዘት ተገቢነት መመርመር ነው።በመሆኑም ጥናቱ የሚያተኩረው ከ1998 - 2003 ዓ.ም በተዘጋጁ ፈተናዎች ላይ ሲሆን በሰዋስው ጥያቄዎች ላይ ብቻ የተገደበ ነው። በመሆኑም ሌሎች የቋንቋ ይዘቶችን መሠረት አድርገው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን አይመለከትም።

## 1.5. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ ፈተናዎች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የክልሉ ፈተና ክፍል አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ይተባበራል የሚል ተስፋ ነበር። ይሁን እንጂ ለጥናቱ አስፈላጊ ከሆኑ መረጃዎች ውስጥ የእያንዳንዱን ዓመተ ምህረት ፈተናዎችና የመልስ ቁልፍ (Answer key) ማግኘት እና የፈተና ክፍሉ ባለው ሚስጥራዊ አሰራር ምክንያት ባለሙያዎቹን በአካል አግኝቶ ቃለመጠይቅ ማቅረብ አለመቻል ጉልህ ችግሮች ነበሩ።

እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ አጥኚዋ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን ፈተናዎች ከትምህርት ቤቶች በማፈላለግ ያሰባሰበች ሲሆን የመልስ ቁልፉን ደግሞ ከዞን ትምህርት ቢሮ ማግኘት ችላለች።

በሌላ በኩል በዚህ ጥናት ለፈተና አዘጋጆች ቃለመጠይቅ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም የፈተና ክፍሉ ባለው ሚስጥራዊ አሰራር ምክንያት ባለሙያዎቹን በአካል አግኝቶ ቃለመጠይቅ ማድረግ አልተቻለም፤ አጥኚዋ ይህንን ችግር ለማቃለል በክልሉ ለፈተና ክፍል ተወካይ ቃለመጠይቅ ያቀረበች ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ችግሩን በተወሰነ መልኩ ለማስወገድ በክልሉ የሚዘጋጀው የፈተና አዘገጃጀት መመሪያ በማየትና ከሰነድ ፍተሻ የተገኙትን መረጃዎች በማመሳከሪያነት በማቅረብ እውነታውን ለማሳየት ጥረት አድርጋለች።

## 1.6. የቁልፍ ቃላት ፍቺ

**ህያውነት** (Reliability)

አንድ ፈተና ወይም ሁለት ተመጣጣኝ ፈተናዎች ለተመሳሳይ ተማሪዎች ከአንድ ጊዜ በላይ ተሰጥተው የሚገኘውን የውጤት ወጥነት የሚያመለክት ነው (Hughes፣1989) ::

**የላህያዊ ተገቢነት** (face validity)

የአንድን ፈተና የላይላይ ተአማኒነት ወይም ተቀባይነት የሚመለከት ነው (Alderson: and et al፣ 1995)::

**ባክዋሽ** (Backwash)

ፈተናዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚኖራቸው ተፈላጊ (አዎንታዊ) ወይም ጎጂ (አሉታዊ) ተፅዕኖ ባክዋሽ ይባላል (Hughes፣ 1995)::

**ተተግባሪነት** (Practicality)

አንድ ፈተና ከጊዜ፣ ከገንዘብ እንዲሁም ከአስተዳደራዊ ሁኔታዎች አኳያ ያለችግር በተግባር ላይ መዋሉን ነው (Hughes፣ 1989)::

**ተገቢነት** (validity)

አንድ ፈተና እንዲመዝን የታሰበውን ጉዳይ በትክክል የለካ ከሆነ ተገቢነት አለው ይባላል (Heaton፣ 1988)::

**የችሎታ መለኪያ ፈተና** (Achievement Test):-

በአንድ የቋንቋ ትምህርት ዓላማና ይዘት ላይ በመመስረት ተማሪዎች የቀረበላቸውን የቋንቋ ትምህርት ምን ያህል ተገንዝበውታል የሚለውን ለመመዘን የሚዘጋጅ ፈተና ነው (Hughes፣ 1989)::

**አሳሳቾች (distractors)**

በባለ ብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ውስጥ ከዋናው መልስ ጋር በአማራጭነት የሚቀርቡ መልሶችን ይመለከታል:: ተአማኒ አሳሳቾች ሲባልም በአማራጭነት የቀረቡ መልሶች የመምሰል ባህሪያቸውን ይመለከታል::

**የይዘት ተገቢነት (Content Validity)**

አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው ሊባል የሚችለው የፈተናው ይዘት መያዝ የሚገባውን የትምህርቱን ይዘት ተመጣጣኝ (ወካይ) በሆነ ናሙና ያቀረበ ሆኖ ሲገኝ ነው (Heaton፣ 1975)።

## 1.7. በጥናቱ የዓመተ ምህረት አጠቃቀም

በዚህ ጥናት በኢትዮጵያ እና በውጪው የዘመን አቆጣጠር የተፃፉ ጽሑፎች በጥቅም ላይ ውለዋል። ከነዚህ ውስጥ በኢትዮጵያ አቆጣጠር የተገለጹት በሙሉ ዓመተምህረቱን ከሚያመለክቱ ቁጥሮች ቀጥሎ ዓ.ም የሚል እንዲታከልባቸው ተደርጓል። ስለዚህ ዓ.ም የሚል ያልተጨመረባቸው ሁሉ የውጭውን አቆጣጠር  የሚመለክቱ ዓመተምህረቶች ናቸው።

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

### 2.1 የቋንቋ ፈተና ምንነት

በርካታ ምሁራን የቋንቋ ፈተናን ምንነት በተለያየ መንገድ ሲበይኑት የሚታይ ቢሆንም በብያኔያቸው የሚያነሷቸው ነጥቦች ተመሳሳይነት አላቸው። እንደነዚህ ምሁራን ገለጻ ፈተና ያንድን ግለሰብ ዕውቀት፣ ችሎታ፣ ባህሪይ፣ ወይም አንድ ሰው በአንድ ነገር ላይ ያለውን አመለካከት የምንለካበት መሳሪያ ነው(Baker፣1989፤ Oller፣1979)።

ከላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ የሚያጠናክር Bacheman (1990) Carrollን በመጥቀስ ሲያስረዱ ፈተና የአንድን ግለሰብ ባህሪይ ለመመዘን የሚጠቅም መሣሪያ ነው። ሲሉ እንደዚሁም Brown(1981) Brown(1976)ን ጠቅሰው ከላይ የጠቀስነውን ሀሳብ በሚደግፍ መልኩ እንደሚከተለው ብሏል። ፈተና ስለአንድ ተማሪ ማወቅ ያለብንን መረጃ የምንሰበስብበት ዘዴ ነው ።

ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ የምንረዳው የቋንቋ ፈተና የተፈታኞችን አጠቃላይ መረጃ የምንሰበስብበት መሳሪያ ነው።ይህም ማለት የተፈታኞቹን ፍላጎት፣ዕውቀት፣የባህሪይ ለውጥ፣ድክመትና ጥንካሬ፣ወዘተ ያሉትን መረጃዎች ለመሰብሰብ የሚያግዝ መሳሪያ ነው።

በተጨማሪም Baker (1989) ስለፈተና ሲገልፁ ፈተና ትርጉም ያለው ውሳኔ ላይ እንድንደርስ ያግዛል። Brown (1983) ም የBakerን ሀሳብ በመደገፍ ፈተና የተማሪውን ውጤት በመመልከት አንድ ውሳኔ ላይ እንድንደርስ ያግዘናል። እንደነዚህ ሰዎች ሀሳብ ፈተና በአንድ ነገር ላይ ትክክለኛ ውሳኔ ለማሳለፍ ድጋፍ ይሰጣል ማለት ነው።

በአጠቃላይ የቋንቋ ፈተና ስንል ለአንድ ቋንቋ ትምህርት አብይ መመዘኛ መስፈርት ሆኖልን በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ተማሪዎች ምን ያህል የትምህርቱን አላማ እንደጨበጡ የምናረጋግጥበት መሳርያ ነው። ብዙ ጊዜም ይህ የመመዘኛ መሳርያ አሀዛዊ መረጃዎችን የሚሰጥ ሲሆን ተፈታኞቹ በቋንቋ ክሂል (በማዳመጥ፣ በንግግር፣ በንባብና በጽህፈት) ወይም በቋንቋ እውቀቶች(በስነ ጽሁፍና በስነ ልሳን) አኳያ ያሉበትን ደረጃ ለፈታኙ የሚያመለክትና በትምህርቱ ሂደት ውስጥም እጅግ አስፈላጊ የሆነ መሳሪያ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን በአንድ ውስን የቋንቋ

ክሂል ወይም የዕውቀት ዘርፍ ዙሪያ የተፈታኞችን ዕውቀትና ችሎታ ለመለካት እንጠቀምበታለን(Ur፣1996፤ Bachman፣ 1990 እና Brown፣1980)።

## 2.2. የቋንቋ ፈተና ዓላማ

በቋንቋ ትምህርት ፈተናዎች በተማሪዎች የታየውን የችሎታ እድገት ለማወቅ፣ለመማር፣ አስቸጋሪ የሆኑ ነጥቦችን ለመለየት፣ ተማሪዎችን ለማበረታታት፣ የችሎታ ደረጃቸውን ለመለየት በተገቢ ቦታቸው ለመደልደል፣ ለመምረጥ፣ ስለችሎታቸው ለማወቅ፣ ዓላማ እንደሚሰጡ Heaton (1990) ይገልፃሉ። ይህም ማለት የቋንቋ ፈተና የሚሰጥበት አላማ የተማሪዎችን አጠቃላይ የሆነ መረጃ ለማግኘት ነው።

Bachman (1995)ም እንደዚሁ በአንድ የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ፈተናዎች የሚሰጡበት ዓላማ የተለያዩ ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ነው በማለት ይገልፃሉ። ይህም የሚያመለክተው ፈተና በተማሪዎች ላይ የተለያዩ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ እና በቋንቋ ትምህርቱ ላይ አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ያግዛል።

በተጨማሪም Ur (1996) የቋንቋ ፈተና ተቀዳሚ ዓላማው ተፈታኙ አንድን ነገር ምን ያህል እንደሚያውቀው ወይም ተግባራዊ እንዳደረገው ለመረዳት የሚያገለግል ክንውን ነው በማለት ገልጸውታል። ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው የቋንቋ ፈተና ስለተፈታኙ እውቀትና በባህሪው ላይ ያመጣውን ለውጥ የምንገመግምበት ዘዴ ነው።

## 2.3. ቋንቋን ማስተማርና መፈተን ያላቸው ዝምድና

ፈተና የተማሪዎችን የቋንቋ ብቃትና ዕውቀት ለማወቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥም ወሳኝ ነው፤ በመሆኑም የቋንቋ ፈተና ዝግጅት ከመማር ማስተማር ጋር ግንኙነት ሊኖረው ይገባል።

Heaton(1975) በፈተና እና ቋንቋን በማስተማር መካከል ያለውን ከፍተኛ ግንኙነት ሲገልጹ ማስተማር እና መፈተን በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። በመሆኑም አንዱን ከአንዱ ነጥሎ መመልከት ፈጽሞ የሚቻል አይደለም። ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ቋንቋን ማስተማርና ቋንቋን መፈተን በእጅጉ የተቆራኙ በመሆኑ አንዱን ከሌላው ነጥሎ ማየት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ነው።

እንደ Davies (1968) ገለጻ ጥሩ ፈተና የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚከተል በመሆኑ እንደ ታማኝ ታዛዥ ይቆጠራል፡፡ እንዲሁም Stevenson (1977) ይህንን ሀሳብ ሲያጠናክሩ የቋንቋ ፈተና ለመማር ማስተመሩ ዘዴ እንደ ድጋፍ ሰጪ መታየት አለበት በማለት የሁለቱን ግንኙነት ያጠናክራሉ፡፡

በርካታ ምሁራን በተለይም Weir (1990)፣ Hughes (1988) እና Bachman (1995) መፈተንና ማስተማር የተሳሰሩ መሆናቸው ላይ ተቃውሞ ባይኖራቸውም በDavies (1968) በተገለጸው አይነት ግንኙነታቸው የሚስማሙ አይደሉም፡፡ እንደነሱ ትንታኔ ፈተና ከታዛዥነት፣ ከማስተማር ተከታይነት በላይ ሚና ያለው ነው፡፡ የተወሰኑትን ለአብነት ብናይ Hughes(1995) ስለሁለቱ ተዛምዶ ሁለቱ ትክክለኛ አቻነት አይነት ግንኙነት ያላቸው እንደሆኑ አድርገው ነው የሚያዩት፡፡ እንደሳቸው አባባል ፈተና ሁልጊዜ ማስተማርን የሚከተል አድርገን ማሰብ የለብንም፡፡ ለጥሩ ማስተማር ድጋፍ ሰጪ ሆኖ እንዲያገለግል መጣር አለብን፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በመጥፎ ማስተማር ሂደት ላይ በጎ ተጽዕኖ አድርጎ የማስተማር ሂደቱ የሚሻሻልበትን ስልት የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡ በማለት ቋንቋን ማስተማርና ቋንቋ መፈተን በእጅጉ የተዛመዱ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት ምሁራን ገለጻ መረዳት የሚቻለው የቋንቋ ትምህርትና ፈተና የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡ ይህ ማለት ያለቋንቋ ፈተና ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርቱን ዓላማ በትክክል ከግብ ማድረሳቸውን ማረጋገጥ አዳጋች ነው፡፡ ቋንቋን ማስተማርና ቋንቋን መፈተን በእጅጉ የተቆራኙ መሆናቸውን ተገንዝበን ለሁለቱም መስኮች ትኩረት መስጠት የዘወትር ተግባራችን መሆን አለበት (Heaton 1975)

ሌላው ቋንቋን ማስተማርና ቋንቋን መፈተን ያላቸውን ዝምድና የሚያስረዳ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ውስጥ የታዩ ልዩ ልዩ  ዘዴዎች በመርሃ ትምህርቶችና በማስተማሪያ መፃህፍት አዘገጃጀት በተጨማሪ  በቋንቋ አፈታተን ዘዴዎችም ላይ ተፅዕኖ አሳድረዋል የሚለው ሀሳብ ነው፡፡

እንደ Brown (1980) ገለጻ የቋንቋ ፈተና ታሪካዊ ዳራን በሦስት ደረጃዎች የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው የቋንቋ ፈተና ዳራ ሌሎች የማህበራዊ ሳይንስ መስኮች ይገዙበት የነበረው እና ከ1950ዎቹ በፊት ያለውን ጊዜ የሚሸፍነው የቅድመ ሳይንስ መስኮች ዘመን ነው ሁለተኛው የቋንቋ ፈተና ታሪካዊ ዳራ ደግሞ ከ1950ዎቹ - 1960ዎቹ ያለውንና የቋንቋ ቅንጣቶችን

ነጣጥሎ የሚፈትነውን የመዋቅራዊያንን ዘመን ይይዛል፡፡ ሶስተኛው የቋንቋ ፈተና ዳራ ተግባቦታዊ የቋንቋ ፈተናዎች የሚሰጡበትና ክሂሎችን አቀናጅቶ በፈተና ማካተትን የሚመለከተው ዘመን ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ የቋንቋ ፈተና ለውጦች በቋንቋ ማስተማር ላይም ይታዩ የነበሩ በመሆናቸው በቋንቋ ማስተማር ላይ የታየ ተጽዕኖ ወደ ቋንቋ መፈተን የሚሄድ በመሆኑ ሁለቱም ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን ያስረዳናል፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋ ፈተና ቋንቋን በማስተማር ረገድ በየዘመኑ ከተነሱት ንድፈ ሀሳቦች ጋር ተያያዥነት አለው፡፡ ልክ እንደ ቋንቋ ማስተማር ሁሉ ቋንቋ መፈተን ታሪካዊ ሂደት ስናይ በየዘመኑ ፈተናዎች የተለያየ አቅጣጫና መንገድ እንደነበራቸው መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.4. የቋንቋ ፈተና ዓይነቶች

የቋንቋ ፈተናዎች ከሚሰጡት መረጃና ከሚዘጋጁበት ዓላማ የተነሳ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የተለያዩ የቋንቋ ፈተና ምሁራን የቋንቋ ፈተና ዓይነቶችን በተለያዩ መልኮችና አይነቶች ቢገልጹም በአራት ይከፍሏቸዋል፡፡ ለአብነት ብንመለከት Harison(1989)፣ Hughes(1989)፣ Brown(1980)፣ ተስፋዬ(1981) እና Heaton(1975) የቋንቋ ፈተና አይነቶችን የብቃት መለኪያ ፈተና (proficiency test) ፣ የድክመትና ጥንካሬ መለኪያ ፈተና (diagnosis test )፣ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (placement test) እና የችሎታ መለኪያ ፈተና (achievement test ) በማለት በአራት ይከፍሏቸዋል፡፡

Hughes (1989) እንደሚሉት ደግሞ በታሪክ ሂደት በርካታ የቋንቋ ፈተና ዓይነቶችና ስልቶች የተፈጠሩ ቢሆንም ጥሩ ወይም መጥፎ የሚባል ፈተና የለም፡፡ ስለዚህ ከትምህርቱ ዓላማ እና መመዘን ከተፈለገው ችሎታ አንጻር ተስማሚ ጎኑን መርጦ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ምንም እንኳን የዚህ ጥናት ትኩረት የማጠቃለያ ፈተናዎች ላይ ቢሆንም የሌሎቹን የፈተና አይነቶች ምንነት መዳሰሱ ይህንኑ የፈተና አይነት ይበልጥ ለመገንዘብ ስለሚረዳ ቀጥሎ ከላይ የተጠቀሱትን የፈተና አይነቶች በአጭሩ ለመቃኘት ይሞከራል፡፡

### 2.4.1. የብቃት መለኪያ ፈተና (proficiency test)

የብቃት መለከኪያ ፈተና አንድ ተማሪ ምንም ስልጠና ወይም ትምህርት ከመውሰዱ በፊት በአንድ ቋንቋ ላይ ያለውን አጠቃላይ የሆነ ብቃት የምንመዝንበት ሲሆን የፈተናው ይዘት በትምህርቱ ዓላማ ወይም ይዘት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ከዚህ ቀደም ባካበታቸው የቋንቋ ችሎታዎች ላይ ነው (Hughes፣ 1989 እና Alderson and etal፣ 1995)፡፡

ይህም ማለት ብቃትን የመለኪያ ፈተና በአጠቃላይ በየትኛውም ትምህርት አላማና ይዘት ላይ አይመሰረትም ማለት እንችላለን፡፡ የዚህ ፈተና ዋና አላማ ተማሪው ከዚህ ቀደም ያውቀዋል ወይም ይረዳዋል ተብሎ የሚገመት የቋንቋ ችሎታውን መገምገም ነው፡፡

ተስፋዬ (1981) የብቃት መለኪያ ፈተናን አስመልክተው ደረጃን ለመለካት የሚዘጋጅ ፈተና ከተለያዩ የትምህርት ተቋሞች ተወጣጥተው በአንድ ክፍል ወይም በአንድ ተቋም ውስጥ ለመማር የሚመጡ ተማሪዎች ያላቸውን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ የሚዘጋጅ ፈተና መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ይህ የፈተና አይነት አጠቃላይ የሆነ የቋንቋ እውቀትን ለመመዘን የሚዘጋጅ ፈተና ነው፡፡ በመሆኑም ፈተናው የተወሰነ መርሀ ግብርን መሰረት አድርጎ አይዘጋጅም፡፡ ይህም ማለት ምንም አይነት ስልጠና ወይም ትምህርት ከመውሰዳቸው በፊት የተማሪውን ብቃት ወይም ችሎታ ለመለካት የሚዘጋጅ ነው፡፡

### 2.4.2. የድክመትና ጥንካሬ መለኪያ ፈተና (Diagnostic test)

የዚህ ፈተና የቅድሚያ ትኩረት የተማሪውን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ተጨማሪ ትምህርት የሚያስፈልግበትን የቋንቋ ክሂልና ክፍል ማሰስ እንደሆነ ምሁራን ይገልጻሉ (Heaton፣ 1975 እና Hughes፣ 1989)፡፡

Harrison (1989) ደግሞ የድክመትና ጥንካሬ መለኪያ ፈተናዎች እንደ ተጨማሪ መሳሪያ ስለሚያገለግሉ ለተማሪዎች ቢሰጡ መልካም ከመሆኑ በተጨማሪ የተማሪዎቹን ድክመትና ጥንካሬ ስለሚለይ በቀጣይ የመማር ማስተማሩ ሂደት በምን መልኩ መቀጠል እንዳለበት ጥቆማ ይሰጣል፡፡

የድክመትና ጥንካሬ መለኪያ ፈተና ዓላማ ተማሪዎች በየትኛው የቋንቋ ክህሎት ላይ ድክመት እንደሚያሳዩ መመርመር ነው። በተገኘውም መረጃ መሰረት ቀጣይ የመፍትሄ እርምጃዎችን ለመውሰድ መንገድ ይከፍታል (Brown ፣1980 እና Alderson and etla፣ 1995)።

ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው የድክመትና ጥንካሬ መለኪያ ፈተና ዋና አላማ ተማሪዎችን ከክፍል ክፍል ማሳለፍ ወይም ክፍል እንዲደግሙ ማድረግ አይደለም፤ ይልቁንም ተማሪዎች በየትኛው የቋንቋ ክሂል ላይ ድክመት እንደሚያሳዩ ለማወቅ የሚሰጥ የፈተና አይነት ነው።

### 2.4.3. የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (Placement Test)

ቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች ገና ያልጀመሩትን የቋንቋ ትምህርት ወደፊት ትምህርቱን ቢማሩ ውጤታማ መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ የሚዘጋጅ ፈተና ነው። ይህ የፈተና ዓይነት ተማሪው ወደፊት በዚያ ቋንቋ ትምህርቱን መቀጠል አለመቀጠሉን ውሳኔ የሚያሰጥ የፈተና አይነት ነው (Harrison፣ 1989)።

ተስፋዬ (1981) የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተናን ሲገልጹ ለአንድ የቋንቋ ትምህርት የሚቀርብ ተማሪ ቋንቋ ለመማር ወይም ለትምህርቱ የተዘጋጀውን ፕሮግራም ለመከታተል ያለውን ችሎታ ለመለካት የሚሰጥ ፈተና ነው በማለት ገልፀውታል።

ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ መረዳት የሚቻለው የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና አንድ ተማሪ የቋንቋ ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት ያለውን የቋንቋ የእውቀት ደረጃ ለመለካት የሚቀርብ ፈተና ነው።

### 2.4.4. የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement test)

በርካታ ምሁራን የችሎታ መለኪያ ፈተናን በተመሳሳይ መልኩ በይነውታል። ከነዚህም ውስጥ Hughes (1989) የችሎታ መለኪያ ፈተና በአንድ የቋንቋ ትምህርት ዓላማና ይዘት ላይ በመመስረት ተማሪዎች የቀረበላቸውን የቋንቋ ትምህርት ምን ያህል ተገንዝበውታል የሚለውን ለመገምገም የሚዘጋጅ ፈተና መሆኑን ይገልጻሉ። Heatonም(1975) እንደዚሁ ብዙዎቹ በየዓመቱ የሚሰጡ የትምህርት ቤት ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ ፈተና ቅርፅ እንደሚኖራቸው ገልጸው ማንኛውም የተወሰነ ትምህርት መረሃ ግብር መጠናቀቁን ለማወቅ በብሔራዊ ደረጃ የሚሰጡ ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ናቸው ይላሉ። በተጨማሪም Alderson and

etal (1995) የችሎታ መለኪያ ፈተና ለትምህርት የቀረበውን መርሃ ትምህርት የመማሪያ መፅሐፍት መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅና ትምህርቱ ሲጠናቀቅ ለተማሪዎች የሚቀርብ ፈተና ነው በማለት ይገልጻሉ።

ባጠቃላይ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሲማሩ የቆዩትን ይዘቶች መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ የፈተና አይነት ነው።

እንደ Heaton (1975) ገለጻ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ዝግጅት የሚከናወነው በአብዛኛው በመምህሩ ሆኖ የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎትና ዕውቀት ለመለካት የሚያስችሉ ናቸው። የፈተናው አይነት የተለመደ በሰፊው አገልግሎት ላይ የሚውልና መምህራን የተማሪዎቻቸውን የቋንቋ ብቃት ለመገምገም የሚጠቀሙበት የፈተና አይነት ነው።

የችሎታ መለኪያ ፈተና ከመማር ማስተማር ጋር ጥብቅ የሆነ ግንኙነት ስላላቸው ለዝግጅታቸው መሰረት የሚያደርጉት አንድን በተግባር ላይ ያለን ትምህርት፣ መርሃ ትምህርትንና የማስተማሪያ መፅሐፍትን ነው (Hughes፣1989)። በሌላ አገላለጽ በመርሃ ትምህርቱ ላይ ተመስርተው የሚዘጋጁ በመሆናቸው ከመማር ማስተማር ስራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። በመሆኑም በመርሃ ትምህርቱ የተካተቱትን ይዘቶችና ዓላማዎች መሰረት ስለሚያደርጉ ፈተናዎቹ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የሚረዱ መረጃዎችን በመስጠት በኩል ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል።

ከዚህም የተነሳ የችሎታ መለኪያ ፈተና ዓላማ ተማሪው እንዲማረው ከተደረገው የቋንቋ ትምህርት ምን ያህሉን ተምሮታል ወይም አውቆታል የሚለውን ለመገምገም የሚወጣ የፈተና ዓይነት ነው (Underhill፣ 1987)።

ደጀኔ (1994) እንደሚገልጹት የችሎታ መለኪያ ፈተና ሦስት መሰረታዊ ጉዳዮችን ይይዛል፤ እነዚህም

1.ብዙ ጊዜ ተማረው ተምሮታል ተብሎ የሚታሰብ መርሃ ግብር ላይ የተመሰረተ ነው፣

2. የተሰጠውን ትምህርት ማጠናከር አለበት፣

3. ዘዴው የመማር ማስተማሩን አቀራረብ ማንፀባረቅ ይጠበቅበታል። የሚሉ ናቸው።

ከነዚህ ሶስት ነጥቦች መረዳት የሚቻለው የችሎታ መለኪያ ፈተና መሰረት የሚያደርገው ተማሪዎች ይማሩታል ተብሎ የሚታሰበውን መርሃ ትምህርት በመሆኑ በክፍል ውስጥ የተሰጡትን ትምህርቶች በሚገባ ማሳየት አለበት፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን ሐሳብ መረዳት የምንችለው የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪዎች ክፍል ውስጥ የተማሩትን ትምህርት ‹ምን ያህል አውቀዋል?› የሚለውን ጥያቄ መመለስ አላማ አድርገው የሚዘጋጁ በመሆናቸው ተማሪዎች ይህንን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲዘጋጁ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም የችሎታ መለኪያ ፈተና በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑንና ከመማር ማስተማር ሂደት ተነጥሎ የሚታይ አለመሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

## 2.4.4.1 የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችና የመርሃ ትምህርት ዝምድና

የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ማስገኘት ያለባቸውን ፋይዳ እንዲያስገኙ የተነሱበትን ዓላማ ከግብ እንዲያደርሱ በቀረበው መርሃ ትምህርት ላይ መመስረት አለባቸው፡፡ Bachman (1990) እና Harrison፡፡ (1989) ይህንን ሀሳብ ሲያጠናክሩ ተማሪዎች በቀረበው ትምህርት ላይ ያላቸውን ዕውቀት ለማወቅ በመርሃ ትምህርቱ ላይ ሊመሰረት እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ ይህም ማለት የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪዎች ክፍል ውስጥ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል ተገንዝበዋል? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ዓላማ አድርገው ከመዘጋጀታቸው የተነሳ ተማሪዎች ለተወሰኑ ጊዜያት የተማሩትን የቋንቋ ትምህርት በሚያንፀባርቅበት መንገድ መዘጋጀት አለባቸው ማለት ነው፡፡

Madsen (1983) እንደሚገልጹት የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርገው መዘጋጀት ሲኖርባቸው ወካይነታቸው የጎላ እንዲሆን በመርሃ ትምህቱ ውስጥ ቦታ የተሰጣቸው ይዘቶች መመርመር ይገባል፡፡ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የረጅም ጊዜ የክፍል ውስጥ ተግባራት መገለጫዎች በመሆናቸው መርሃ ትምህርቱን የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው፡፡ ይህንንም ዕውን ለማደረግ የትምህርቱን ዓላማና ይዘት የሚያሳይ ንድፍ ቢኖር የፈተናውን ውጤት ተገቢ ያደርገዋል፡፡ በሌላ አባባል የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርገው መዘጋጀታቸው በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ውክልና እንዲያገኙ ከማድረጉም በበለጠ የሚጠበቀውን እውቀት ለመገምገም እገዛ ያደርጋል፡፡

### 2.4.4.2 ናሙና

እንደ Heaton (1990) ገለጻ ከሌሎች የቋንቋ ፈተና አይነቶች ይልቅ በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ውስጥ ምን መካተት እንዳለበት መወሰን ያዳግታል፡፡ ምክንያቱም ተማሪው ለረዥም ጊዜ ሲማረው የቆየውንና ይማረዋል ተብሎ የሚገመተውን እንዲመዝን ስለሚጠበቅ በሚዘጋጁት ጥያቄዎች ውስጥ የትምህርቱን ወካይ ናሙናዎች በብርቱ ጥንቃቄ መርጦ ማካተት ስለሚያስፈልግ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ Madsen (1983) እና Bachman (1990) እንደሚሉት የፈተናውን ናሙናዎች ስንመርጥ ለክሂሎችና ዘርፎች የተሰጠውን ትኩረት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል፡፡ በሌላ አባባል ፈተናዎቹ ሲዘጋጁ በደረጃው በተማሩት ይዘቶች ላይ ተገቢና ሚዛናዊ ትኩረት በሚሰጥ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም የተዘጋጁት ፈተናዎች ተማሪዎቹ የተማሯቸውን ይዘቶች በተመጣጠነ መልኩ ወካይ ናሙና እንዲኖራቸው ያግዛልና ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ Weirም (1993) በመምህሩ የሚዘጋጁ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪዎች ለተወሰነ ጊዜያት የተማሩትን ትምህርት በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤ ለመገምገም ከመዘጋጀታቸው አንጻር ፈተናው ትምህርቱን በሚወክልበት መንገድ መዘጋጀት እንደሚኖርባቸውና ለደረጃው የተነደፉት ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው በፈተናው ውስጥ ውክልና ሊያገኙ እንደሚገባቸው ይገልጻሉ፡፡

ከላይ ካነሳናቸው ሀሳቦች የምንረዳው አንድ የችሎታ መለኪያ ፈተና ሊይዘው የሚችለው ለትምህርቱ ከቀረቡት ይዘቶች ወካይ ናሙና ጥያቄዎችን ብቻ ነው፡፡ ሁሉንም የትምህርት ይዘቶች በፈተናው ማካተት የማይቻል፤ ቢፈለግ እንኳን ሊፈጸም የማይቻል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሰፊ ክፍለ ጊዜ ተሰጥቶት ተማሪዎች የተማሩት ይዘት አጭር ክፍለ ጊዜ ተሰጥቶት ከቀረበ ይዘት ይልቅ በርከት ያሉ ናሙና ጥያቄዎችን በፈተናው ያስመርጣል፡፡ ይህም ማለት የፈተናው ጥያቄዎች ትምህርቱን ሊያንጸባርቁ የሚችሉ ወካይ ሊሆኑ ይገባል ማለት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የተዘጋጀ ፈተና ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት መገንዘብ አለመገንዘባቸውን ለመረዳት ያስችላል፡፡

በአጠቃላይ በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ውስጥ የናሙና አወሳሰድ ብርቱ ጥንቃቄ የሚያሻ ጉዳይ ነው፡፡ ሁሉንም የትምህርት ይዘቶች ለፈተና ማቅረብ ባይቻልም በተቻለ መጠን በዛ ያሉ

ጥያቄዎችን በማቅረብ የትምህርር ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው ወካይ ናሙና እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ይዘቶችንና ያላቸውን ትኩረት በግልጽ የሚያሳይ የፈተና ንድፍ በእጅጉ ጠቃሚ ነው (Harrinson፣1989)። የፈተና ንድፍ ስንል ፈተናው ከመዘጋጀቱ በፊት ፈተናው ምን ምን ነገሮችን ማካተት አለበት የሚለውን የሚመልስ ነው። እንደ Alderson and etal (1995) ገለጻ የፈተና ንድፍ (እቅድ) የፈተናው አላማ ምንድነው? የተማሪዎች እድሜ፣ የክፍል ደረጃና ብስለት ምን ይመስላል? በፈተናው የሚካተቱ ጥያቄዎችና በስራቸው የሚኖረው ጥያቄ ብዛት ምን ያህል ነው? የትኛው የትምህርር ይዘት በፈተናው ይካተት? እያንዳንዱ ይዘት በምን ያህል ጥያቄዎች ይወከል? የሚሉትን መሰል ጥያቄዎች የያዘ ነው። ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው አንድ የፈተና አዘጋጅ አስቀድሞ የተዘጋጀ የፈተና ንድፍ ቢኖረው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ወካይ ናሙና እንዲኖራቸው ያግዛል።

### 2.4.4.3. የችሎታ መለኪያ ፈተና ጥያቄዎች አዘገጃጀት

ፈተናዎች እንደሚዘጋጁበት ዓላማ የተለያዩ ዓይነት ጥያቄዎችን በውስጣቸው ያካትታሉ። Callhan and Clark (1988) እንደሚያስረዱት በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የሚካተቱት አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች ምርጫ ሰጪ (objectives) እና አታች (subjective) በሚል በሁለት ይከፈላሉ። እነዚህ የጥያቄ ዓይነቶች ደግሞ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉት በተገቢ መርሆች ላይ ተመስርተው ሲዘጋጁ ነው።

የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት ሁሉም ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙት ጥያቄዎች የቀረቡበት መንገድ ከምርጫ ሰጪ የጥያቄ ማቅረቢያ ዘዴዎች ውስጥ የባለብዙ ምርጫ ሰጪ (Multiple choice items) በመሆኑ ይህንኑ ዘዴ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ባለ ብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች በተጨባጭ የሚታረሙ ሲሆኑ በትምህርት ቤት ደረጃ በመምህራን ከሚዘጋጁ ጥያቄዎች ተዘውታሪና መምህሩ ያስተማረውን ትምህርት በፈተናው ውስጥ በበቂ ሁኔታ በናሙናነት ለማካተት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ናቸው። እንደ Gronlund (1981) ገለጻ የፈተናውን የመለካት አቅም ከፍ ለማድረግ ከአማራጮች መካከል አንዱ ብቻ ትክክለኛ መልስ እንዲሆን ማድረግ ሌሎችም አሳሳች ምርጫዎች የመመረጥ ዕድል እንዲኖራቸው አድርጎ መቀረፅ ሊተኮርበት ይገባል።

እነዚህ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ተማሪዎች ምን እንደተጠየቁ ለማወቅ እንዲረዳቸው የጥያቄው ግንድ የተሟላ መረጃ እንዲይዝ ማድረግ፣ ጊዜን ለመቆጠብና መደናገርን ለማስቀረት በምርጫዎች ላይ

አንድን ሀሳብ ከመድገም ይህንኑ ሀሳብ በጥያቄው ግንድ ላይ ማስፈር፣ አጭርና ግልፅ ጥያቄዎችን መጠቀም፣ አሉታዊ ቃላትን ማስወገድ አስፈላጊ ከሆነም ከስራቸው ማስመር ወይም ጎላ አድርጎ መጻፍ ይገባል፡፡ ፍንጭ ላለመስጠት አማራጮችን በእርዝመት ማመጣጠን፣ ፍንጭ ሰጪ ቃላትን በጥያቄውም ሆነ በምርጫዎቹ ውስጥ አለመጠቀም እንዲሁም ሁሉም አማራጮች በሃሳብም ሆነ በንበት ከጥያቄው ግንድ ጋር እንዲጋጠሙ ማድረግ ይገባል፡፡

ከዚህ ሌላ ባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ አንድ ጥያቄ በእርግጠኝነት አንድ መልስ ብቻ እንዲኖረው ማድረግ፣ ትክክል ያልሆኑ አሳሳች አማራጮች ቢያንስ በተወሰኑ ተማሪዎች የሚመረጡ እንዲሆኑ ማድረግ ተማሪዎች የተወሰኑ ምርጫዎችን ብቻ ካወቁ ሌሎችን ባያውቋቸው እንኳ መልሱን በቀላሉ ለማግኘት ስለሚረዳቸው የፈተናውን የምልከታ አቅም ከፍ ለማድረግ ሁሉም መልስ ነው የሚሉ አማራጮችን አለመጠቀም ይገባል፡፡ መልስ የለም የሚሉ አማራጮችን ደግሞ አልፎ አልፎ ብቻ መጠቀም ተማሪዎች አማራጮችን እያወዳደሩ ትክክለኛውን መልስ ለማግኘት እገዛ እንዳያደርግላቸው አማራጮችን ቁልቁል መደርደርና በተከታታይ አንድ ዓይነት መልሶችን አለማስቀመጥ ወይም መልሶችን ማዘበራረቅ እንደሚገባ Alderson and et al. (2001) እና Hughes (1989) ይገልጻሉ፡፡

## 2.5. የጥሩ ፈተና መስፈርቶች

የቋንቋ ፈተናዎች የታሰበላቸውን ዓላማ ከግብ ያደርሱ ዘንድ በጥንቃቄ ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ ፈተናዎችን በጥንቃቄ ለማዘጋጀት ደግሞ የጥሩ ፈተና መስፈርቶችን ማወቅ ግድ ይለናል፡፡ በርካታ ምሁራን የጥሩ ፈተና መስፈርቶች ብለው የሚያነሷቸው ነጥቦች ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም ተገቢነት (validity) ፣ ህያውነት (reliability) እና ተተግባሪነት (practicality) በመባል ይታወቃሉ፡፡ በመሆኑም አንድ የቋንቋ ፈተና በሚገባ ተዘጋጅቷል የምንለው እነዚህን የፈተና መስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ ቀጥለን ስለ ሦስቱ የጥሩ ፈተና መስፈርቶች በዝርዝር እናያለን፡፡

### 2.5.1. ተገቢነት (validity)

አብዛኞቹ ምሁራን ተገቢነትን በተመሳሳይ መልኩ ሲበይኑት ይስተዋላል፡፡ ከነዚህም ውስጥ Heaton (1975)፣ Harrision (1989) እንዲህ ገልጸውታል፡፡ አንድ ፈተና ተገቢነት አለው

የሚባለው መመዘን ያለበትን ነገር በትክክል መመዘን ሲችል ነው። በመሆኑም ፈተናው ለመፈተን ካሰበው ዓላማ ውጪ መሆን የለበትም ይላሉ።

Heaton(1975) ይህንን ጉዳይ በምሳሌ ሲያስረዱ የዕህፈት ክሂልን ለመመዘን ታስቦ ተማሪው ‹‹ፎቶግራፍ ማንሳት ጥበብ ነው ወይስ ሳይንስ ?›› ተብሎ ቢጠየቅ የተጠየቀው ርዕሰ ጉዳይ ከዕህፈት ክሂሉ ውጭ የፎቶ ግራፍ ዕውቀትን የሚጠይቅ በመሆኑ ምዘናው ተቢነት የለውም። ስለዚህ አንድ ፈተና ተገቢነት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጉዳይ ለሁሉም የፈተና አዘጋጆች እና የፈተና አይነቶች ተገቢ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም አንድ ፈተና ለተዘጋጀለት አላማ ተገቢነት ከሌለው ከፈተናው ይገኛል ተብሎ የሚታሰበው ውጤት ትክክለኛነት አጠያያቂ ይሆናል (Alderson and etal፣ 1995)።

ከእነዚህ ምሁራን ሀሳብ የምንረዳው አንድ ፈተና ተገቢነት አለው የምንለው ፈተናው ለመመዘን የታሰበውን የቋንቋ ክሂል በትክክል መመዘን ሲችል ነው። በመሆኑም አንድ የቋንቋ ክሂል ለመመዘን ታስቦ የተዘጋጀ ፈተና ከዚያ ውጭ የሌላ ጉዳይ ዕውቀትን የሚጠይቅ ከሆነ በፈተናው ተገቢነት ላይ ጥያቄ ያስነሳል።

የተገቢነት ዓይነቶች በርካታ ናቸው፤ ይሁን እንጂ Devis (1984) እንደሚገልጹት የችሎታ መለኪያ ፈተናዎችን ለመገምገሚያነት የሚያገለግሉ የተገቢነት ዓይነቶች የይዘትና የላህያዊ ተገቢነት ናቸው በማለት ይገልጻሉ። በመቀጠል እነዚህን በዝርዝር እንመልከት።

#### 2.5.1.1 የይዘት ተገቢነት (Content validity)

አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው የሚባለው ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው ይዘት ጋር በቀጥታ ሲያያዝ ነው። ይህንን አስልክተው Finochiaro and Brumfit፣(1983) አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው የሚባለው ፈተናው የተመሰረተበትን መርሃ ትምህርት በትክክል ካንጸባረቀ ነው ይላሉ። Heatonም (1975) እንደዚሁ አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው የሚባለው የቋንቋውን ይዘት ወካይ የሆኑ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ሲካተቱ እንደሆነ ያስረዳሉ። Hughes (1989) በበኩላቸው ተገቢ ናቸው የሚባሉት የቋንቋ ይዘቶች ላይ ተመስርቶ ይዘቶቹን በተመጣጠነና ወካይ በሆኑ ናሙናዎች የሚያቀርብ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው ሊባል ይችላል በማለት የገለጹ ሲሆን፤ እነ Alderson and etalም(1995) ይህንን ሐሳብ ይጋሩታል።

Heaton (1975) እና Brown (1970) ስለ ይዘት ተገቢነት ሲያስረዱ፣ ፈተና በክፍል ውስጥ የተካሄዱትን የመማር ማስተማር ተግባራት በናሙናነት የሚወክል ከሆነ የይዘት ተገቢነት ይኖረዋል። ለምሳሌ የምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ በአንድ አካባቢ ያሉና ለማዘጋጀት የሚቀሉትን መምረጥ ወይም ስነድምፅ ለመፈተን ጫናንና ቃናን በመተው በድምጾች ቅርፅ ላይ ብቻ ማተኮር የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ስለሚቀንስ ተማሪዎች የተማሩትን እያንዳንዱን ይዘት ከተሰጣቸው ትኩረት አንጻር በፈተናው ውስጥ ውክልና እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል በማለት ያስረዳሉ።

እንደዚሁም Hughes (1989) አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት እንዲኖረው ከተፈለገ ዝግጅቱ በፈታው ንድፍ ላይ መመስረት እንዳለበትና ይህን ማድረጉ ደግሞ ይዘቶች በፈተናው ሳይካተቱ እንዳይቀሩ ከመርዳቱም በላይ ፈተናው ጠቃሚ በሆኑና ትረኩት በተሰጣቸው የትምህርት ክፍሎች ላይ እንዲያተኩር ያደርገዋል በማለት ይገልጻሉ። ይህም የሚያመለክተው የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ለመጠበቅ የፈተና አውጪዎች የፈተና ንድፍ ላይ መሰረት ቢያደርጉ የፈተናውን የይዘት ተገቢነት መጠበቅ ይቻላል።

በአጠቃላይ የይዘት ተገቢነት ተማሪዎች የተማሩትን የቋንቋ ይዘቶች በተገቢው የጥያቄ መጠን መወከል እንዳለባቸውና ተገቢውን ዓላማ መመዘን እንዳለበት ያስገነዝበናል።

የአንድን ፈተና የይዘት ተገቢነት ለመመርመር የሚረዱ ሶስት የአጠናን ስልቶች መኖራቸውን Alderson and etal(1995) ያመለክታሉ። አንደኛው የፈተናውን ይዘት ከመርሃ ትምህርቱ ይዘት ጋር በማነጻጸር ስልት ነው። ሁለተኛው መጠይቆችን ቃለ መጠይቆችን በማዘጋጀት ባለሙያዎች ማለትም መምህራን፣ በትምህርቱ የላቀ ችሎታ ያላቸው የመስኩ ምሁራን፣ የተግባራዊ ስነ ልሳን ሊቃውንት መጠይቆችን እንዲሞሉ በማድረግ ነው። ሶስተኛው በፈተናው ጥያቄዎችና ጽሁፎች ላይ የባለሞያዎችን ዳኝነት መጠቀም ነው። በዚህ ጥናትም ተግባራዊ የተደረገው የይዘት ተገቢነት የማጥኛ ወይም የመገምገሚያ ስልት ከላይ ከቀረቡት የይዘት ተገቢነት መገምገሚያ ዘዴ አንዱ የሆነው የፈተናው ይዘት ከመርሃ ትምህርቱ ይዘት ጋር በማነጻጸር ነው።

### 2.5.1.2.. የላህያዊ ተገቢነት /Face Validity/

ላህያዊ ተገቢነት ተፈታኙ፣ መምህሩ እና ሌሎች የመስኩ ባለሙያዎች ስለፈተናው በሚሰጡት አስተያየት ላይ የተመረኮዘ ነው። በመሆኑም አንድ ፈተና ላህያዊ ተገቢነት አለው የሚባለው በእነዚህ ሰዎች ፈተናው ተገቢ መምሰል ሲችል ነው። ፈተናው ለተማሪዎቹ ቀሏቸዋል ወይስ ከብዷቸዋል የሚሉትን ጥያቄዎች አፋዊ በሆነ መልኩ የሚመልስ መሆን አለበት።

የላህያዊ ተገቢነት የአንድን ፈተና የላዕላይ ተአማኒነት ወይም የህዝብ ተቀባይነት የሚመለከት እንደሆነ Alderson and etal(1995) ያስረዳሉ። ይህም ማለት የላህያዊ ተገቢነት አንድ ፈተና በላዕላይ ገጽታው የሚኖረውን ተቀባይነት የሚመለከት ነው። እንዲሁም Hughes (1989) አንድ ፈተና የላህያዊ ተገቢነት አለው የሚባለው እንዲመዝን የተፈለገውን የሚመዝን መስሎ ከታየ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ደጀኔ (1990) ፈኖቺኖና ሳኮን (1983) ጠቅሰው አንድ ፈተና ላህያዊ ተገቢነት አለው ለመባል ፈተናው ትክክል ወይም ተገቢ የመምሰል ባህሪም ሊኖረው እንደሚገባ ያስረዳሉ።

በተጨማሪም ምሁራኑ እንደሚሉት ተማሪዎች የሚፈተኑት ፈተና የላህያዊ አግባብነት ያለው መስሎ ካልታያቸው መስራት የሚገባቸውን በሚገባ እንዳይሰሩ መሰናክል ሊሆንባቸው እንደሚችል ነው። ተፈታኞች የሚፈተኑት ፈተና የላህያዊ ተገቢነት ያለው እንደሆነ አድርገው ከተገነዘቡት በተቻላቸው መጠን ያላቸውን ችሎታ ሁሉ ተጠቅመው ለመስራት እንደሚጥሩና ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ እንደሚሞክሩ ይህም የላህያዊ ተገቢነት ጥያቄዎችን በተገቢው መንገድ በመመለስ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑን Alderson and etal(1995) ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ አንድ ፈተና ላህያዊ ተገቢነት አለው የሚባለው ፈተናው ለተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለሌሎች ተገቢ መምስል የቻለ እንደሆነ ነው።

### 2.5.2. ህያውነት (Reliability)

ይህ ሌላው የጥሩ ፈተና መሰፈርት ነው። Hughes (1989) እና Brown (1980) እንደሚገልፁት ህያውነት አንድ ፈተና ወይም ሁለት ተመጣጣኝ ፈተናዎች ለተመሳሳይ ተማሪዎች ከአንድ ጊዜ በላይ ተሰጥተው የሚገኘውን የውጤት ወጥነት (consistancy) የሚያመለክት መሆኑን ይስማሙበታል። ህያውነት ያለው ፈተና በውስጡ የያዛቸው ጥያቄዎች እርስ በርስ የተዛመዱና አንድን ባህሪ ወጥ በሆነ መልኩ ለመለካት የሚችሉ ይሆናሉ። በሌላ

አገላለጽ ፈተናው በተለያየ ጊዜ ወይም ሁኔታ ለተፈተኞች በሚቀርብበት ጊዜ የሚገኘው ውጤት ምን ያህል ተመሳሳይ መሆኑን ወይም በአንድ ፈተና ውስጥ ለሚገኙ ጥያቄዎች ተፈታኙ በዘላቂነት የሰጣቸውን መልሶች መመርመር የህያውነት ተግባር ነው (Heaton፣ 1975)፡፡

ህያውነት የአንድ ፈተና ተከታታይ ውጤት ተመሳሳይነት ነው፡፡ ህያው ፈተና አይወላውልም፡፡ (Gronlund፣1981)፡፡ እንደ Alderson and etal(2001) ገለጻ በአንድ ፈተና ህያውነት ላይ ተጽዕኖ የሚያደርጉ የተለያዩ ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህም አንድን ፈተና ተመሳሳይ ተማሪዎች በተለያየ ጊዜ ቢወስዱትና ያመጡት ውጤት የተለያየ ቢሆን ልዩነቱ የሚመጣው በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው በእውነተኛ ልውጠት ለምሳሌ ፈተናው የሚጠይቀው ክሂል ላይ ተማሪዎች የሚያሳዩት መሻሻል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተለያዩ ተጽዕኖዎች ለምሳሌ ከተማሪው ግላዊ ችግርና ከፈተና ክፍሉ አመቺ አለመሆን ወዘተ ሲሆን ይችላል፡፡

### 2.5.3.ተተግባሪነት (practicality)

ተተግባሪነት ማለት ፈተናውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ወጪዎችና የሰው ሀይል የሚመለከት ነው፡፡ይህ የፈተና መስፈርት ምናልባት ፈተናው ለበርካታ ተማሪዎች የሚሰጥ ከሆነ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም የፈተናው ተተግባሪ አለመሆን ቀደም ባሉት መስፈርቶች ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

Brown (1980) እንደሚገልጹት አንድ ፈተና ተተግባሪ መሆን አለበት ሲባል ከገንዘብ አቅም፣ ከጊዜና ከሰው ሃይል፣ ፈተናውን ፈትኖ ውጤቱን አርሞ እስከ መተርጎም ያለውን ተፈጻሚነት ሁኔታ ይመለከታል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ Weirም (1993) ተተግባሪነት ከጊዜ ከጉልበትና ከቁሳቁስ አቅም ጋር ተይይዞ የሚታይ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

እንደ Hughes (1989) ገለጻ ደግሞ አንድ ፈተና ተተግባሪነት እንዲኖረው የሚከተሉት ሁለት ነጥቦች መሟላት አለባቸው፡፡

1. ዝግጅት፡- ይህ ፈተናው ሰፋ ያለ ጊዜ ተሰጥቶ በጥንቃቄ እንዲዘጋጅ የሚያሳሰብ ሲሆን በዝግጅቱም ወቅት አንደኛ ፈተናውን ለማዘጋጀት የምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶች፣ ሁለተኛ የፈታኞች ምደባ፣ ሦስተኛ የተፈታኞች አቀማመጥ፣ አራተኛ መፈተኛ ክፍሎች ዝግጅት እና የመሳሰሉት በደንብ ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

2. የፈተናው አሰጣጥ፡- ፈተናው በሚሰጥበት ወቅት ያለውን የአሰጣጥ ሂደት ይመለከታል። ለምሳሌ ከፈታኝና ከተፈታኞች የሚጠበቅ ዲስፒሊን፣ የፀጥታ አጠባበቅ፣ ዘግይተው የሚመጡ ተማሪዎች ሁኔታ ወዘተ በምን መልክ መካሄድ እንዳለበት የሚወሰንበት ነው (Hughes, 1989)።

ይህም ማለት ፈተናው ሲዘጋጅ እነዚህ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ፈተናውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሁሉ የተሟሉ መሆናቸውንና የፈተናውን ተፈጻሚነት የማያግቱ መሆናቸውን የምናረጋግጥበት መንገድ ነው።

ከላይ ከተነሱት ሐሳቦች መረዳት የሚቻለው ተተግባሪነት ፈተናው ከሚወስደው ጊዜ፣ ወጪ እና የሰው ኃይል አንጻር ነው። እነዚህ ባልተሟሉበት የሚዘጋጅ ፈተና የተተግባሪነት ደረጃው ሊቀንስ ይችላል ።ለምሳሌ አንድ የቋንቋ መምህር በመቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ለመመዘን ፈተና ቢያዘጋጅ ፈተናውን አርሞ ለመመለስም ሆነ ብቻውን ፈተናውን ለመፈተን ይቸገራል፤ በመሆኑም የፈተናው ተተግባሪነት አጠያያቂ ይሆናል ማለት ነው።

## 2.6. የፈተና አዘገጃጀት ዝርዝር መርሆች

ማንኛውም የቋንቋ ፈተና ሲዘጋጅ አዘጋጆች ሊከተሉት የሚገባቸው በርካታ መርሆች አሉ። በዚህ ክፍል የፈተና አዘገጃጀት መርሆች የሆኑ ዝርዝር ነጥቦች እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

- ለምን እንደምትፈትን ወይም የምትፈትንበትን ዓላማ ማወቅ። ይህ መርህ የትምህርቱን ዓላማ ጠንቅቆ በመረዳት አንድ ፈተና አዘጋጅ ምን ለመፈተን እንደፈለገ ግልፅ የሆነ ዓላማ እንዲኖረው የሚጠይቅ ነው። በዚህም ፈተናው ጠቃሚ ችሎታዎችን እንዲመዝን ይጠበቃል፣
- የፈተናው መመሪያዎች ግልጽ፣ አጭርና ቀላል መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- ፈተናው በተስማሚ የጥያቄ አቀራረብ ስልት መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣
- ሰፋ ያለና ወካይ ናሙና ማቅረብ

ሰፋ ያለ ናሙና ለማቅረብ በርከት ያሉ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ጠቃሚ ነው፤ ጥያቄዎቹ ወካይ ናሙና እንዲሆኑ ለማድረግ ደግሞ ጠቅላላ ፈተናውን በዓላማና ይዘት ከፋፍሎ ከይዘቱ ተመጣጣኝ የሆነ ቁጥር መውሰድ አስፈላጊ ነው።

- በፈተናው ውስጥ አላስፈላጊ ወገናዊነትን (Bias) የሚያሳዩ ጥያቄዎችን ማስወገድ ይህ መርህ በፈተናዎቻችን ውስጥ የጾታ፣ የባህል፣ የእምነት ወዘተ ወገናዊነት እንዳይኖር ማድረግን የሚጠይቅ ነው፡፡ ለምሳሌ ለአጠቃላይ ተግባቦታዊ ፈተና በሚዘጋጁ የቃላት ጥያቄዎች ውስጥ ሙያ ወይም ዘዬ ነክ ቃላት ቢቀርቡ ለተወሰኑ ተፈታኞች አድሎአዊነት ስለሚኖራቸው ተቀባይነት የላቸውም፡፡
- ፈተናውን ለማዘጋጀት ሰፊ ትእግስት እንዲኖር መጣር
- ፈተናው በምርጫ ሰጪ የጥያቄ አቀራረብ ስልት የሚቀርብ ከሆነ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ መኖሩን ማረጋገጥ
- የፈተናው ባክዋሽ ጠቃሚ እንዲሆን መጣር፡፡ ይህ መርህ በተቻለ መጠን ፈተናው ለጥሩ ማስተማር ድጋፍ እንዲሰጥ መጥፎ ማስተማርን ደግሞ እንዲያስተካክል ለማድረግ የሚያስችል ነው (ሂዩዝ፣1989፤ማድሰን፣1983 እና ደጀኔ ፣1994)፡፡

## 2.7. ሰዋስውን ማስተማርና መፈተን

ሰዋስውን ማስተማርና መፈተን ከመመልከታችን በፊት ሰዋስው ምንድነው ? የሚለውን እንመልከት፡፡ የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን ስለሰዋስው ምንነት በሰፊው ገልጸውታል፤ ለምሳሌ ባዬ (1987) ሰዋስው የአንድ ቋንቋ ሥርዓት ከድምፅ እስከ ሀረግ አመሰራረት ድረስ ያለውን የሚያሳይ ሳይንስ ነው በማለት ገልጸውታል፡፡

ጌታሁን (1990) በበኩላቸው የሰዋስውን ፍቺ በሁለት ዓይነት መልኩ ይመለከቱታል፤ አንደኛው ፍቺ የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ቋንቋ ‹እውቀት› የሚጠቀመውና በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ያለውን ችሎታ ነው፡፡ የሰው ልጅ ቋንቋውን ሲያውቀውና ሲጠቀምበት የሚችለው ይህ ችሎታ ስላለው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ሰዋስው አእምሮአዊ እሳቤ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለቋንቋ ስርአት እና መዋቅር የሚያደርጉትን ገለጻ የሚጠቁም ነው፡፡ ይህ ፍቺ የአንድ ቋንቋ የስርዓት ጥናት የሚመለከት ስለሆነ ከመጀመሪያው ጠበብ ይላል በማለት ገልፀውታል፡፡

Brown (1994) ስለሰዋስው ሲገልፁ ሰዋስው የቋንቋ ሰርዓት ነው ይላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ስርዓት በሚያተኩርባቸው ጉዳዮች ላይ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ በዚህ መሰረት ብዙዎቹ ብያኔዎች ዐ.ነገርን መሰረት ያደረጉና ሰዋስው የቃላትን የቅንጅት ስርዓት የሚመለከት፣ በዐ.ነገር ደረጃ

የሚታይና የቋንቋውን ተናጋሪዎች ስምምነት መሰረት ያደረገ ቅደም ተከተላዊ የቃላት አገባብ ነው፡፡ ስለዚህም በዚህ አገላለጽ መሰረት ሰዋስው የቋንቋን አገባባዊ ስርዓት የሚመለከት ነው፡፡

Ur (1996) ግን ይህንን የብራውንን ሀሳብ አይቀበልም፡፡ እንደ Ur ገለፃ ሰዋስው በዐ.ነገር ደረጃ የማይገደብ ሲሆን፣የቋንቋ የአገባብ ስርዓት ደግሞ ድምፆች ምዕላድን ወይም ቃላትን ለመመስረት ከሚፈጥሩት ቅንጅት የሚጀምርና እስከ ዐ.ነገር ምስረታ ድረስ የሚዘልቅ ነው፡፡ በመሆኑም ድምፀ ልሳናት የቃልን መዋቅር ሲመሰርቱ፣ ምዕላዶች ደግሞ ሌላ መዋቅር የሚፈጥሩት በዘፈቀደ ሳይሆን የቋንቋውን ስርዓት ተከትለው ነው፡፡ ስለዚህ ሰዋስው ማለት ከድምፅ ጀምሮ እስከ ዐ.ነገር ያለውን የመዋቅር ስርዓት የሚመለከት ጥናት ነው በማለት ይገልፁታል፡፡

በዚህ መሰረት ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ስርአት ከድምጽ እስከ ዐ.ነገር ድረስ ያለውን መዋቅር የሚያጠና ሳይንስ ነው፡፡ በመሆኑም ሰዋስው አጠቃላይ የቋንቋ መዋቅራዊ ስርአት መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

### 2.7.1. ሰዋስውን ማስተማር

ሰዋስው በማስተማር አስፈላጊነት ላይ በተካሄዱት ክርክሮች ተቃራኒ አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡ ሰዋስው የማስተማርን አስፈላጊነት የሚቃወሙ ወገኖች የሚያነሱት ሀሳብ የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማለትም መናገር፣ ማዳመጥ፣ መጻፍና ማንበብ በብቃት ማሰጨበጥ እንጂ ስለቋንቋው መግለፅ አይደለም ይላሉ፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ አብዛኛው አፍፈት ተናጋሪዎች ስለቋንቋው የመግለፅ ችሎታ ሳይኖራቸው ቋንቋውን አቀላጥፈው በብቃት እንደሚጠቀሙበት ያስረዳሉ፡፡

በሌላ በኩል ይህንን ሀሳብ የሚቃወሙት ወገኖች ደግሞ የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ያነሳሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ Ur (1996) እንደሚገልጹት የማንኛውም ቋንቋ ተናጋሪ በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ሀሳቡን በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ለመግለጽ እንዲሁም የሌላውን ሰው መልእክት በትክክል ለመረዳት የሰዋስው እውቀት ያስፈልገዋል፡፡ Brown (1994) ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ክህሎትን ከማዳበር ባሻገር የቋንቋው ተማሪ ሊገነዘበው የሚገባውን ዕውቀት ማካተት ይኖርበታል፤ ይህም እውቀት የቋንቋ ስርዓት ወይም ሰዋስው ነው ይላሉ፡፡ በዚህም መሰረት አፍ መፍቻም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋን ከተግባቦታዊ አገልግሎት በተጨማሪ ሰዋስዋዊ ስረዓቱን መማርም ሆነ ማስተማር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የቋንቋ ዕውቀትና ችሎታ የሚለካው

ተግባቦታዊ አገልግሎቱን ከነስርዓቱ አቀናጅቶ መገንዘብ በመሆኑ ሰዋስውን መማርም ሆነ ማስተማር የግድ ያደርገዋል፡፡

ከላይ ከጠቀስናቸው ሀሳቦች መገንዘብ የምንችለው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስውን ማስተማር የግድ መሆኑን ነው ምክንያቱም አንድ የቋንቋ ተማሪ ቋንቋውን ችሏል የሚባለው ከአራቱ ክሂሎች በተጨማሪ የቋንቋውን ሰዋስው ጠንቅቆ ሲያውቅ መሆኑንን ነው፡፡

እንደ Larsen Freeman. (1997፣18-19) ገለፃ "በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስው አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም፣ ምክንያቱም ቋንቋ በትምህርትነት ከማቅረባችን በፊት የቋንቋን ተፈጥሮ፣ አሰራርና ባህሪያት ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡ ከቋንቋ ባህሪያት ውስጥ ደግሞ አንዱ ስርአቱ ነው፤ ስርአቱ የሚጠናው ደግሞ በሰዋስው ትምህርት ነው፡፡" በማለት የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

በአጠቃላይ ሰዋስው ማስተማርና መማር ለተሳካ ተግባቦት ተገቢ በመሆኑ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መቅረት የሌለበት ጉዳይ መሆኑን ተመልክተናል የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት አይቀሬ ጉዳይ ከሆነ የተማሪዎችን የሰዋስው ዕውቀትን ለመመዘን ስለሚዘጋጅ የሰዋሰው ፈተናዎች እንመልከት፡፡

### 2.7.2. ሰዋስውን መፈተን

ቋንቋን ማስተማርና ቋንቋን መፈተን የማይነጣጠሉ ተግባሮች መሆናቸውን ቀደም ብለን በንዑስ ርዕስ 2.3. ላይ ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ የቋንቋ ፈተና ከሚያካትታቸው ይዘቶች ውስጥ ሰዋስውን በተመለከተ ባጭሩ ለማየት እንሞክራለን፡፡

የሰዋስው ጥያቄዎች ዓላማ  በቋንቋው ሥርዓትና ሕግ መሠረት የተገነቡ ዐ.ነገሮችን የሚመለከት ነው፡፡ የሰዋስው ችግር ያለባቸውን ዐ.ነገሮች፣ ሐረጎች፣ ወዘተ. በጥያቄ በማካተት ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት ጠብቀው እነዚህ ችግር ያለባቸውን ዓረፍተነገሮች፣ሐረጎችና የመሳሰሉትን ማስተካከል መቻላቸውን ወይም ደግሞ ትክክለኛውን ሰዋስዋዊ ስርአት ተከትለው ቋንቋውን መጠቀማቸውን ለመመዘን ሰዋስዋዊ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች በቋንቋ ፈተና ውስጥ ይካተታሉ፡፡

የሰዋስው ፈተናን በተመለከተ Heaton (1975) ሲገልፁ የሰዋስው ፈተና ተማሪዎች በቋንቋው አገባብ ሲገለገሉ የሚያሳዩትን ችሎታ እንዲሁም ትክክለኛ የሆነውን የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ቅርፅ ትክክለኛ ካልሆነው ሰዋስዋዊ ቅርፅ የመለየት ብቃታቸውን የምንለካበት ነው፡፡

በተጨማሪም Kitao and Kitao (1996) የሰዋስው ፈተና በቋንቋ ፈተና ውስጥ ትልቅ ቦታ እንዳለው ገልጸው ተማሪዎች በቋንቋው በሚናገሩበትም ሆነ በሚፅፉበት ወቅት የቋንቋውን ሰዋስው ጠብቀው መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ሰዋስውን መፈተን ግድ ይለናል፡፡ በመሆኑም የቋንቋውን ትክክለኛ አጠቃቀም ለማወቅ ፍቺን ሳይሆን መፈተን ያለብን የቋንቋውን አገባብና ስርዓት ነው በማለት ሰዋስው በቋንቋ ፈተና ውስጥ ሰፊ ቦታ እንዳለው ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም ማለት የተማሪዎችን የሰዋስው እውቀት ለመለካት ሰዋስውን መፈተን ተገቢ ነው፡፡

Hughes (1989) ስለ ሰዋስው ፈተና ሲያስረዱ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስውን ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ ሰዋስዋዊ ይዘት ያላቸውን ጥያቄዎች ለማካተት ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሁል ጊዜ የሚደረግ ከሆነ ፈተናው አሉታዊ ከሆነ ባክዋሽ የፀዳ እንዲሆንና፡፡ የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አይቀሬ ከሆነ የሰዋስው ጥያቄም በቋንቋ ፈተና ውስጥ መቅረት የሌለበት ጉዳይ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

ከላይ ከተነሱት ምሁራን ሃሳብ የምንረዳው የተማሪውን የቋንቋ ብቃት ማለትም ተማሪው በቋንቋው ሲገለገል ያለውን ችሎታ ለመለካት በቋንቋ ፈተና ውስጥ የሰዋስው ፈተና ተገቢ መሆኑን ነው፡፡

### 2.7.3. የሰዋስው ጥያቄዎች አቀራረብ

የተማሪዎችን የሰዋስው ዕውቀት ለመመዘን ፈተናዎቹን በተለያዩ የአፈታተን ዘዴዎች ማዘጋጀት እንደሚቻል Heaton (1975) እና Kitao (1996) ይገልጻሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ምርጫ ሰጪ፣ ስህተትን ማረም፣ ክፍት ቦታ መሙላት፣ የቃላት ቅደም ተከተል ወዘተ. በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

**ምርጫ ሰጪ፡-** የጥያቄ አቀራረብ ዓይነት የሰዋስው ዕውቀትን ለመመዘን በአብዛኛው በአገልግሎት ላይ የሚውል ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ብዙ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ለማቅረብ እና ለማረም አመቺ በመሆኑ በብዙ ፈተና አዘጋጆች ተመራጭ ነው፡፡ ሰዋስዋዊ ዕውቀትን ለመገምገም አብዛኛው የተለመደው የምርጫ ሰጪ አጠያየቅ መንገድ አንድ ያልተሟላ ዐነገር በማቅርብ

ዐ.ነገሩን በትክክል የሚያሟሉ አራት ወይም አምስት አማራጮችን በመስጠት ትክክለኛውን እንዲመርጡ የመጠየቅ ዘዴ ነው (Heaton፣ 1975)::

ሌላው በምርጫ ሰጪ ፈተና ላይ የሰዋስው አፈታተን ዘዴ አንድ ዐ.ነገር ሰጥቶ ከአራቱ ወይም ከአምስቱ አማራጮች በፍቺ አቻ የሆነውን እንዲመርጡ መጠየቅ። እንደ kitao (1996) ገለጻ ይህን ዓይነት አፈታተን አንብቦ መረዳትና የሰዋስው ዕውቀትን የሚጠይቅ ነው። አንድን ዐ.ነገር አንብቦ ለመረዳት ተፈታኙ ሰዋስዋዊ አገባቡን ማወቅ ይጠበቅበታል። በመሆኑም በምርጫ ሰጪ የአፈታተን ዘዴ በእንደዚህ መልኩ የተማሪውን የሰዋስው ዕውቀት መመዘን ይቻላል።

ስህተት የማረም ዘዴ፡- እንደ Heaton (1975) ገለጻ ይህ ዓይነት የአፈታተን ዘዴ የሰዋስው ዕውቀትን ለመፈተን ጠቃሚ ነው። በዚህ ዘዴ ስህተት ያለበት ዐ.ነገር በመስጠት በዐ.ነገሩ ውስጥ የሰዋስው ስህተት ያስከተለው ቃል ወይም ሐረግ እንዲመርጡ በማድረግ ሰዋስዋዊ ዕውቀታቸውን መመዘን ይቻላል።

ክፍት ቦታ መሙላት፡- ይህ የአጠያየቅ ዘዴ ክፍት ቦታ ያለበትን ዐ.ነገር በመስጠት ዐ.ነገሩን እንዲያሟሉ ማድረግ ነው። Kitao (1996) እንደሚገልጹት በዚህ ዘዴ ሰዋስዋዊ ዕውቀትን ለመፈተን በክፍት ቦታው ላይ የሚገቡ ቃላት የአገልግሎት ቃላት መሆን አለባቸው። ይህ ዘዴ በጥንቃቄ ከተዘጋጀ የተማሪዎችን ትክክለኛ የሰዋስው ዕውቀት ለመመዘን አመቺ ነው። እንደ Heaton (1975) ገለጻ ዘዴው የተማሪዎችን ትክክለኛ የሰዋስው ስርአት የማመንጨት ችሎታ ለመመዘን ይረዳል።

ሌላው የተማሪዎችን የሰዋስው ዕውቀት ለመመዘን የሚያስችል የጥያቄ አቀራረብ የቃላት ቅደም ተከተል መጠየቅ ዘዴ ነው። በዚህ ዘዴ አራት ቃላት (ሐረግ) ያለው በመስጠት ቅድም ተከተሉን እንዲያስተካክሉ በመጠየቅ የተማሪዎችን የሰዋስው ዕውቀት መመዘን አንዱ መንገድ እንደሆነ Heaton (1975) ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ እነዚህ መንገዶች የተማሪዎችን ዕውቀት ለመመዘን የሚረዱ የጥያቄ አቀራረብ ዘዴዎች ሲሆኑ በችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ ለመጠቀም አመቺ ዘዴዎች ናቸው።

## 2.8. የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን የገመገሙ ቀደምት ጥናቶች

በአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ላይ የተሰሩ በርከት ያሉ ጥናቶች ለመዳሰስ ተሞክሯል። በዚህም መሠረት ሁለት ለመጀመሪያ ዲግሪ ስድስት ደግሞ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶችን ቀጥለን እናያለን።

አበበ ከበደ (1975 ዓ.ም) "የ6ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ግምገማ" በሚል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ከ1962-1972 ዓ.ም የቀረቡ የ6ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናዎችን ገምግሞ ከ1962-1966 ያሉት ፈተናዎች ከስርዓተ ትምህርቱ ውጭ የሚፈትኑና ብዙ ድክመት ያለባቸው ሲሆኑ ከ1967-1972 ዓ.ም ያሉት ግን ተመሳሳይ ድክመት ቢታይባቸውም የተሻሉ እንደሆኑ አመላክቷል።

ተስፋዬ መኮንን (2000 ዓ.ም) የሶስት ዓመት ፈተናዎችን በመውሰድ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን የይዘት ዝምድና በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ያጠና ሲሆን፣ የጥናቱ ውጤት እንደሚገልፀውም በሶስቱም አመታት ፈተናዎች ውስጥ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች አለመካተታቸው ተገቢነት የለውም በተጨማሪም የዕህፈት ክሂል የፈተና ይዘቶች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር የሚዛመዱ ሲሆን፣ በአንፃሩ ከፈተናዎቹ ይዘቶች ውስጥ ከመርሃ ትምህርቱ ዝርዝር ዓላማዎች እና ይዘቶች ጋር የማይዛመዱ እንዳሉ አመልክቷል።

ትንሳኤ ብርሃኔ (1988 ዓ.ም) ‹‹የአማርኛ የቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት (1980-1987 ዓ.ም) ›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ነው። ትንሳኤ በእነዚህ ስምንት ዓመታት የተሰጡ ብሔራዊ የአማርኛ ፈተናዎችን ተገቢ ወይም ጥሩ የመመዘኛ መሳሪያ መሆን አለመሆናቸውን መርምሯል። በዋናነት ዕኑእነትና አስተማማኝነት እንደ መመዘኛ በመውሰድ ያየ ሲሆን በውጤቱም ከዕኑእነት አንፃር አብዛኛዎቹ የቃላት ፈተናዎች መማሪያ መፅሐፍቱን መሠረት ያደረጉ አለመሆናቸውንና የአስተማማኝነት ደረጃቸውም ዝቅተኛ እንደሆነ በዚህም ከ269 ጥያቄዎች 55 የሚሆኑት አንድ ትክክለኛ መልስ እንደሌላቸው አመልክቷል። ከዚህ ሌላ አማርኛ የአፍመፍቻቸው የሆኑ ተማሪዎች ካልሆኑት ይልቅ በውጤት እንደተሻሉ አሳይቷል።

አገኘሁ ተስፋ (1990 ዓ.ም) ‹‹አማርኛን በማስተማር ሂደት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች የይዘትና የላህያዊ አግባብነትና የአጠያየቅ ዘዴዎች፣ በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች የ12ኛ ክፍል ሞዴል

ፈተናዎች›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያካሄዱት ጥናት ነው፡፡ አጥኚው የፈተናዎቹ የምንባቦችና የአጠያየቅ ዘዴዎች አመራረጥ በተለያዩ ተመራማሪዎች ከቀረቡ መርሆች፣ መመዘኛዎች አኳያ ገምግሞ በተገኘው መረጃ አሉታዊ ጎናቸው በዝቶ የተገኘ መሆኑን አመልክቷል፡፡ በተለይም የአጠያየቅ ዘዴዎች አመራረጥ ድክመት በጣም የጎላ፣ በተፈታኞቹ የፈተና ውጤትም ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሆኖ መገኘቱን ገልጿል፡፡

በለጠ ያዕቆብ (1995 ዓ.ም) ‹‹ ለ9ኛ ክፍል የሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ለደረጃው ከሚቀርበው ትምህርት ጋር ያላቸውን የይዘት አግባብነት እና የአጠያየቅ ብቃት›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተካሄደ ጥናት ሲሆን፣ የጥናቱ ውጤትም እንደሚያመለክተው ፈተናዎቹ ለደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር ያላቸውን የይዘት አግባብነት ዝቅተኛ መሆኑን እና ከመማሪያ መፅሐፍ ይዘት አኳያ ሲቃኙ ዝምድና እንዳላቸው አመልክቷል፡፡

ፀጋዬ ግርማ (1997 ዓ.ም) ‹‹ ከ1993 እስከ 1996 ዓ.ም ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል መምህራን ስልጠና የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ የሴሚስተር ማጠቃለያ ፈተናዎች ግምገማ›› በሚል ርዕስ የተካሄደ ጥናት ሲሆን በጥናቱም የተገኘው ውጤት በፈተናዎቹ ውስጥ ከቀረቡ 246 ጥያቄዎች 94.5% የሚሆኑት በስርዓተ ትምህርቱ ላይ ሲመሰረቱ 5.5% የሚሆኑት ግን ከስርዓተ ትምህርቱ ውጪ መሆናቸውን እና በርካታ ይዘቶች በፈተናው ውክልና ሳያገኙ መቅረታቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

ራሔል ወርቁ (2001 ዓ.ም ) ‹‹ከ1995 እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ በቀረቡት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መልቀቂያ ፈተናዎች የመድብለ ቃላት አፈታተን ላይ የሚያተኩር ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናቱም ዓላማ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መልቀቂያ ፈተናዎች ውስጥ ተካተው የቀረቡት የቃላት ፈተናዎች የቀረቡበትን የቃላት ፈተና አቀራረብ መንገድ መመርመር ነው፡፡ በጥናቱ ውጤትም የቃላት ፈተናዎቹ በ11 የቃላት ጥያቄ አቀራረብ መንገዶች ላይ በመመስረት የቀረቡ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

በመጨረሻም የምናየው የጥናት ሥራ ኤደን ብርሃኔ (2002 ዓ.ም) “ከ1995 እስከ 2001 ዓ.ም በቀረቡ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የቃላት አፈታተን ግምገማ›› በሚል ርዕስ የተጠና ሲሆን በጥናቱም የተገኘው ውጤት በቃላት ጥያቄዎች ውስጥ በአገልግሎት ላይ የዋሉት የፈተና ማቅረቢያ መንገዶች የተለያዩ መሆናቸውንና የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ፈተናዎች

የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ በተገቢው ሁኔታ የመመዘን ብቃት እንደሚጎድላቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው የጥናት ሥራዎች በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ቢያመሳስላቸውም ውስጣቸውን በምንመረምርበት ጊዜ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ ከጥናቶቹ መካከል የመጀመሪያዎቹ ሁለት ጥናቶች ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ናቸው፡፡ ዓላማቸውን ስንመለከት አምስቱ የጥናት ስራዎች ፈተናው ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለውን ዝምድና መመርመር ሲሆን ሦስቱ ፈተናዎች ደግሞ በቃላት አፈታተን ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ባጠቃላይ እነዚህ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ የተሰሩ ጥናቶች የፈተናዎቹን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ያሳዩ ሲሆን በግኝታቸውም በአብዛኛው የፈተናዎቹ ደካማ ጎን ጎልቶ እንደሚታይ አሳይተዋል፡፡

ቀደምት ጥናቶችን ይህን ያህል ካየን ይህ ጥናት ቀደም ብለው ከተሰሩ ጥናቶች የሚለይበትንና የሚመሳሰልበትን ቀጥለን እናያለን፡፡ ጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ ማተኮሩ ከሌሎች ጥናቶች ጋር ሲያመሳስለው ከዚህ ሌላ ፈተናዎቹ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለውን ዝምድና መመልከቱ ከአበበ (1975 ዓ.ም)፣ ከአገኘሁ (1990 ዓ.ም)፣ ከበለጠ(1995 ዓ.ም) ከፀጋዬ (1997 ዓ.ም) እና ከተስፋዬ (2000 ዓ.ም) የሚያመሳስለው ሲሆን አራቱ ጥናቶች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሶስቱ ደግሞ በብሔራዊ ፈተናዎች እንዲሁም አንዱ በኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጁ ፈተናዎች ላይ ያተኩራሉ፡፡ አጥኚዋ በክልል ደረጃ የተዘጋጁ የማጠቃለያ ፈተናዎች ላይ የተሰሩ ጥናቶች ያጋጠማት ባለመሆኑ ቀደም ብለው ከተሰሩት ጥናቶች እንደሚለይ ታምናለች፡፡ በሌላም በኩል ጥናቱ የሚያተኩረው በሰዋስው ጥያቄዎች ላይ ብቻ በመሆኑ ከአሁን በፊት ከተሰሩ ጥናቶች ልዩ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የሚከተለው ያሰራር ሂደት አይነታዊ የምርምር ዘዴን ሲሆን የትንተናው ሂደት የቀረበው በገላጭ ዘዴ ነው። ይህን የአጠናን ስልት ለዚህ ጥናት የተመረጠበት ዋና ምክንያት ገላጭ የጥናትና ምርምር ዘዴ በሰነዶች ላይ ተመስርቶ ከሚካሄደው የጥናት ሥራ ጋር በጣም ተስማሚ ሆኖ በመገኘቱና ነገሮችን በመግለፅና በመተንተን ላይ የማተኮር ባህሪይ ስላለው ነው።

Best and Khan (2002) እና Dornye (2007) እንደሚገልፁት ገላጭ የምርምር ዘዴ በአያሌ የጥናት መስኮች ዘንድ ዋና ተፈላጊ ምንጭ በመሆን የሚታወቁትን የሰነድ ፍተሻ፣ መዛግብትን፣ የህትመት ውጤቶችን፣ ደብዳቤዎችን፣ ግለታሪኮችን፣ የመስክ ማስታወሻዎችን፣ መጽሔቶችን፣ መጣጥፎችን፣ ፎቶዎችን፣ መርሃ ትምህርቶችን፣ ወዘተ. በመረጃ ምንጭነት አካቶ የያዘ በመሆኑና ጽሑፍ ላይ የተመሠረተ ጥናት ለማድረግ አመቺ ሁኔታን መፍጠር የሚችል ነው። የጥናቱ አቅራቢ ለዚህ በሰነዶች ላይ ተመስርቶ ለምታከናውነው የጥናት ጽሑፍ ገላጭ የምርምር ዘዴን ለመምረጥና ለመጠቀም የቻለችው በዚህ ምክንያት ነው።

## 3.2. የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች ለደረጃው ከቀረበው መርሃ ትምህርት ጋር ያላቸውን የይዘት ተገቢነትና የፈተና አዘገጃጀት መርህን የተከተሉ መሆናቸውን ለመመርመር የታለመ ነው። ዓላማውም እነዚህ ጥያቄዎች ለክፍል ደረጃው ከተዘጋጀው ይዘት ጋር ያላቸውን የይዘት ተገቢነት መፈተሽ ነው። ይህንንም ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተግባራዊ ሆነዋል። እነሱም 1. ከ1998-2003 ዓ.ም የቀረቡ ፈተናዎች

2. መርሃ ትምህርት

3. የክልሉ የፈተና ክፍል ተወካይ

ከዚህ በመቀጠል ስለ መረጃ ምንጮቹ በጥቂቱ እናያለን፡-

### 3.2.1. ፈተናዎች

የጥናቱ ዓላማ ፈተናዎችን መገምገም እንደመሆኑ የተመረጡት የስድስት ዓመት ፈተናዎች የጥናቱ አብይ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በኦሮሚያ ክልል ከ1998-2003 ዓ.ም አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ የስድስት ዓመት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች በዋናነት በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡

### 3.2.2. መርሃ ትምህርት

የመርሃ ትምህርት ይዘት የችሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት መሠረት እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል፡፡ ከዚህ አኳያ የፈተናዎቹን የይዘት ተገቢነት ለመመርመር የመርሃ ትምህርቱን ይዘቶች ማየት ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም መርሃ ትምህርቶቹ ልክ እንደፈተናዎቹ ሁሉ አብይ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል፡፡ ፈተናው የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ማጠቃለያ ፈተና በመሆኑ በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉት መርሃ ትምህርቶች ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ያሉት ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት በ1997 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ የተዘጋጀው አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መርሃ ትምህርቶች ከ5ኛ- 8ኛ ክፍሎች ያሉ አራት መርሃ ትምህርቶች በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡

### 3.2.3. በክልሉ የፈተና ዝግጅት ክፍል ተወካይ

በዚህ ጥናት ሌላው በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ፈተና ዝግጅት ክፍል ተወካይ በቃለ መጠይቅ ስለሚሳተፉ የዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ ምንጭ ናቸው፡፡

## 3.3. የናሙና አመራረጥ

### 3.3.1. የፈተናዎች አመራረጥ

ቀደም ሲል በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው የጥናቱ ዓላማ ከ1998-2003 ዓ.ም ድረስ በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች ለደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር ያላቸውን የይዘት ተገቢነት መመርመር በመሆኑ ለጥናቱ ወካይ የሚሆኑ ፈተናዎችን መምረጥ የግድ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ክልሉ ፈተናዎችን ማዘጋጀት የጀመረው በ1992 ዓ.ም ሲሆን ከ1998-2003 ዓ.ም ድረስ ያሉት

ፈተናዎች ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል፡፡ እነዚህ ፈተናዎች የተመረጡበት ዋና ዋና ምክንያቶች፡-

1ኛ. ከ1998 ዓ.ም በፊት የነበረው መርሃ ትምህርት አሮጌ በመሆኑና በአዲስ መርሃ ትምህርት የተተካ በመሆኑ አገልግሎት ላይ በሌለ መርሃ ትምህርት ላይ ተመስርቶ ጥናት ማድረጉ ፋይዳው ዝቅተኛ መሆኑ በመታመኑና ፤

2ኛ. በቅርብ ዓመታት ፈተናዎች ላይ ማተኮሩ መረጃዎችን ለማግኘትና ወቅታዊ በሆኑ መረጃዎች ተመስርቶ በተጨባጭ ለማሳየት አመቺ በመሆኑ እነዚህ ፈተናዎች ተመርጠዋል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ከ1998 - 2003 ዓ.ም የተሰጡ የስድስት ዓመት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን በናሙናነት በማካተት ጥናቱ ተከናውኗል፡፡

### 3.3.2 የክልልና የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የኦሮሚያ ክልል የተመረጠው በአመቺ የናሙና ዘዴ ነው፡፡ አመቺ የናሙና ዘዴን የተጠቀመበት ምክንያት አንደኛ፣ በሁሉም ክልሎች የተዘጋጁ ፈተናዎችን ለማጥናት ከጊዜ እና ከወጪ አንፃር የማያመች መሆኑ፤ ሁለተኛው፣ በክልሉ ለተወሰኑ አመታት በመምህርነት ስታገለግል በክልሉ እየተዘጋጁ የሚቀርቡ ፈተናዎችን የማየት እድል ገጥሟት ስለነበር እና ክልሉ ለአጥኚዋ ካለው ቅርበት የተነሳ ሊመረጥ ችሏል፡፡ በሌላ በኩል የስምንተኛ ክፍል የተመረጠው በክልሉ እየተዘጋጀ የሚቀርበው ፈተና ለዚህ የክፍል ደረጃ ብቻ በመሆኑ የዓላማ ተኮር ናሙና ዘዴን በመጠቀም ሊመረጥ ችሏል፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት ተገቢ መረጃ ያስገኛሉ ተብለው በተግባር ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሰነድ ፍተሻ እና ቃለመጠይቅ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው የሰነድ ፍተሻ ሲሆን በአጋዥነት ቃለ መጠይቅን ተጠቅሟል፡፡ ስለ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ አጠቃቀም እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞከራል፡፡

### 3.4.1. የሰነድ ፍተሻ

የሰነድ ፍተሻ አንድን ጥናት በማካሄድ ሂደት ውስጥ መረጃን ለማሰባሰብ ከሚያግዙ ዘዴዎች አንዱ ነው። እንደ ያለው (1998) ገለጻ ሰነዶች ተመራማሪው ስላለፈም ይሁን ስለወቅታዊ ጉዳይ መረጃ ለመሰብሰብ ሲነሳ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ጠቃሚ ነገሮች ናቸው። በመሆኑም የዚህ የጥናት ዓላማ ፈተናዎችን መገምገም እንደመሆኑ መጠን ለጥናቱ በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉት ሰነዶች ናቸው። እነዚህ ሰነዶች ከ1998-2003ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች እና ከ5ኛ -8ኛ ክፍሎች ያሉ መርሃ ትምህርቶች ናቸው። ስለዚህ በዚህ ጥናት ውስጥ አብይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ የሚሆነው የሰነድ ፍተሻ ነው። በሰነድ ፍተሻው ከ1998-2003ዓ.ም ተዘጋጅተው በቀረቡት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን የይዘት ተገቢነት እና ጥያቄዎቹ ተገቢ የአዘገጃጀት መርህን ተከትለው መዘጋጀት አለመዘጋጀታቸውን ለመመርመር ጥረት ተደርጓል።

### 3.4.2. ቃለ-መጠይቅ

ቃለ-መጠይቅ በአብዛኛው ውስን ለሆኑ ተጠያቂዎች ሊቀርብ የሚችልና ምርምሩ የሚካሄድበትን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ ጥልቅ እና የተብራራ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ጠቃሚ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው (ያለው፣ 1998)። በዚህ ጥናትም ለጥናቱ አጋዥ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አምስት ጥያቄዎችን የያዘ ቃለ-መጠይቅ ተዘጋጅቶ በትምህርት ቢሮ ለፈተና ዝግጅት ክፍል ተወካይ ቀርቧል። የቀረበው ቃለ-መጠይቅ በዋናነት ለሚነሱ ሃሳቦች ደጋፊ መረጃዎችን እንዲሰጥ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ቃለ መጠይቁ በክልሉ ስለፈተና ዝግጅት ያላቸውን አጠቃላይ ግንዛቤ ለማወቅ ክፍትና በከፊል ዝግ የሆኑ ጥያቄዎችን በማንሳት ሰፋ ያሉ ሃሳቦችን ለማሰባሰብ ተችሏል። ቃለ-መጠይቁ በአጥኚዋ ከተዘጋጀ በኋላ ለአማካሪ ቀርቦ አስተያየት ተሰጥቶበት ለመጨረሻ ጊዜ ተሻሽሎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

ተሻሽሎ የቀረበውን መጠይቅ ለዝርዝሩ አባሪ 2 ይመልከቱ። በመጠይቁ ፈተና ዝግጅቱን በተመለከተ አምስት ነጥቦችን በማንሳት በፈተና ዝግጅት ወቅት ተግባራዊ ይደረጉ እንደሆነ ለማወቅ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል።

### 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት በሰነድ ፍተሻና በቃለ መጠይቅ መረጃዎችን ከሰበሰበ በኋላ የተገኙትን መረጃዎች ገላጭ ስልትን በመከተል ከክለሳ ድርሳኑ ውስጥ በሠፈሩት ትውረቶች መሠረት ትንተናው ተካሂዷል፡፡ አጥኚዋ ገላጭ የትንተና ዘዴን የተጠቀመችበት ዋና ምክንያት የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ባህሪይ ነው፡፡ እንደ Domye (2007) ገለፃ ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች በአብዛኛው የሚተነተኑት በቃላት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ ገላጭ ዘዴን ተጠቅሞ ተንትኗል፡፡ በተጨማሪም በመርሃ ትምህርቱ እና በፈተናዎቹ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ብዛት ወይም ሽፋን በቁጥር እና በመቶኛ በማስቀመጥ ያላቸው ተመጣጣኝነት እንዲተነተን ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ አቀራረብ፣ አተናተንና አተረጓጎም

ምዕራፍ አንድ ሥር እንደተገለጸው የዚህ ጥናት አብይ ዓላማ በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎችን መገምገም ነው፡፡

የዚህ ምዕራፍ ትኩረት ደግሞ የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ የተገኘውን ውጤት እየተነተነ ከነማብራሪያው ማቅረብ ነው፡፡ ለአተናተን ይመች ዘንድም ምዕራፉን በሁለት ንዑሳን ክፍሎች ለመክፈል ተሞክሯል፡፡

የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል የይዘት ተገቢነት እንደ አንድ መመዘኛ መስፈርት በመውሰድ ፈተናዎችን ለመገምገም ይሞክራል፤ በግምገማው ሂደት አስፈላጊ በሆነ ቦታ ከመርሃ ትምህርቱ እና ከፈተናዎቹ የተገኙ መረጃዎች እየገቡ ትንተናውን ያግዛሉ፡፡

በሁለተኛ ንዑስ ክፍል የጥያቄዎችን አዘገጃጀት በተመለከተ ፈተናዎች ተገቢ በሆነ መርህ መዘጋጀታቸውን ከባለ ብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች መስፈርት አንጻር ለመተንተን ይሞከራል፡፡ በዚህም ክፍል ከፈተናዎቹ የተገኙ መረጃዎች እንዳስፈላጊነቱ እየገቡ ትንተናው ይካሄዳል፡፡

### 4.1 የፈተናው ተገቢነት /Validity/

በተዛማጅ ፅሑፍ ውስጥ ለመግለፅ እንደተሞከረው አንድ ፈተና ተገቢ ነው የሚባለው መመዘን ያለበትን እውቀት በትክክል መመዘን ሲችል ነው፡፡ ፈተናው ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ደግሞ ሁሉንም የተገቢነት ዓይነቶች ማየት አስፈላጊ ቢሆንም ይህ ጥናት የሚያተኩረው በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ላይ በመሆኑ የፈተናዎቹን ተገቢነት ለማረጋገጥ የይዘት ተገቢነትን ብቻ መመልከቱ በቂ እንደሆነ ፀጋዬ (1997 ዓ.ም) Sax (1974)ን ጠቅሶ ይገልጻል፡፡ በዚህ መሠረትም ጥናቱ የይዘት ተገቢነት ላይ በማተኮር ትንተናው እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

## የይዘት ተገቢነት

አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት እንዲኖረው ሁለት ነገሮችን በዋናነት ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡ የመጀመሪያው ፈተናው በመርሃ ትምህርቱ ይዘቶች ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት ሲኖርበት በሁለተኛ ደረጃ በመርሃ ትምህርቱ ይዘቶች ላይ መመስረት ብቻ ሳይሆን ይዘቶቹን እንደየትኩረት ደረጃቸው መወከል ይገባዋል፡፡ ከዚህ መሠረተ ሀሳብ በመነሳት የፈተናዎቹን የይዘት ተገቢነት ለመመርመር ተሞክሯል፡፡

በይዘት ተገቢነት ግምገማ የትምህርቱ ይዘቶች ተመጣጣኝ በሆነ መልክ በፈተናው ውስጥ መወከላቸውንና በፈተናው ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች ከመርሃ ትምህርቱ ውጪ ያልወጡ መሆናቸውን ለመገምገም በመርሃ ትምህርቱ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ያገኙትን ውክልና ማመሳከር ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም የፈተናዎቹን የይዘት ተገቢነት ለመመርመር የትምህርቱን ይዘቶች የሚያሳየውንና ለእያንዳንዱ ይዘት ምን ያህል ጊዜ እንደተመደበ በግልጽ የሚያሳየውን መርሃ ትምህርት በመጠቀም ትንተናው ተካሂዷል፡፡

ፈተናው የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ማጠናቀቂያ በመሆኑ መሠረት የሚያደርገው መርሃ ትምህርት ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉ መርሃ ትምህርቶችን ነው፡፡ ይህንንም በቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በእነዚህ መርሃ ትምህርቶች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ምን ያህል ለደረጃው ተዘጋጅቶ በሚቀርቡት ፈተናዎች ውስጥ እንደተንፀባረቁ ለማየት ስለሚሞከር በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ይዘቶች ለደረጃው ተዘጋጅተው ከቀረቡት የሰዋስው ፈተናዎች ይዘቶች ጋር ማነፃፀር ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህንን ለማድረግ በቅድሚያ የሰዋስው ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ያገኙትን ቦታ ማየት ይገባል፡፡ በመሆኑም ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ባሉ መርሃ ትምህርቶች ውስጥ በሰዋስው የትምህርት ክፍል ስር የቀረቡት ይዘቶች በቃላት ውስጥ የድምፅ መጥበቅና መላላት፣ የቃላት ምስረታና እርባታ፣ የቃላት ፍቺ፣ የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት፣ ገላጮች፣ ሐረግ እና ዐረፍተነገር ሲሆኑ እነዚህ ይዘቶች ለደረጃው በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ያገኙትን ትኩረትና የክፍለ ጊዜ መጠን ማየት ተገቢ በመሆኑ ይህም በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ አንድ፡- ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ መርሃ ትምህርቶች ውስጥ የተነደፉት የሰዋስው ይዘቶችና የተመደባለቸው ክፍለ ጊዜ ብዛት በመቶኛ፡

| ተ.ቁ | ይዘት | 5ኛ ክፍል | | 6ኛ ክፍል | | 7ኛ ክፍል | | 8ኛ ክፍል | | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የክፍለ ጊዜ ብዛት | % | የክፍለ ጊዜ ብዛት | % | የክፍለ ጊዜ ብዛት | % | የክፍለ ጊዜ ብዛት | % | | |
| 1 | የቃላት ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት | 3 | 10 | 3 | 9.7 | 4 | 11.1 | 3 | 11.1 | 13 | 10.6 |
| 2 | ቃላትን መመስረትና ማርባት | 10 | 35 | 9 | 29 | 8 | 22.2 | 8 | 29.6 | 35 | 28.4 |
| 3 | የቃላት ፍቺ | 6 | 21 | 7 | 22.6 | 6 | 16.7 | 7 | 26 | 26 | 21.1 |
| 4 | የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት | 3 | 10 | 3 | 9.7 | - | - | - | - | 6 | 4.9 |
| 5 | የግስና የስም ገላጭ | 3 | 10 | 4 | 12.9 | 4 | 11.1 | 3 | 11.1 | 14 | 11.4 |
| 6 | ቃልና ሐረግ | 4 | 14 | 5 | 16.1 | 6 | 16.7 | - | - | 15 | 12.2 |
| 7 | ዐ.ነገር | - | | - | | 8 | 22.2 | 6 | 22.2 | 14 | 11.4 |
| | **ድምር** | **29** | **100** | **31** | **100** | **36** | **100** | **27** | **100** | **123** | **100** |

በሠንጠረዡ ከቀረበው ዝርዝር መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ይዘቶቹ የተሰጣቸውን ትኩረት ከተሰጣቸው የክፍለ ጊዜ ብዛት መገንዘብ ይቻላል። በዚህ መሠረት የሰዋስው ይዘቶቹ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ከተሰጣቸው ክፍለ ጊዜ አንጻር ከ1ኛ እስከ 7ኛ "የቃላት እርባታና ምስረታ" 35 ክፍለ ጊዜ፣"የቃላት ፍቺ" 26 ክፍለ ጊዜ፣ "ቃልና ሐረግ" 15 ክፍለ ጊዜ፣ "የግስና የስም ገላጭ" 14 ክፍለ ጊዜ፣ "ዐ.ነገር" 14 ክፍለ ጊዜ፣ "በቃላት ውስጥ የድምፅ መጥበቅና መላላት" 13 ክፍለ ጊዜ እንዲሁም "የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት" 6 ክፍለ ጊዜ በቅደም ተከተል ይዘዋል። የሰዋስው ይዘቶቹ አጠቃላይ ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል 123 ክፍለ ጊዜ ይዘዋል። ይህም አጠቃላይ ለቋንቋው ከተመደበው 544 ክፍለ ጊዜ 22.6 % የሚሆነው ነው። እነዚህ የሰዋስው ይዘቶች ያላቸውን የትኩረት ደረጃ ለማወቅ ለይዘቱ ምን ያህል ክፍለ ጊዜ ተመድቧል የሚለውን በማየት ትንተናው ተካሂዷል።

እነዚህ የሰዋስው ይዘቶች በውስጣቸው የተለያዩ ንዑስ ይዘቶችን አቅፈዋል ንዑስ ይዘቶቹን ማወቅ በተዘጋጁት የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡትን እና ያልቀረቡትን የሰዋስው ይዘቶች በመለየት የፈተናዎቹን የይዘት ተገቢነት ለመመርመር ስለሚያመች እዚህ ላይ ማንሳቱ ተገቢ ነው። በመሆኑም አንዳንድ የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ የተነደፉትን ንዑስ ይዘቶች መመልከቱ ለምርመራው መቀላጠፍ ስለሚያመች እንደሚከተለው ቀርቧል።

4. የቃላት እርባታና ምስረታ
   - 4.1. ከሆሄያት ቃላት መመስረት
   - 4.2. ከአንድ ቃል ሌሎች ቃላትን መመስረት
   - 4.3. በቅጥያዎች ቃላትን ማርባት
   - 4.4. በቅጥያዎች ቃላትን መመስረት
   - 4.5. ጥምር ቃላትን መመስረት
   - 4.6. ምህፃረ ቃላትን መመስረት

ከነዚህ ንዑስ ይዘቶች መካከል ጥምር ቃልን በ5ኛ እና በ6ኛ ክፍል መርሃ ትምህርቶች ውስጥ ድርብ ቃል ተብለው የቀረቡ ሲሆን በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍል መርሃ ትምህርቶች ውስጥ ደግሞ ጥምር ቃል ተብለው ቀርበዋል። በዚህ ጥናት ውስጥም ጥምር ቃል ተብሎ ቀርቧል። ምክንያቱም ቃላቱ የተገኙት በመደረብ ሳይሆን በመጣመር በመሆኑ ነው (ባዬ፣ 2000፤ ጌታሁን፣ 1990)።

5. የቃላት ፍቺ

5.1. የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ

5.2. የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ

5.3. የቃላት ተቃራኒ ፍቺ

5.4. የቃላት አወዳዊ ፍቺ እና

5.5. የቃላት እማሪያዊና ፋካሪያዊ ፍቺ ናቸው፡፡

6. ገላጮች

6.1. የስም ገላጭ

6.2. የግስ ገላጭ

እነዚህ ከላይ ያየናቸው የሰዋስው ይዘቶች በውስጣቸው ንዑስ ይዘቶችን የያዙ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህንና ሌሎቹንም የሰዋስው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ያላቸውን የይዘት ተገቢነት እንዲሁም ይዘቶቹ በፈተናው ውስጥ የሚያገኙትን ውክልና ከተሰጣቸው የክፍለ ጊዜ መጠን አንፃር ተመርምሯል፡፡

በአጠቃላይ መርሃ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ይዘቶች ለይቶ ለደረጃው ተዘጋጅተው ከቀረቡት ፈተናዎች ጋር ምን ያህል እንደሚዛመዱ መመርመር የፈተናዎችን የይዘት ተገቢነት በቀላሉ ለማወቅ ይረዳል (Alderson and et al፣ 1995)፡፡ ይህ ጥናትም የፈተናዎችን የይዘት ተገቢነት ለመመርመር ይህንኑ አካሄድ ተጠቅሟል፡፡ የሰዋስው ይዘቶች በመርሃ ትምህርት ውስጥ ያገኙትን ትኩረትና የክፍለ ጊዜ መጠን ካየን በመቀጠል የሰዋስው ይዘቶች በእያንዳንዱ ዓመተ ምህረት ፈተናዎች ውስጥ ያገኙትን ውክልና እና የሰዋስው ጥያቄዎቹ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን የይዘት ተገቢነት እንመረምራለን፡፡ በዚህ መሠረት እያንዳንዱ ፈተና በተናጠል በሠንጠረዥ በማደራጀት ትንተናው ተካሂዷል ይህም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የሰዋስው ይዘቶች በ1998 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና

| ተ.ቁ | ይዘቶች | ጥያቄዎቹ በፈተናው ውስጥ የሚገኙበት ተራ ቁጥር | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በቃላት ውስጥ የድምጽ መጠበቅና መላላት | 31፣35፣36 | 3 | 9.4 |
| 2 | ቃላትን መመስረትና ማርባት | 32፣34፣37፣40 | 4 | 12.5 |
| 3 | የቃላት ፍቺ | 1፣2፣3፣4፣5፣6፣7፣8፣9፣10፣ 11፣12፣13፣14፣15፣26፣27፣ 28፣29፣45 | 20 | 62.5 |
| 4 | የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት | - | - | - |
| 5 | የግስና የስም ገላጭ | 33፣38 | 2 | 6.2 |
| 6 | ቃልና ሐረግ | - | - | - |
| 7 | ዐ.ነገር | 39፣42፣43 | 3 | 9.4 |
| ከመርሃ ትምህርቱ ውጭ የሆኑ ጥያቄዎች | | - | - | - |
| ድምር | | | 32 | **100** |

በሠንጠረዥ ሁለት ከቀረበው መረጃ መረዳት የሚቻለው በ1998 ዓ.ም ፈተና ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች 32 ሲሆኑ ሁሉም ጥያቄዎች ለደረጃው የተዘጋጀውን መርሃ ትምህርት መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ነገር ግን የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባው ጉዳይ አንዳንድ የሰዋስው ይዘቶች በፈተናዎቹ ውስጥ አልተካተቱም፤ ከእነዚህም ውስጥ "የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት" እና "ቃል እና ሐረግ መለየት" የሚሉት ሁለት የሰዋስው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ አልተካተቱም፡፡ በሌላ አገላለጽ ከሰባት የሰዋስው ይዘቶች ሁለቱ በፈተናው ውስጥ ውክልና የላቸውም፤ ይህም በመቶኛ 71.4% የሚሆኑት የሰዋስው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ውክልና ሲያገኙ 28.6% የሚሆኑት የሰዋስው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ውክልና አለማግኘታቸውን ያሳያል፡፡ እንዲህ ያለ ችግር ያለበት ፈተና ሙሉ ለሙሉ የይዘት ተገቢነት አለው ለማለት አያስደፍርም፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ የሚታየው ችግር ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ያለመካተት ብቻ ሳይሆን የተካተቱትም ይዘቶች ቢሆኑ እንደየትኩረት ደረጃቸው ወካይ ጥያቄዎችን ያለማግኘት ሁኔታም ይታያል፡፡ ይህን በዝርዝር ስንመለከት

በ1998 ዓ.ም የቀረበውን አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ፈተና ስንመረምር 13 ክፍለ ጊዜ የተሰጠው "በቃላት ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት" የሚለው የሰዋስው ይዘት በ3 ጥያቄዎች ሲወከል "ቃላትን ማርባትና መመስረት" 35 ክፍለ ጊዜ ይዞ በ4 ጥያቄዎች ብቻ ተወክሏል:: እንደዚሁም 26 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት ፍቺ" በ20 ጥያቄዎች ሲወከል፤14 ክፍለ ጊዜ ያለው "ዐረፍተ ነገር" ደግሞ በ3 ጥያቄዎች ተወክሏል። ስለዚህ በፈተናው ውስጥ ውክልና ያላቸውን ይዘቶች ስንመለከት የተወከሉበት የጥያቄ መጠን ተመጣጣኝ አይደለም። ለምሳሌ፡- "የቃላት ፍቺ" 26 ክፍለ ጊዜ ይዞ በ20 ጥያቄዎች መወከሉና "ቃላትን ማርባትና መመስረት" 35 ክፍለ ጊዜ ይዞ በ4 ጥያቄዎች ብቻ መወከሉ ከይዘት ተገቢነት አንፃር ተገቢነት የለውም ።

ምክንያቱም በምዕራፍ ሁለት እንዳየነው አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው የሚባለው ጥያቄዎቹ በመርሃ ትምህርቱ ይዘት ላይ መመስረት ብቻ ሳይሆን ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው ውክልና ሲያገኙ ነው። ይህ ፈተና ደግሞ ይህንን አሟልቶ አልተገኘም። እንደ Madsen (1983) እና Bachman (1990) ገለፃ ናሙናዎችን ስንመርጥ በመርሃ ትምህርቱ ለክሂሎችና ለእውቀት ዘርፎች የተሰጠውን ትኩረት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል። በሌላ አባባል ፈተናዎቹ መዘጋጀት ያለባቸው ተማሪዎች በክፍል ደረጃው በተማሯቸው ይዘቶች ላይ ተገቢና ሚዛናዊ ትኩረት በሚሰጥ መልኩ መሆን ይኖርበታል። ነገር ግን ይህን የማጠቃለያ ፈተና ከዚህ አኳያ ስንመረምረው ለሁሉም የሰዋስው ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው ተመጣጣኝ ናሙና አላቀረበም።

በመርሃ ትምህርቱ ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት የተነደፈው የሰዋስው ይዘት በአራት ጥያቄዎች ብቻ ተወክሏል። ይህ ደግሞ ተማሪዎች በደረጃው የተማሩትን ወይም ይማሩታል ተብሎ የሚጠበቀውን እውቀት በአጥጋቢ ሁኔታ ለመመዘን በቂ ነው ተብሎ አይታሰብም። ስለሆነም ይህ የማጠቃለያ ፈተና የይዘት ተገቢነቱ ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋግጧል።

በአጠቃላይ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የቀረበው የ1998 ዓ.ም የማጠቃለያ ፈተና ውስጥ የተጠየቁት የሰዋስው ጥያቄዎች ከመርሃ ትምህርቱ መውጣታቸው ጥሩ ቢሆንም ለይዘቶች የተሰጠው ትኩረት ግን አናሳ ነው። ይህም ማለት ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው ወካይ የሰዋስው ናሙና ጥያቄዎችን አላካተቱም። ስለሆነም ከጠንካራ ጎኑ ይልቅ ደካማ ጎኑ ያመዘነ ነው።

ሠንጠረዥ ሦስት፦ የሰዋስው ይዘቶች በ1999 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና

| ተ.ቁ | ይዘቶች | ጥያቄዎቹ በፈተናው ውስጥ የሚገኙበት ተራ ቁጥር | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በቃላት ውስጥ የድምጽ መጠበቅና መላላት | - | - | - |
| 2 | ቃላትን መመስረትና ማርባት | 47,48 | 2 | 10.5 |
| 3 | የቃላት ፍቺ | 1፣2፣3፣4፣5፣6፣7፣8፣9፣10፣ 11፣12፣13፣14፣15፣ 53፣54 | 17 | 79 |
| 4 | የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት | - | - | - |
| 5 | የግስና የስም ገላጭ | - | - | - |
| 6 | ቃልና ሐረግ | - | - | - |
| 7 | ዐ.ነገር | 45፣46 | 2 | 10.5 |
| ከመርሃ ትምህርቱ ውጭ የሆኑ ጥያቄዎች | | | | |
| | | ድምር | 21 | 100 |

በሠንጠረዥ ሦስት ከቀረበው መረጃ የምንረዳው በ1999 ዓ.ም በቀረበው አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ፈተና ውስጥ 21 የሰዋስው ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ ከ7 የሰዋስው ይዘቶች 3 ያህሉ በፈተና ውስጥ ውክልና ሲያገኙ የተቀሩት 4 የሰዋስው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ውክልና አላገኙም፡፡ እነዚህም "በቃላት ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት"፣ "የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት"፣ "የግስና የስም ገላጮች" እና "ቃልና ሐረግን መለየት" የሚሉት ተገቢ ውክልና ያላገኙ ናቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ ከሠባት ይዘቶች ውስጥ 42.5% ያህሉ በፈተናው ውስጥ ውክልና ሲያገኙ 57.5% ያህሉ ውክልና የላቸውም፤ ይህም የሚያሳየው አብዛኛው ይዘት በፈተናው አለመካተቱን ነው፡፡ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪዎች ለረጅም ጊዜ ሲማሩት የቆዩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡት ለመገምገም የሚዘጋጁ በመሆናቸው ይዘቶች በፈተና ውስጥ ሳይካተቱ መቅረት ፈተናው ለተነሳበት አላማ ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለመስጠት ያስችላል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ የታየውም ችግር ይኸው ነው፡፡

በዚህ ፈተና አብዛኛው የሰዋስው ይዘት አለመካተት ችግር በተጨማሪ በፈተናው የተካተቱትም ይዘቶች ቢሆኑ እንደየትኩረት ደረጃቸው ወካይ ናሙና አላገኙም፡፡ ለምሳሌ "የቃላት ፍቺ" 26 ክፍለ ጊዜ ይዞ በ17 ጥያቄዎች ሲወከል 35 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት ዕርባታና ምስረታ" በ2 ጥያቄዎች ብቻ ተወክሏል፡፡ ይህም ከይዘት ተገቢነት አንፃር ስናየው ተመጣጣኝ አይደለም፡፡

ምክንያቱም በመርሃ ትምህርቱ ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት የተነደፈው "የቃላት እርባታና ምስረታ" በመሆኑ ይህ ይዘት ከሌሎች ይዘቶች በተሻለ ወካይ ናሙና ሊኖረው ይገባ ነበር፡፡ እንደ Bachman (1990) ገለፃ በፈተና ውስጥ ይዘቶች ናሙና እንዲኖራቸው ለይዘቱ የተሰጠውን ትኩረት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል፡፡ ይህ የማጠቃለያ ፈተና ይህንን ከግምት ያስገባ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም አንድ ይዘት በክፍል ደረጃው ሰፊ ጊዜ አግኝቶ ከሆነ አናሳ ጊዜ ካገኘው ይዘት በበለጠ ናሙናዎችን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ፈተና የታየው ግን ይህ አይደለም፤ ለቃላት እርባታና ምስረታ ከተሰጠው ከፍተኛ ክፍለ ጊዜ አንፃር ከሌሎች ይዘቶች በተሻለ መልኩ ናሙና ማግኘት ሲገባው በአንድ ጥያቄ ብቻ መወከሉ አግባብነት የለውም፡፡

በአጠቃላይ በ1999 ዓ.ም አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅቶ በቀረበው ፈተና ውስጥ 21 የሰዋስው ጥያቄዎች ሲቀርቡ ሁሉም ጥያቄዎች በመርሃ ትምህርቱ የተነደፉ ይዘቶችን መሠረት ያደረጉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ከቀረቡት ጥያቄዎች ሁሉም በመርሃ ትምህርቱ ይዘት ላይ መመስረቱ ጥሩ የሚያስብለው ቢሆንም በፈተና ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው ውክልና ያለማግኘትና ፈተናው ሁሉንም ይዘቶች አለማካተቱ የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ስለሚቀንሰው በዚህ ረገድ ጉድለት ታይቶበታል፡፡ ስለሆነም ይህ የማጠቃለያ ፈተና ተማሪዎች ይማሩታል ተብሎ በመርሃ ትምህርቱ የተነደፉት የሰዋስው ይዘቶች አብዛኛው አለመካተታቸው የፈተናውን የመመዘን አቅምና የይዘት ተገቢነት አነስተኛ አድርጎታል፡፡ በዚህ መሠረት 1999 ዓ.ም የተዘጋጀው ፈተና ውስጥ የሰዋስው ይዘትን ለመገምገም የቀረቡት ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት የላቸውም ለማለት ያስደፍራል፡፡

ሠንጠረዥ አራት፡- የሰዋስው ይዘቶች በ2000 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና

| ተ.ቁ | ይዘቶች | ጥያቄዎቹ በፈተናው ውስጥ የሚገኙበት ተራ ቁጥር | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በቃላት ውስጥ የድምጽ መጠበቅና መላላት | 31፣32፣39 | 3 | 11 |
| 2 | ቃላትን መመስረትና ማርባት | 33፣34፣41 | 3 | 11 |
| 3 | የቃላት ፍቺ | 1፣2፣3፣4፣5፣6፣7፣8፣9፣10፣ 11፣12፣13፣14፣15፣ 55፣59 | 17 | 63 |
| 4 | የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት | - | - | - |
| 5 | የግስና የስም ገላጭ | 40 | 1 | 4 |
| 6 | ቃልና ሐረግ | - | - | - |
| 7 | ዐ.ነገር | 35፣36፣56 | 3 | 11 |
| ከመርሃ ትምህርቱ ውጭ የሆኑ ጥያቄዎች | | - | - | - |
| ድምር | | | 27 | 100 |

በሠንጠረዥ አራት ከቀረበው ዝርዝር መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በ2000 ዓ.ም በተዘጋጀው አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ፈተና አብዛኛዎቹ የሰዋስው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ በተወሰነ መልኩ ውክልና አግኝተዋል፡፡ 2000 ዓ.ም በቀረበው የማጠቃለያ ፈተና ውስጥ ከሁለት ይዘቶች በስተቀር አምስቱ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ መካተታቸውን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን በፈተናው ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች የአወካከል ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ይዘቶቹ የተወከሉበትን የጥያቄ መጠን ስንመለከት 13 ክፍለ ጊዜ ያለው "በቃላት ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት" በ3 ጥያቄዎች፣ 35 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት እርባታና ምስረታ" በ3 ጥያቄዎች፣ 26 ክፍለ ጊዜ ያለው የቃላት ፍቺ በ17 ጥያቄዎች ሲወከሉ 14 ክፍለ ጊዜ ያለው "የግስና የስም ገላጭ" የተወከለው በ1 ጥያቄ ብቻ ነው፡፡ ከእነዚህ የጥያቄዎች ስርጭት መረዳት የሚቻለው በፈተናው ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው ውክልና አለማግኘታቸውን ነው፡፡ ለምሳሌ 35 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት ምስረታና ዕርባታ" ከያዘው ከፍተኛ ክፍለ ጊዜ አንፃር ከሌሎች በተሻለ የጥያቄ መጠን መወከል ሲገባው 14 ክፍለ ጊዜ ከተሰጠው "ዐረፍተነገር" እና 13 ክፍለ ጊዜ ካለው "በቃላት ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት" እኩል በ3 ጥያቄዎች ተወክሏል፡፡ በሌላ በኩል 26 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት ፍቺ" ከሌሎቹ በበለጠ የጥያቄ መጠን በመወከል

ቀዳሚ ነው። እንደ የቋንቋ ፈተና ምሁራን ገለፃ ግን ከሌሎች በተሻለ የጥያቄ መጠን መወከል የነበረበት 35 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት ምስረታና ዕርባታ" ነበር፤ ነገር ግን ይህ ሆኖ አልተገኘም። በአጠቃላይ በ2000 ዓ.ም የተዘጋጀው ፈተና ይዘቶቹ ከመርሃ ትምህርቱ ውጭ ያለመሆን ጠንካራ ጎን ሲኖረው ይዘቶቹ እንደየትኩረት ደረጃቸው በተመጣጣኝ ጥያቄዎች ያለመወከል ደካማ ጎን ተስተውሎበታል። ስለሆነም ፈተናው ተማሪዎች ለረጅም ጊዜ ሲማሩት የቆዩትን ትምህርት በአግባቡ ይመዝናል ተብሎ አይታሰብም።

**ሠንጠረዥ አምስት: የሰዋስው ይዘቶች በ2001 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና**

| ተ.ቁ | ይዘቶች | ጥያቄዎቹ በፈተናው ውስጥ የሚገኙበት ተራ ቁጥር | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በቃላት ውስጥ የድምጽ መጠበቅና መላላት | 31፣32፣38 | 3 | 12 |
| 2 | ቃላትን መመስረትና ማርባት | 33፣34፣35፣37 | 4 | 15 |
| 3 | የቃላት ፍቺ | 1፣2፣3፣4፣5፣6፣7፣8፣9፣10፣ 11፣12፣13፣14፣15፣ 52፣56 | 17 | 65 |
| 4 | የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት | - | - | - |
| 5 | የግስና የስም ገላጭ | - | - | - |
| 6 | ቃልና ሐረግ | - | - | - |
| 7 | ዐ.ነገር | 36፣41 | 2 | 8 |
| ከመርሃ ትምህርቱ ውጭ የሆኑ ጥያቄዎች | | - | - | - |
| ድምር | | | 26 | 100 |

በሠንጠረዥ አምስት ከቀረበው ዝርዝር መረጃ መረዳት የሚቻለው በ2001 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበው አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ፈተና ውስጥ በመርሃ ትምህርቱ ከቀረቡት ሰባት የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ ሶስት ይዘቶች በፈተናው ውስጥ አለመካተታቸውን ነው። እነሱም "የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት"፣ "የግስና የስም ገላጭ" እና "ቃልና ሐረግን መለየት" የሚሉት የሰዋስው ይዘቶች ናቸው። እነዚህ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ አይካተቱ እንጂ በፈተናው ውስጥ የተካተቱት 26 ጥያቄዎች ሁሉም ከመርሃ ትምህርቱ የሰዋስው ይዘቶች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። በሌላ አገላለጽ ሁሉም ጥያቄዎች መሠረት የሚያደርጉት መርሃ ትምህርቱን ነው። በመሆኑም በመርሃ ትምህርቱ ከቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ውስጥ 4 ወይም

57% በፈተናው ተካትተዋል። እነሱም "በቃላት ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት" ፣ "ቃላትን ማርባትና መመስረት"፣ "የቃላት ፍቺ" እና "ዐረፍተ ነገር" ናቸው።

በ2001 ዓ.ም አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅቶ የቀረበው ፈተና ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች አወካከል ሂደትን ስንመረምር ደግሞ 13 ክፍለ ጊዜ ያለው "በቃላት ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት" በ3 ጥያቄዎች፣ 35 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት ምስረታና እርባታ" በ4 ጥያቄዎች፣ 26 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት ፍቺ" በ17 ጥያቄዎች ሲወከሉ 14 ክፍለ ጊዜ ያለው "ዐረፍተ ነገር" በ2 ጥያቄዎች ተወክሏል። ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው በፈተና ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ያገኙት ውክልና ተመጣጣኝ አይደለም። ምክንያቱም በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ሰፊ ክፍለ ጊዜ ተሰጥቶት የቀረበው "ቃላትን ማርባትና መመስረት" በፈተናው ውስጥ ያገኘው ውክልና ከ "ቃላት ፍቺ" አንጻር ሲታይ በተመጣጣኝ ጥያቄዎች አልተወከለም። በሌላ በኩል 14 ክፍለ ጊዜ ያለው "ዐረፍተ ነገር" በ2 ጥያቄዎች ብቻ ተወክሎ 26 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት ፍቺ" በ17 ጥያቄዎች መወከሉ አግባብነት ያለው አይደለም። አንድ ፈተና የይዘት አግባብነት አለው የምንለው የፈተናው ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ ላይ ከመመስረት በተጨማሪ በፈተናው ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ተመጣጣኝ በሆነ ጥያቄዎች መወከል እንዳለባቸው በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል፤ በዚህ መሠረት የዚህን ፈተና የይዘት ተገቢነት ስናይ ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ በፈተናው ውስጥ ባለመወከላቸው የይዘት ተገቢነት ችግር እንዳለበት ያሳየናል።

በአጠቃላይ በማጠቃለያ ፈተናው የቀረቡትን የሰዋስው ይዘቶች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያለውን ግንኙነት ስንመረምር የቀረቡት ጥያቄዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመርሃ ትምህርቱ ከተነደፉት የሰዋሰው ይዘቶች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። ለአብነት ያክል በዚህ ዓ.ም ከቀረቡት ጥያቄዎች በጥያቄ ቁጥር 31 ላይ

- የሚጠብቅ ድምጽ ያለው ቃል የትኛው ነው?

  A. ጥብስ　　C. ልብስ

  B. ቅቅል　　D. ወንዝ

የሚለው ጥያቄ "በቃላት ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት" ከሚለው የሰዋስው ይዘት ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። ከዚህ በተጨማሪ ከጥያቄ 1-10 ያሉት የቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍቺን የሚጠይቁ በመሆናቸው እነዚህም በመርሃ ትምህርቱ በሰዋስው ትምህርት ክፍል ስር

ከተነደፈው "የቃላት ፍቺ" ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ አላቸው፡፡ በአጠቃላይ በፈተናው የቀረቡትን የሰዋስው ጥያቄዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ተዛምዶ እንዳላቸው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ይዘቶች በፈተናው ውስጥ እንደየትኩረት ደረጃቸው ተመጣጣኝ ወካይ ናሙና ስለሌላቸው በፈተናው የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች በመርሃትምህርቱ ይዘት ላይ መመስረታቸው ብቻ ፈተናው የይዘት ተገቢነት አለው አያስብለውም ፡፡

ሠንጠረዥ ስድስት ፡ የሰዋስው ይዘቶች በ2002 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና፡፡

| ተ.ቁ | ይዘቶች | ጥያቄዎቹ በፈተናው ውስጥ የሚገኙበት ተራ ቁጥር | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በቃላት ውስጥ የድምጽ መጠበቅና መላላት | 19፣20 | 2 | 10.5 |
| 2 | ቃላትን መመስረትና ማርባት | 15፣16፣17፣18 | 4 | 21 |
| 3 | የቃላት ፍቺ | 1፣2፣3፣4፣5፣6፣7፣8፣9፣10፣59 | 11 | 58 |
| 4 | የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት | - | - | - |
| 5 | የግስና የስም ገላጭ | 30፣31 | 2 | 10.5 |
| 6 | ቃልና ሐረግ | - | - | - |
| 7 | ዐ.ነገር | - | - | - |
| ከመርሃ ትምህርቱ ውጭ የሆኑ ጥያቄዎች | | - | - | - |
| | ድምር | | 19 | **100** |

በሠንጠረዥ ስድስት ከቀረበው መረጃ የምንረዳው በ2002 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበው ማጠቃለያ ፈተና ሦስት ይዘቶች በፈተናው ውስጥ አለመካተታቸውን ነው፡፡ እነዚህም "የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት" ፣ "ቃልና ሐረግን መለየት" እና "ዐረፍተነገር" ናቸው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲሠላ 43% የሚሆኑ የትምህርቱ ይዘቶች ናቸው፡፡

በዚህ ዓ.ም 19 የሰዋስው ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ የተካተቱት ጥያቄዎች መርሃ ትምህርቱን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ይህ ማለት በዚህ የማጠቃለያ ፈተና ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች በመርሃ ትምህርቱ ከተነደፉት የሰዋስው ይዘቶች ተዛምዶ አላቸው ማለት ነው፡፡ ለአብነት ያክል በፈተና ውስጥ 17ኛ ጥያቄ ላይ የሚገኘው፡

- ድርብ ቃል ያልሆነው የትኛው ነው?

  A. እንጀራ አባት　　　C. መርፌ ቁልፍ

  B. ዳቦ ቆሎ　　　D. ተበላሽቶብናል

የሚለው ጥያቄ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ቃላትን ማርባትና መመስረት ከሚለው የሰዋስው ይዘት ጋር ተዛምዶ አለው፡፡ በተጨማሪም በፈተናው ከጥያቄ 1-10 ያሉት የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒን የሚጠይቁ በመሆናቸው ይህም በመርሃ ትምህርቱ ከተነደፈው "የቃላት ፍቺ" ጋር ተዛምዶ እንዳለው እንረዳለን፡፡

በሌላ በኩል ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ያገኙትን ውክልና ስንመለከት 13 ክፍለ ጊዜ ያለው "በቃላት ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት" በ2 ጥያቄዎች፣ 35 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት እርባታና ምስረታ" በ4 ጥያቄዎች ፣ 26 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት ፍቺ" በ11 ጥያቄዎች እንዲሁም 14 ክፍለ ጊዜ ያለው "የግስና ስም ገላጭ" በ2 ጥያቄዎች ተወክለዋል፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ እንደየትኩረት ደረጃቸው ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና አለማግኘታቸውን ነው፡፡ ምክንያቱም በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ሰፊ ጊዜ የተሰጠው ይዘት በጥቂት ጥያቄዎች ተወክሎ ከዚያ ያነሰ ክፍለ ጊዜ ያላቸው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ የተሻለ ውክልና አግኝተዋል፡፡

ይህ ደግሞ ፈተናው ሙሉ በሙሉ የይዘት ተገቢነት አለው ማለት አያስችልም፡፡ ምክንያቱም በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት አለው የሚባለው ጥያቄዎቹ በመርሃ ትምህርቱ ላይ መመስረት ብቻ ሳይሆን የመርሃ ትምህርቱ ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው በፈተናው ውስጥ በተመጣጣኝ ጥያቄዎች ሲወከሉ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ይህ ፈተና ይህንን መስፈርት ስለማያሟላ ጉድለት ታይቶበታል፡፡

ሠንጠረዥ ሠባት: የሰዋስው ይዘቶች በ2003 ዓ.ም ፈተና ውስጥ ያገኙት ውክልና

| ተ.ቁ | ይዘቶች | ጥያቄዎቹ በፈተናው ውስጥ የሚገኙበት ተራ ቁጥር | ድምር | % |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በቃላት ውስጥ የድምጽ መጠበቅና መላላት | 11 | 1 | 3.4 |
| 2 | ቃላትን መመስረትና ማርባት | 12፣13፣14፣15፣16፣17 | 7 | 24.1 |
| 3 | የቃላት ፍቺ | 1፣2፣3፣4፣5፣6፣7፣8፣9፣10፣ 25፣27፣42፣43፣44፣59 | 16 | 55.1 |
| 4 | የሆሂያት ቦታ መቀያየርና መተካካት | - | - | - |
| 5 | የግስና የስም ገላጭ | 23፣24 | 2 | 6.8 |
| 6 | ቃልና ሐረግ | - | - | - |
| 7 | ዐ.ነገር | 21፣22፣32 | 3 | 10.3 |
| ከመርሃ ትምህርቱ ውጭ የሆኑ ጥያቄዎች | | - | - | - |
| ድምር | | | 29 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ ሠባት ከቀረበው መረጃ መረዳት የሚቻለው በ2003 ዓ.ም በቀረበው የማጠቃለያ ፈተና ከሠባት የሰዋስው ይዘቶች አምስቱ በፈተናው ውስጥ ተካተዋል፡፡ በዚህ ዓ.ም 29 የሰዋስው ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በርካታ ጥያቄዎችን በማቅረብ የፈተናውን የይዘት ተገቢነት መጠበቅ እንደሚችል በምዕራፍ ሁለት ተመልክተናል፡፡ አንድ ፈተና በርከት ያለ ጥያቄ ከያዘ ለይዘቶች ተመጣጣኝ የሆነ ወካይ ናሙና ማቅረብ ይችላል፡፡ እስካሁን ካየናቸው የማጠቃለያ ፈተናዎች "ቃላትን ማርባትና መመስረት" ለሚለው ይዘት የተሻለ ወካይ ናሙና ያቀረበ ነው፡፡ ነገር ግን ልክ በሌሎች ፈተናዎች ላይ እንደታየው ሁሉ የአወካከል ችግር አለበት፡፡ ለምሳሌ:_ 15 ክፍለ ጊዜ ያለው "የግስና የስም ገላጭ: በ2 ጥያቄ መወከልና 35 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት እርባታና ምስረታ" በ7 ጥያቄ መወከሉ በተወሰነ መልኩ አግባብነት ያለው ቢመስልም 26 ክፍለ ጊዜ ያለው "የቃላት ፍቺ" በ16 ጥያቄ መወከሉ ግን አግባብነት የለውም፡፡ ምክንያቱም አንድ ይዘት በብዙ የጥያቄ መጠን መወከሉ ሌሎች ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና እንዳያገኙ ስለሚያደርግ የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ይቀንሳል፡፡ በዚህ ፈተና ላይ የታየውም ይኸው ችግር ነው፡፡ በፈተናው የቃላት ፍቺ በብዙ የጥያቄ መጠን መወከል በሌሎች ይዘቶች ላይ ተፅእኖ አሳድሯል የሚል ግምት አለ፡፡

በአጠቃላይ በፈተናው ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች በመርሃ ትምህርቱ ከተካተቱት የሰዋስው ይዘቶች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው መሆኑ ጥሩ ሆኖ በአንፃሩ ግን በአንድ የሰዋስው ይዘት ላይ ብቻ ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ቀንሶታል

ስድስቱም ዓመታት ውስጥ ተዘጋጅተው የቀረቡትን ፈተናዎች በአጠቃላይ ስንገመግም ፈተናዎች ሁሉንም የመርሃ ትምህርቱን ይዘት ያለማካተትና ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው ውክልና ያለማግኘት ችግር ቢታይባቸውም ከቀረቡት 154 የሰዋስው ጥያቄዎች ሁሉም ጥያቄዎች በመርሃ ትምህርቱ ይዘቶች ላይ መመስረታቸውን ማረጋገጥ ተችሏል። ስለዚህ ፈተናዎቹ ሙሉ በሙሉ በመርሃ ትምህርቱ የሰዋስው ይዘቶች ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ተገቢነት አለው ለማለት ያስደፍራል። ነገር ግን ይህ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም፤ በመሆኑም Hughes (1989) እና Heaton (1975) እንደሚገልጹት ፈተናዎች በመርሃ ትምህርቱ ላይ እንዲመሰረቱና የትምህርቱን ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው እንዲወክሉ ለማድረግ የፈተና ንድፍ በማዘጋጀት የትምህርቱን ይዘቶችና ያገኙትን ትኩረት በመግለጽ በፈተናው ሊያገኙት የሚገባውን ወካይ ናሙና ጥያቄ ብዛት አስቀድሞ መረዳት ያስፈልጋል።

ከ1998 ዓ.ም እስከ 2003 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡት የማጠቃለያ ፈተናዎች ትንተና ለማየት እንደተሞከረው ፈተናዎች የፈተና ንድፍ ላይ ያለመመስረት ችግር ያለባቸው ይመስላል። ከኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ የፈተና ክፍል ተወካይ በዚህ ጉዳይ ላይ ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው ሲመልሱ፣ “ፈተና አዘጋጆች ሊከተሉት የሚገባ በክልሉ የተዘጋጀ መመሪያ አለ መመሪያውም ለደረጃው የተካተቱትን ይዘቶች ሁሉ ማካተት እንዳለባቸው የሚገልጽ ነው። እኛም ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋሉ ብለን እንገምታለን ከዚህም በተጨማሪ ለፈተና አዘጋጆቹ የሚሰጥ ‘ኦረንቴሽን’ ላይ በዚህ ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው መስራት እንዳለባቸው አስረግጠን እንነግራቸዋለን።” በማለት የመለሱ ቢሆንም ከቃለ ምልልሱ በኋላ አጥኚዋ መመሪያውን ለማየት እንደሞከረችው በመመሪያው ላይ ሁሉንም የትምህርቱን ይዘቶች ያካት ከማለት ውጭ የፈተና አውጪው የፈተና ንድፍ ያዘጋጅ በሱም ይከተል የሚል ነጥብ አልተመለከተችም። ቀደም ሲል ከቀረበው ግምገማም ሆነ ከቃለመጠይቁ አንድምታ መረዳት የሚቻለው ፈተና አውጪዎች የትኛው ይዘት ይካተት? በምን ያህል ጥያቄ ይወከል? የሚለውን አስቀድመው አለማከናወናቸው ሊሆን ይችላል ችግር የፈጠረው የሚል ስጋት በአጥኚዋ ዘንድ አድሯል። አጥኚዋ ይህን እንድታስብ ያደረጋት በሁሉም ፈተናዎች ውስጥ ብዙ ጥያቄዎችን

ለማዘጋጀት ወደሚቀሉ ይዘቶች ላይ ትኩረት እንዳደረጉ የሚጠቁም ነገር ስላስተዋለች ነው፡፡ ለምሳሌ የቃላት ፍቺ በብዙ የጥያቄ መጠን መወከል ጥያቄዎቹን ለማዘጋጀት ከመቅለሉ የተነሳ ነው፡፡ የሚል ግምት በአጥኚዋ ዘንድ አሳድሯል፡፡

በአጠቃላይ የስድስቱንም ዓመታት ፈተናዎች ስንመለከት በተመሳሳይ መልኩ በፈተናው ውስጥ የተዘነጉ ይዘቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ "የሆሄያት ቦታ መቀያየርና መተካካት" እንዲሁም 14 ክፍለ ጊዜ ያለው "ቃልና ሐረግ" በአንዱም የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ ምንም ትኩረት ወይም ውክልና አላገኙም፡፡ እነዚህ ይዘቶች በመርሃ ትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ተሰጥቷቸው እስከቀረቡ ድረስ በፈተናው ውስጥ ውክልና ማግኘት ነበረባቸው፤ ምክንያቱም እነዚህ ይዘቶች በፈተና ውስጥ ውክልና አለማግኘታቸው የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ዝቅ እንዲል ያደርገዋልና፡፡ እንደ Hughes (1995) ገለፃ ፈተናዎቹ ተፈላጊ ውጤት እንዲኖራቸው ይዘቶች በፈተና ውስጥ መዘንጋት የለባቸውም፡፡ ከዚህም ሌላ በፈተና የተዘነጋ በትምህርት አሠጣጥ ላይም መዘንጋቱ ስለማይቀር በዚህ ረገድ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ሁሉም የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ የሚታየው ተመሳሳይ ችግር አንድን ይዘት በከፍተኛ የጥያቄ መጠን መወከል ነው፡፡ ለምሳሌ "የቃላት ፍቺ" የሚለው ይዘት በስድስቱም ዓመተ ምህረት በተሰጡ ፈተናዎች ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር ይዟል፡፡ ይህ ደግሞ የፈተና አውጪዎቹ በአንድ አካባቢ ያሉ ይዘቶች ላይ ወይም ለማዘጋጀት የሚቀሉ ይዘቶች ላይ ትኩረት ማድረጋቸውን ያመለክታል፡፡ በአንድ አካባቢ ያሉ ይዘቶች ላይ ወይም ለማዘጋጀት ቀላል በሆኑ ይዘቶች ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ስለሚቀንስ የፈተና አዘጋጆች በዚህ ላይ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው Heaton (1975) ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ አንፃር ሁሉም የሰዋስው ፈተና ጥያቄዎች በአብዛኛው "የቃላት ፍቺን" መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ እነዚህን ብቻ በፈተና ውስጥ ማቅረቡ ደግሞ የፈተናው የይዘት ተገቢነት እንዲቀንስ አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም የማጠቃለያ ፈተናዎች ለአንድ ደረጃ የቀረበውን ትምህርት ተማሪዎች ምን ያህል አውቀዋል የሚለውን ለመገምገም ከመዘጋጀታቸው አንጻር ሁሉም የትምህርቱ ይዘቶች ተመጣጣኝ የሆነ ወካይ ናሙና ማግኘት ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን የጥናቱ ተተኳሪ ፈተናዎች ይህንን አሟልተው አልተገኙም፡፡

ከላይ ከቀረበው የእያንዳንዱ ዓመተ ምህረት ፈተናዎች ዝርዝር ትንታኔ መረዳት የሚቻለው ሁሉም ፈተናዎች ላይ ተመሳሳይ የሆነ ችግር መኖሩን ነው፡፡ በየዓመቱ ተዘጋጅተው የቀረቡት የማጠቃለያ ፈተናዎች ላይ ተመሳሳይ ችግር መንፀባረቁ ደግሞ ክልሉ በፈተናዎቹ ላይ ምንም

አይነት ጥናት አለማድረጉንና ለፈተና አዘጋጆቹ ሙያዊ እገዛ የሚያደርጉ ሥልጠናዎችን አለመስጠቱ እንደሆነ በቃለ መጠይቁ ተረጋግጧል።

## 4.2 የጥያቄዎች አዘገጃጀት

እንደ Callaham እና Clark (1988) የምርጫ ሰጪ እና አታች የጥያቄ አይነቶች በችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተዘውትረው የሚታዩ ናቸው። በዚህ ክፍል ለማየት የታሰበውም የጥናቱ ትኩረት በሆኑት የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ የምርጫ ሰጪና አታች ጥያቄዎችን ቢሆንም የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ሁሉም የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች ከምርጫ ሰጪ የጥያቄ አይነቶች ባለብዙ ምርጫ ሰጪ (multiple choice item) ጥያቄዎች ብቻ በመሆናቸው በዚሁ ጥናት የሚዳሰሱት ባለ ብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ብቻ ይሆናሉ። በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ እነዚህ የባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ተገቢ የአዘገጃጀት መርሆችን ተከትለው መዘጋጀት አለመዘጋጀታቸውን እንመለከታለን።

### 4.2.1 ባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች (multiple choice item)

ባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ሊከተሏቸው የሚገቡ በርከት ያሉ የአዘገጃጀት መርሆች አሉ። በምዕራፍ ሁለት በ2.3.4.3 ላይ በተዘረዘሩት የባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች መስፈርት መሠረት  የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ የ6 ዓመት የማጠቃለያ ፈተናዎች የቀረቡትን 154 የባለ ብዙ ምርጫ ሰጪ የሰዋስው ጥያቄዎችን በመመርመር ጥያቄዎቹ መርሆቹን ተከትለው መዘጋጀት አለመዘጋጀታቸውን በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ እንደሚከተለው ዝርዝር ማብራሪያ ለማቅረብ ተሞክሯል።

- እያንዳንዱ ጥያቄ የታሰበለትን ችሎታ መለካት እንዲችልና ትክክለኛ መረጃ እንዲሰጥ ግልጽ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፡- በክልሉ ትምህርት ቢሮ የተዘጋጁና የ6 ዓመት ፈተናዎች ውስጥ ከቀረቡት 154 የሰዋስው ጥያቄዎች ሁሉም የያዟቸው ሃሳቦች ተማሪዎቹ ያለምንም ችግር ሊረዷቸው ይችላሉ የሚል ግምት አለ፤ ከዚህ መስፈርት አንጻር በሁሉም ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች የግልጽነት ችግር የሚታይባቸው አይደሉም።
- ተማሪዎቹ በተሰጣቸው ጊዜ የተሰጣቸውን ጥያቄዎች በተገቢው መመለስ እንዲችሉ አንዱን ሀሳብ በሁሉም ምርጫዎች ከመደጋገም በጥያቄ ግንዱ ላይ አንድ ጊዜ ማስፈር

ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎችም ቢሆኑ የያዙት ዋጋ ተመጣጣኝ ነው ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በማጠቃለያ ፈተናዎቹ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች ለምሳሌ “የቃላት ዕርባታና ምስረታ” ሆነ “ገላጮች” በፈተናው ውስጥ የተሰጣቸው ዋጋ እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ጥያቄዎቹን መስሪያ ተገቢ ጊዜ መመደብ ነው፡፡ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተማሪዎቹ የትምህርቱን ይዘቶች ምን ያህል እንዳወቁ መለኪያ ስለሆኑ በቂ ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ ለሆኑት የማጠቃለያ ፈተናዎች የተሰጠው ጊዜ ስናይ ለሁሉም ማጠቃለያ ፈተናዎች የተሰጠው ጊዜ 60 ደቂቃ ነው፡፡ ለአንድ ጥያቄ አንድ ደቂቃ እንደማለት ነው፡፡ በመሆኑም በእያንዳንዱ የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ ለቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች የተሰጠው ጊዜ በቂ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ጥያቄዎቹ የቀረቡት በባለ ብዙ ምርጫ ሰጪ የጥያቄ ስልት መሆንና የግልፅነት ችግር የሌላቸው መሆኑ የተሰጠው ሰዓት በቂ ይመስላል፡፡

በዚህ ጥናት አጠቃላይ መርሆችን በተመለከተ መካተት ያለባቸው የጥያቄ ማቅረቢያ ስልቶች ያለመካተት ችግር ቢኖርም እንዳይካተቱ የሆኑበትን ምክንያት ተወካዩ በገለፁት መሰረት አሳማኝ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ፈተናዎች በእጅ የመታረማቸው ጉዳይ በተማሪዎች ውጤት ላይ ልዩነትን ሊፈጥር ይችላል የሚለው አሳማኝ ምክንያት ይመስላል፡፡ በተረፈ ፈተናዎቹ ከመርህ አንፃር ሲታዩ በአብዛኛው ጠንካራ ጎናቸው የጎላ ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ እና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ከ1998 - 2003 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ለስምንተኛ ክፍል አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅተው በቀረቡት ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች ተገቢ የመመዘኛ መሣሪያ መሆን አለመሆናቸውን መመርመር ነበር። በዚህ መሠረት በጥናቱ የሚመለሱ መሠረታዊ ጥያቄዎች የሰዋስው ጥያቄዎች መርሃ ትምህርቱን መሠረት አድርገው ተዘጋጅተዋል? ፤ ጥያቄዎቹ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ያሉ ይዘቶችን እንደየትኩረት ደረጃቸው የወከሉ ናቸው ወይስ አይደሉም? እና ጥያቄዎቹ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች የሚዘጋጁበትን መርህ ተከትለው የተዘጋጁ ናቸው? የሚሉት ነበሩ።

እነዚህን መሠረታዊ የጥናት ጥያቄዎች ለመመለስና ውጤት ላይ ለመድረስ ከተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ማለትም ከሰነድ ፍተሻ እና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ገላጭ ስልትን በመጠቀም ተተንትነዋል። በዚህም ከ1998 - 2003 ዓ.ም የተዘጋጁ ፈተናዎች ተመርጠው በጥሩ የፈተና መስፈርት የይዘት ተገቢነት እና በፈተና አዘገጃጀት መርሆች ተገምግመዋል። ከትንተናው በኋላም የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል።

- በመርሃ ትምህርቱ ያሉ ይዘቶችን በመዘርዘር በእያንዳንዱ ፈተና ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ጥያቄዎች በእነዚህ ይዘቶች ላይ መመስረታቸውን ይዘቶችን እንደየትኩረት ደረጃቸው መወከላቸውን በማየት የፈተናዎችን የይዘት ተገቢነት ለመመርመር በተደረገው ሙከራ የተወሰኑ የሰዋስው ይዘቶች በፈተናው ሳይካተቱ የቀሩ መሆኑና የተካተቱት ይዘቶችም ቢሆኑ እንደየትኩረት ደረጃቸው በተገቢ የጥያቄ መጠን እንዳልተወከሉ ማየት ተችሏል።

- ፈተናዎች የታሰበላቸውን ዓላማ እንዲያሳኩ ተገቢ መርሆችን መሰረት አድርገው መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ አንፃር የተለያዩ ምሁራን ያነሷቸውን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ ፈተናዎች ተገምግመው በአብዛኛው ጠንካራ ጎናቸው የሚያይል ቢሆንም የተወሰኑ ድክመቶች እንዳሉባቸው ማየት ተችሏል። አሉታዊ ቃሎችና ሐረጎችን በተገቢው

መንገድ ያለመጠቀም፣ ሁሉም መልስ ነው የሚሉ አማራጮችን መጠቀም እና አላስፈላጊ ድግግሞሽ በተወሰኑ ፈተናዎች(ጥያቄዎች) ላይ የሚታዩ አብይ ችግሮች ናቸው። በሌላ በኩል ሁሉም ፈተናዎች መካተት የሚገባቸውን የጥያቄ ዓይነቶች ያለማካተት ችግር ታይቶባቸዋል ይህም የመነጨው ፈተናዎቹ በክልል ደረጃ ተዘጋጅተው ለበርካታ ተማሪዎች የሚሰጡ በመሆኑና ፈተናውን የሚያርሙት የተለያዩ ሰዎች በመሆናቸው የውጤት ልዩነት ሊያመጣ ስለሚችል ይህንን ችግር ለማስቀረት ሁሉም ጥያቄዎች በባለ ብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች እንዲሆኑ የተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት

1. አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት እንዲኖረው የሚያካትታቸው ጥያቄዎች በመርሃ ትምህርቱ ላይ መመስረትና ይዘቶችን እንደየትኩረት ደረጃቸው መወከል ይኖርባቸዋል። በስድስቱ ፈተናዎች ከቀረቡ 154 ጥያቄዎች ሁሉም የሰዋስው ጥያቄዎች በመርሃ ትምህርቱ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸው ተረጋግጧል። ከዚህ ሌላ የተወሰኑ የትምህርቱ ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ውክልና ሳያገኙ መቅረታቸው እና በፈተናው የተካቱት ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው በተገቢ የጥያቄ መጠን ያለመወከል ችግር ታይቶባቸዋል። ለምሳሌ በመርሃ ትምህርቱ ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቶት የቀረበ ይዘት በተገቢ የጥያቄ መጠን መወከል አለመቻሉ Hughes (1995) እንደሚሉት ፈተና አውጪዎቹ የሚፈትኑት መፈተን ያለባቸውን ሳይሆን ለመፈተን አመቺ የሆኑላቸውን ይዘቶች ነው ወደሚል ድምዳሜ የሚመራ ይመስላል። በዚህ የተነሳ ይሁን በሌላ ምክንያት መመዘን ካለባቸው የሰዋስው ይዘቶች ብዙዎቹ በፈተናው አለመሸፈናቸው የይዘት ተገቢነቱን ደረጃ ዝቅ ያደረገው ይመስላል።

2. በተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ ከታዩ ጉድለቶች በስተቀር ፈተናዎቹ በአብዛኛው ተገቢ የአዘገጃጀት መርሆችን ተከትለው እንደተዘጋጁ ከተደረገው ግምገማ ለማረጋገጥ ተችሏል።

## 5.2 አስተያየት

የጥናቱን ውጤት መሠረት በማድረግ ወደፊት ለሚዘጋጁት ፈተናዎች መነሻ እንዲሆኑ የሚከተሉት አስተያየቶች ወይም መፍትሔዎች በአጥኚዋ ቀርበዋል።

1. በምዕራፍ አራት ከቀረበው የይዘት ተገቢነት ትንተና እንደታየው 28.5% የሚሆኑ የትምህርቱ ይዘቶች በፈተናዎቹ ውስጥ ያለመካተት ችግር ተስተውሏል። ስለዚህ ይህ

ችግር እንዳይከሰት የፈተና አውጪዎቹ በቅድሚያ ፈተና ንድፍ ቢያዘጋጁና እያንዳንዱ ይዘት በምን ያህል ጥያቄ መወከል አለበት የሚሉትን ቢወስኑ ችግሮቹን መቅረፍ ይቻላል። ከዚህ ሌላ የጥያቄዎቹን መጠን ከፍ በማድረግ ሁሉም ይዘቶች በተገቢ የጥያቄ መጠን እንዲወከሉ በማድረግ፣የፈተናዎቹን ይዘቶች በቀረበው መርሃ ትምህርት ላይ እንዲመሰረቱና ይዘቶችን እንደየትኩረት ደረጃቸው እንዲወከሉ ቢደረግ፣

2. ፈተናዎች ተገቢ የአዘገጃጀት መርህን ተከትለው መዘጋጀት አለመዘጋጀታቸውን ለማወቅ በተደረገው ምርመራ እንደታየው በአብዛኛው የፈተናዎች ጠንካራ ጎን የሚያይል ቢሆንም በአንዳንድ ጥያቄዎች አሉታዊ ቃላትና ሐረጋትን በአግባቡ ያለመጠቀምና አላስፈላጊ ድግግሞሾች ተስተውለዋል። እነዚህ ችግሮች ፈተናዎች ሊያስገኙ የታሰበውን ዓላማ እንዳያሳኩ እንቅፋት ሊፈጥሩ ስለሚችሉ፤ የፈተና አውጪዎች በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ብርቱ ጥንቃቄ ቢያደርጉ የፈተናዎችን ብቃት ማሳደግ ይቻላል። በመሆኑም በፈተና ዝግጅት ወቅት ለእያንዳንዱ ጉዳይ ትኩረት ቢሰጥ፤

3. ፈተናዎችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመገምገም ከተገኘው መረጃ የተወሰኑም ቢሆኑ ችግሮች ተስተውለዋል። እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ፈተናዎች የታሰበላቸውን ዓላማ ሙሉ በሙሉ ማሳካት ይችሉ ዘንድ ለፈተና አዘጋጆች ስልጠና መስጠት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ለዚህም የሚመለከታቸው ክፍሎች ፈተና ሲደርስ ብቻ ሰብስቦ ፈተና ማዘጋጀት አለባችሁ ከማለት ይልቅ በፈተና አዘገጃጀትና አፈታተን ላይ ለፈተና አዘጋጆች ሙያዊ ስልጠና ቢሰጥ፤

4. በክልሉ የሚዘጋጁ ፈተናዎች ብቃት ከፍ እንዲል በየጊዜው የሚሰጡ ፈተናዎች ላይ ግምገማ ማድረግ የፈተናውን የመመዘን ብቃት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ እንዲሄድ ስለሚያደርግ በየጊዜው ተዘጋጅተው በሚቀርቡ ፈተናዎች ላይ ግምገማ ማድረግ ጠቀሜታ አለው፣ በመሆኑም የሚመለከተው አካል በየጊዜው የሚዘጋጁ ፈተናዎች ላይ ግምገማ ቢያደርግ፤

# ዋቢ ፅሁፎች


ራሔል ወርቁ።(2001)። "ከ1993 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም በቀረቡት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መልቀቂያ ፈተናዎች የመድብለ ቃላት አፈታተን።" በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ /ያልታተመ/።

በለጠ ያዕቆብ።(1995)። "ለዘጠነኛ ክፍል የሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ለደረጃው ከሚቀርበው ትምህርት ጋር ያላቸው የይዘት አግባብነት እና ያጠያየቅ ብቃት ትንተና።" በቋንቋዎች ጥናት ተቋም ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ /ያልታተመ/።

ባየ ይማም ፡፡ (1987)፡፡ *የአማርኛ ሰዋስው፡፡* አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

----------------። (2000)። *የአማርኛ ሰዋስው*። የተሻሻለ ሁለተኛ እትም። አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማ.ኃ. የግ. ማህበር።

ተስፋዬ መኮንን።(2000)። "በኮምቦልቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ1997 እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ የቀረቡት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸው የይዘት አግባብነት እና የአጠያየቅ ብቃት።" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል፣ ለቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ የተዘጋጀ ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ /ያልታተመ/።

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡(1981)፡፡ "ስነ ልሳንና ቋንቋን ማስተማር፡፡" አዲስ አበባ፣ (ያልታተመ)፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር።(1997)። "አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት።" (5-8ኛ ክፍል)። አዲስ አበባ ፣ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት።

ትንሳኤ ብርሃኔ።(1988)። "የአማርኛ የቃላት አፈታተን በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና መነሻነት (ከ1980-87)።" የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

አበበ ከበደ።(1975)። "የ6ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ግምገማ።" የቢኤ.ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጽሑፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ) ።

አገኘሁ ተስፋ፡፡(1990)፡፡ "አማርኛን በማስተማር ሂደት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች አፈታተን የይዘትና የላህይ አግባብነትና ያጠያየቅ ብቃት፡፡" በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ /ያልታተመ/፡፡

ኤደን ብርሃኔ፡፡(2002)፡፡ "ከ1995 ዓ.ም እስከ 2001 ዓ.ም በቀረቡ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የቃላት አፈታተን ግምገማ በደብረማርቆስ ከተማ በሚገኙ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት፡፡" በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ የጥናት ፅሑፍ ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ /ያልታተመ/፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡(1998)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር*፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡(1990)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

----------------፡፡(1990)፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*፡፡ አዲስ አበባ አልፋ አታሚዎች ድርጅት፡፡

ፀጋዬ ግርማ፡፡(1997)፡፡ "በ1995 እና በ1996 ዓ.ም ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል መምህራን ስልጠና የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ የሴሚስተር ማጠቃለያ ፈተናዎች ግምገማ፡፡" በቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ /ያልታተመ/፡፡

Alderson, J.C Clapham, C. and Wall.O (1995). *Language Test Construction and Evualtion.* Camridge: Cambridge University press.

--------------.(2001). *Languge Test Construction and Evaluation.* 5th ed. Cambridge: Cambridge Univesity Press.

Bachman, L.F. (1990). *Fundamental Consideration in Language Testing.* Oxford: OUP.

___________.(1995). *Fundamental Consideration in Language Testing.* 3rd ed. Oxford: OUP.

Baker, D. (1989). *Language Testing*: Ariticla Survey and Practical Guide. London: Divison of Hodder and Stoughton.

Best, J.W, and Khan, J, V. (2002). *Research in Educaiton.* New Delhi: Prentice. Hall of India.

Brown,F.G.(1970). *Principls of Educational and Psychological Testing.* Lowa: The Dryden Press Inc.

-----------------.(1981). *Measureing Class Room Achievment.* New York: Holt Rinerhart and wiston.

----------------.(1983). *Princpels of Edcuational and Psychological Testing.* (3rd.ed). New York: CBC College Publishing.

Brown, H.D.(1980). *Principles of Learning and Teahcing.* New Jeresey: Prentice Hall Ince.

Brwon, J.D.(1994). *Princple of Language Learning and Teacing.* New Jersey: Profice Mull Regent.

Callhan, J.F. and Calrk,L.H. (1988). *Teaching in the Middle and Secondary Schools: Planning to Competence.* 3rd ed. New York: Macmillan Publishing Company.

Davies, A. (ed).(1968). *Language Testing Symposium*: A psycholotustic prespet ice. Oxford: OUP.

__________.(1984). "Validating Three Testes of English Language Proficency." *Language Testing.* Vol.1.No.1:50-59.

Dejene Leta. (1990). "Achievment wash back and profeiciency in school leaving exmintation." Acase of innovation in on Ethiopia setting unpublished PHD. Theis) university of Lancster; United Kingdom.

________.(1994)."Language Testing and its practical application." A.A. Department of forein languages and Literature Institute of Language studies A.A.U.

Dornyei, Z.(2007). *Research Methods in Applied Linguistics.* Oxford: Oxford University Press.

Finochiaro,M. & Brumift, C. (1983) . *The Fundamental National Appraoch: From Theory to Practice* .Oxford: OUP.

Gronlund, N.E.(1981). *Measurement and Evaluation in Teaching.* 4th ed. New York: Macmillan Publishing Co, Inc.

Harrison, A. (1989). *A Language Testing Hand Book.* London: Macmillan Publishing.

Heaton, J.B.(1975) .*Writing English Language Tests* . London: Longman.

---------------.(1990). *Class room Testing.* London: Longman.

Hughes, A. (ed).(1989) .*Testing for Languae Teachers.* Cambridge: Cambridge Univeirsty Press.

---------------------.(1995). .*Testing for Languae Teachers.* 2nd ed. Cambridge: Cambridge Univeirsty Press.

Kitao, S.K and kitao, K.(1996). "Testing Grammar." Interent Tesol Jounral, 2, 6.

Larsen Freeman, D. (1997). *Grammar Diamnession.* (2nd Ed). Henile: Henile Publisher.

Madsen, H.(1983). *Techniques in Testing* .Newyork: Oxford University Press.

Oller, J.W.(1979). *Language Test at School.* London: Longman.

Sax,G.(1974).*A Principle of Educational Measurmenet and Evaluation.* Calif ornia: Words Mouth Publisher.

Stevenson,D. K.(1977). "Language Testing and Academic Accounablity on Redefining the role of language Testing." ELT Journal 19:26-48.

Underhill. N.(1987). *Testing Spoken Language* .A hand book of orla testing techniquies Cambridge: Cambridge University Press.

Ur, P.(1988). *Grammer Practice Activities Apractical Gudie for Teahcers.* Cambridge: Cambridge University Press.

-----------.(1996). *A Course in Language Teaching:* practice and Theroy Cambridge: Cambridge University press.

Weir, C.J.(1993). *Understanding and Developing Language Tests.* London: Prentice Hall.

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ

**ከ1998-2003 ዓ.ም በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡትን የሰዋስው ጥያቄዎች በዓመተ ምህረትና በመመሪያ የሚያሳይ**

1. 1998 ዓ.ም

*መመሪያ አንድ፡- ከሚከተሉት ቃላት ተመሳሳያቸውን ምረጡ።*

1. እድፍ
   A. ብልሽት B. እንከን C. ቆሻሻ D. ጥራት
2. አከተመ
   A. አቋቋመ B. አደራጀ C. አለቀ D. አበቃ
3. ገመና
   A. ምስጢር B. ጎመን C. ግልፅ D. የተገመደ
4. ከረመ
   A. ከተመ B. ቆየ C. አረፈደ D. ጠፋ
5. በደምሳሳው

*መመሪያ ሁለት፡- ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን ምረጡ።*

6. ተቆራኘ
   A. ተጣበቀ B. ተያያዘ C. ተለያየ D. ተበታተነ
7. ገሚስ
   A. ብልሽት B. እኩሌታ C. ጎዶሎ D. የተገመሰ
8. ታዛዥ
   A. እሺ ባይ B. የበታች C. አሽከር D. እምቢተኛ
9. ኩርፊያ
   A. ጥል B. ፈገግታ C. ፍቅር D. ደስታ
10. ሁካታ
   A. ፀጥታ B. ጫጫታ C. ወሬ D. ዝምታ

*መመሪያ ሶስት፣ የተሰመረባቸውን ቃላትና ሐረጎች ፍች በዓረፍተ ነገሩ አገባብ መሠረት መልሱ*

11. ሥራ ፍለጋ ብዙ <u>ባዘነ</u>።
   A ሮጠ B. ተንከራተተ C. ሞከረ D. ቦታ ሄደ
12. ሽንኩርቱን <u>እየመተረ</u> ድስቱ ውስጥ ጨመረ።
   A.እየላጠች B. እያጠበ C. እያቁላላ D.እየከተፈ
13. ክረምቱ <u>ከባተ</u> ገና ሳምንቱ ነው።
   A.ከጀመረ B. ከገባ C. ከጠነከረ D.ካቆመ

14.ብዙ መክሬው ስለታከተኝ ተውኩት፡፡

A.ስላልሰማኝ B.ስላቃተኝ C. ስለደከመኝ D.ስለሰለቸኝ

15.አንደኛው ነቃሽ ስላልቀረበ ውሳኔ መስጠት አልተቻለም፡፡

A.ምስክር B.ከሳሽ C. ዳኛ D. ተከሳሽ

*መመሪያ ስድስት፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደ ትዕዛዙ መልሱ*

26. ላይጨለጥ እንደ ውሃ በሚለው ስንኝ ውስጥ የተሰመረበትን ቃል---------ሊተካ ይችላል

A.ላይፈላ B. ላያረካ C. ላይደፋ D. ላይጠፋ

27. ላይቆረጠም ሲል-------------- ማለቱ ነው፡፡

A. ላይቆላ B. ላይበላ C. ላይጣፍጥ D.ላይታመስ

28. ላይሆነኝ ከፈን ሲል ምን ማለቱ ነው

A. ልብስ ላይሆነኝ B. ምግብ ላይሆነኝ C. መጠለያ ላይሆነኝ D. መድኃኒት ላይሆነኝ

*መመሪያ ሰባት ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደ ትዕዛዙ መልሱ*

31. ከሚከተሉት ቃላት ከአንድ በላይ ፍቺ የሌለው ------------ነው፡፡

A. ጠርጥር B.ጠራ C.ተራ D.ጠረጴዛ

32. የኦሮሚያ ልማት ማህበር በምህፃረ ቃል ሲፃፍ --------- ነው፡፡

A. የ.ል.ማ B. ኦ.ል.ማ C. የ.ኦ.ል.ማ D.ኦሮሚ.ያ. ል.ማ

33. የሚያንን ነገር አየች፡፡ በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ ገላጩ ቃል------- ነው፡፡

A. ነገር B. አየች C. የሚያንን D. የሚያንን ነገር

34. የሚመጣው በሚለው ቃል ውስጥ ያሉት ቅጥያዎች------ ናቸው፡፡

A. የሚ.... B. ...ው C. የ... D. የሚ....ው

35. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ሲጠብቅና ሲላላ የፍች ልዩነት የሚያመጣው----------ነው፡፡

A. መሳም B. መብላት C. ሠራ D. መጥፋት

36. "መለየት" የሚለው ቃል ሲላላ------- የሚል ትርጓሜ አለው፡፡

A. መራራቅ B. ለይቶ ማወቅ C. መጣላት D. መጥፋት

37. "የሚሰማው" በሚለው ሀረግ ውስጥ ዋናው ቃል -------------- ነው።

A. የሚሰማ B. ሰማው C. ሰማ D. የሚሰማው

38. ህዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች መኪናዎን በዝግታ ያሽከርክሩ። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ የአንቀጽ ገላጭ የሆነው------------ ነው።

A. ሕዝብ በሚበዛባቸው B. አካባቢዎች C. በዝግታ D. ያሽከርክሩ

39. አስገረመን በሚለው ሀረግ ውስጥ ባለቤት ወይም ድርጊት ፈፃሚው-------- ነው።

A. እርሱ B. እኛ C. እናንተ D. እነርሱ

40. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ውስጠ ግንድ ቅጥያ የሌለው ------------- ነው።

A. ተባበረ B. ድርብርብ C. ትክክል D. ቀጫጭን

42. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መካከል ትክክለኛው የቱ ነው

A. እኔ ሊቅር እናንተ ሂዱ።

B. እኔ ልቅር እናንተ ሂዱ

C. እኔ ልቅር እናንቴ ሂዱ።

D. እኔ ሊቅር እናንተ ህዱ።

43. -------------የተነሳ እጁ ይንቀጠቀጥ ነበር። ለባዶ ቦታ ተስማሚ ቃል---------ነው።

A. ከመደሰቱ B. ከመናደዱ C. ከመጨነቀ D. ከመፍራቱ

45. የሚናገረው <u>በጥድፊያ</u> ነው። የተሠመረበትን ቃል---------- ሊተካው ይችላል

A. በቀስታ B. በችኮላ C. በዝግታ D. ድምፁን ከፍ አድርጎ

2. 1999 ዓ.ም

መመሪያ አንድ፣

ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳያቸውን ምርጥ/ጪ

1. ንጎለ

A. ለሰለሰ C. ተያያዘ

B. ሻከረ D. ተላቀቀ

2. ሽርክት

A. የላመ C. ያልደቀቀ

B. የደቀቀ D. የጠጠረ

3. ስታቴ

A. ገንቦ C. እንስራ

B. ድስት D. ምጣድ

4. ወረፋ

A. ድርሻ C. ተራ

B. ክፍያ D. ሰልፍ

5. እንገር

A. እርጎ C. አጓት

B. የጊደር ወተት D. ስጋ ቅቤ

መመሪያ ሁለት

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን ምረጪ/ጥ

6. ወቀሰ

A. አመሰገነ C.አማረረ

B. ተቸ D.አማ

7. ትእቢተኛ

A. ጥጋበኛ C. እብሪተኛ

B. ትሁት D. ቸር

8. ጦዘ

A. ከረረ C. ተልፈሰፈሰ

B. ለሰለሰ D.ረገበ

9. ቃረመ

A. አገዘረከረከ C. ሰበሰበ

B. አረሰ D.ጫኀ

10.ግርድ

A. እህል C.ትንሽ

B. ምርት D. ሰብል

መመሪያ ሶስት፡-

**ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተነገሮች ወስጥ የተሰመረባቸውን ሀረጋት አገባባዊ ትርጉማቸውን ምረጥ/ጪ**

11. አይኑን ሲያጉረጠርብኝ ፈራሁት

A. ሲጠቅሰኝ C. ሲያሽሟጥጠኝ

B. ሲያጮልቅብኝ D. ሲያፈጥብኝ

12. ቅጥ አምባሩ ጠፍቶብኛል

A. ውሉ C. አዝማሚያው

B. አቅጣጫው D. ሀሳቡ

13. ሺብሬ ምንም ጥሩ ነገር ብትናገር ደሟ መራራ ነው፡፡

A. አነጋገሯ ለዛ አለው C. ደሟ ይፈላል

B. ንግግሯ አይጥምም D. ነገር ይከርባታል

14. እሱ የጭካ እሾህ ስለሆነ ከእሱ ጋር ጓደኝነት ቢቀርብህ ይሻላል

A. ነገረኛ C. መሰሪ

B. ፀበኛ D. ተንኮለኛ

15. ወላድ በድባብ ትሂድ እንጂ ምን አለማመጠሽ

A. በሰረገላ ታጅባ C. በጥላ (በገምንጥላ) ተከልላ

B. ተሞሽራ D. በሰጋር በቅሎ ተቀምጣ

መመሪያ አስር፡-

**የሚከተሉትን ሰዋስው ነክ ጥያቄዎች በመመሪያዎች መሰረት መልስ/ሺ**

45. አላገኝሁትም

የዚህ ሃሳብ(አባባል) ባለቤት መሆን የሚችለው -------------- ነው፡፡

A. እሱ C. አንተ

B.እኔ D. እሷ

46. አላገኘሁትም  በተሰኘው ሀሳብ ተሳቢ ሊሆን የሚችለው------------- ነው።

A. እሱን C. አንተን

B.እኔን D. እሷን

47. ልብስ በተሰኘው ቃል ውስጥ ----------------አናባቢዎች እና ------------ተነባቢዎች አለ/ሉ።

A. 3፣2 C. 1፣3

B.3፣1 D. 2.፣3

48. ፈተናውን <u>ከሰራህ</u> ታልፋለህ በተሰመረበት ቃል ላይ  ቅድመ ቅጥያው -------- ሲሆን ድህረ ቅጥያው -----------------ነው

A. ከሠ--እና--ራህ C. ራህ እና ከሠ

B. ህ እና ከ D. ከ--እና---ህ

53. ሜዳው ላይ ያለው ረኛጅም ዛፍ ሽው ይልና ወደ አንድ ወገን <u>ያጋድላል</u>። የተሰመረበት

ቃል ትርጉም

A. ይተኛል C. ያጎነብሳል

B. ይጋደማል D. ያዘማል

54. "...የበረሃ ወንዝ ይደፈርሳል የሚል <u>ንግርት</u> አለ" የተሰመረበት ቃል ትርጉም

A. ተንኮል C.አስማት

B. ትንቢት D. ፍልስፍና

3. 2000 ዓ.ም

መመሪያ አንድ፡-

ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳያቸውን ምርጥ/ጪ

2. አፋፍ

A. አፍ C. መሃል

B. ከፍታ ላይ D. ቤት ውስጥ

2. በራ

A. ገላጣ
C. ብርሃን ሰጠ
B. ተራበ
D. A እና B ትክክል ናቸው፡

3. ማላገጥ

A. ማጋለጥ
C.ማዋሃድ
B. ማሾፍ
D. ማስረዳት

4. ሳይታክት

A. ደከመኝ ሳይል
C.ሳይሰራ
B. ሳይጨምር
D. ሳይመለከት

5. መናጆ

A. የከብት እረኛ
C. ተከታይ
B. መሳሪያ
D. አውደልዳይ

መመሪያ ሁለት፡-

ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን ምረጥ/ጭ

1. አቆለቆለ

A. አዘቀዘቀ
C. አቋረጠ
B. አሻቀበ
D. አጓደለ

7. ሲነጋ

A. ሲጨልም
C. ሲደነግዝ
B. ሲመሽ
D. ሁሉም

8. ተከለ

A. ሰጠ
C. ወጋ
B. ነቀለ
D. ጠወለገ

9. ፈረጠመ

A. ጠነከረ C. ከሳ

B. ደነደነ D. ታየ

10. መልከኛ

A. አስቀያሚ C. ውብ

B. ቆንጆ D. ደግ

**መመሪያ ሶስት**

**ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ወይም ሐረጎች አገባባዊ ትርጉም ምረጥ/ጪ**

11.ሰውየው የያዘው ዱላ <u>ገዳዳ</u> ነው፡፡

A. ጠንካራ C. ቀጥያለ

B. ጠማማ D. ጫፉ ወፍራም

12. በሰፈራችን የተፈጠረውን አደጋ ሲሰማ <u>ክው አለ</u>፡፡

A. ዝም አለ C. ደነገጠ

B. ተዝለፈለ D. ተደሰተ

13. የቡድናችን <u>አንጋፋ</u> ተጫዋች ተብሎ የሚታወቀው እሱ ነው፡፡

A. ዝነኛ ተጫዋች C. አስጠቂ ተጫዋች

B. አጥቂ ተጫዋች D. ያለእድሜው የሚጫወት

14. መምህሩ ተማሪውን <u>በፈገግታ</u> ተቀበለው፡፡

A. በቁጣ C. በግዴለሽነት

B. በደስታ D. ፊት ለፊት

15. እናንተ ግቢውን <u>አጽድታችሁ</u> ቆዩን፡፡

A. ባዶ አድርጋችሁ C.ንጹህ አድርጋችሁ

B. ሙሉ አድርጋችሁ D. አስፍታችሁ

መመሪያ ሰባት

ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ

31. በአነባብ ወቅት የሚጠብቅ ድምጽ ያለው ቃል የትኛው ነው?

A. መሰንቆ C. ወንዝ

B. መሸ D. ተራራ

32. "በላ" በሚለው ቃል ውስጥ ያለው "ላ" ላልቶ ሲነበብ የቃሉ ትርጉም -----------ይሆናል።

A. ተመገበ C.ከላይ

B. አስረዳ D. ተናገረ

33. "የመጽሀፋን" የሚለው ቃል መነሻ(ግንድ) ቃል -----------------ነው

A. መጽሐፍ C. የመጽሐፍ

B. መጽሐፉ D. መጽሐፉን

34. "ስለተማረው" በሚለው ቃል ውስጥ ቅጥያዎቹ የትኞቹ ናቸው?

A. ስለ- C. ስለ-ው

B. -ው D. ቅጥያ የለውም

35. "ወሰደላቸው" በሚለው ቃል ውስጥ ባለቤቱ -----------ነው።

A. ለእነርሱ C. እናንተ

B. እርሱ D. እኔ

36 "ወሰደላቸው" በሚለው ቃል ውስጥ ተሳቢው ------ነው።

A. ለእነርሱ C. እናንተ

B. እርሱ D. እኔ

39. በቃሉ ውስጥ ያለው ድምጽ ሲነበብ በመጥበቁ ወይም በመላላቱ ምክንያት የትርጉም ለውጥ የሚያመጣው ቃል የትኛው ነው

A. ልብስ C. ምስራቅ

B. በሽታ D. መኪና

40. "የትምህርት ቤት መግቢያ ሰዓት ስለተቃረበ በፍጥነት ሄዳ።" በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ ገላጭ የሆነው ቃል የትኛው ነው

A. በፍጥነት C. መግቢያ

B. ሄዳ D. ገላጭ የለውም

41. ብዙ ቁጥር ሆኖ ሲገለፅ ትክክል የሆነው የትኛው ነው

A. ቀሳውስቶች C. መምህራኖች

B. አእዋፍ D. አናብስቶች

55. "ሰውነቱን ሳያፍታታ" የሚለው ሐረግ ፍቺ ምንድን ነው?

A. የታሰረበትን ሳያላቅቅ C. ሳይንጠራራ

B. ሰውነቱን ሳያሟሙቅ D. ሳያልበው

56. "ተፈናጥሮ ወጣ" በሚለው ዓረፍተነገር ፍች ምንድን ነው

A. በፍጥነት ወጣ C. ቀልጠፍ ብሎ ወጣ

B. ዘሎ ወጣ D. ሁሉም

57. "አንዳንድ ሰንበቶችን" የሚለው ቃል ፍቺ ምንድን ነው

A. አውዳ-ዓመት C. የእረፍት ቀን

B. አንዳንድ እሁዶች D. ሁሉም

4. 2001 ዓ.ም

*መመሪያ አንድ*

**ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳያቸውን ምረጥ/ጪ።**

1. አስፀያፊ

A. አስደሳች C. አስኮራፊ

B. አስቀያሚ D. አጠራጣሪ

2. የክት ልብስ

A. የዘወትር ልብስ C. ከሸሚዝ በላይ የሚለበስ

B. የአውዳአመት ልብስ D. መልሱ አልተሰጠም

3. ጊደር

A. ጥጃ C. ወይፈን

B. B.ላም D. መልሱ አልተሰጠም

4. አሰናከለ

A. አስተጓጎለ C. አስተካከለ

B. አደናቀፈ D.A እና B መልስ ናቸው

5. ዳራ

A. ጫፍ C. ሞቀ

B. አከማቸ D. ሳሳ

*መመሪያ ሁለት*

***ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒያቸውን ምረጥ/ጪ***

6. ቀጣፊ

A. እውነተኛ C. ዋሾ

B. ቆራጭ D. አቋራጭ

7. እድገት

A. ስልጣኔ C. ሕብረት

B. ውፍረት D. ውድቀት

8. እሮሮ

A. ደስታ C. ትካዜ

B. ርህራሄ D. ብሶት

9. አጎብዳጅ

A. አሸርጋጅ C. ልበሙሉ

B. ጎባጣ D. አናዳጅ

10. ግዙፍ

A. ትልቅ C ቀጫጫ

B. ወፍራም D. ቀጭን

መመሪያ ሶስት

ከታች በቀረበት አረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ወይም ሐረጎች አገባባዊ ፍች ምረጥ/ጪ

11.ምግብ በአግባቡ ካልተያዘ የጤነ ቀውስን ያስከትላል።

A. መጓደልን C.መታጣትን

B. ችግር D.ሁሉም ትክክል ናቸው

12. የነምትኬ ቀልድ ትዝ ሲለኝ እስቃለሁ።

A. ሲነገረኝ C. ሳስታውስ

B. ስሰማ D. ሲደጋገም

13. መልካም ነገር ለመስራት ተሽቀዳደሙ።

A. ተዘናጉ C. ተሽናነፉ

B. ችላ አሉ D.ተሯሯጡ

14. የአለሙ አባት አረጋዊ ናቸው።

A. ያረጉ C. የተከበሩ

B. ሽማግሌ D. ጎልማሳ

15. ወንድሜን ሳስቀይመው አልሻም።

A. አልመጣሁም C. አልፈልግም

B. አልሸሽም D. አልደፍርም

*መመሪያ ሰባት*

***ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ***

31. የሚጠብቅ ድምጽ ያለው ቃል የትኛው ነው?

A. ጥብስ B. ቅቅል C. ልብስ D. ወንዝ

32. በጽሑፍ ቅርፃቸው የሚመሳሰል ሆኖ ሲነበብ የትርጉም ለውጥ የሚያመጣው ቃል የትኛው ነው

A. በራ C. ለጋ

B. በላ D. ሁሉም መልስ ነው።

33. ቅጥያ የሌለው ቃል የትኛው ነው

A. ቤቱ C. ምስር

B. ለእርሱ D.ትናንሽ

34. "የወሰደው" በሚለው ቃል ውስጥ ቅጥያው ------- ነው።

A. የ----- C. የ------ው

B. ------ው D. ቅጥያ የለውም

35. "ስለደብተሬ" በሚለው ቃል ውስጥ መነሻ ቃሉ (ግንዱ) -----ነው

A. ደብተሬ C. ስለደብተሬ

B. ስለደብተር D. ደብተር

36. የአማርኛን ቋንቋ ስርዓት ተከትሎ ያልተዋቀረው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው

A. ተማሪዎቹ ወደ ቤታቸው ሄዱ።

B. ሙዚቀኛው ክራር መምታት ይችላል።

C. መምህራኖቹ ክፍል ገብተው አስተማሩ

D. ነጋዴው ከፍተኛ ትርፍ አገኘ

37. ድርብ ቃል የሆነው የትኛው ነው?

A.አስተዋለ C. የተስተካከለ

B. ሁለ-ገብ D. እግረኞች

38. አነባበቡ ተመሳሳይ ሆኖ የተለያዩ ትርጉሞችን የማይሠጠው ቃል የትኛው ነው

A. ሰፈር C. ጠላ

B. ትራስ D. ጦጣ

41. ------ ተማሪ በፈተና አንደኛ ወጣ የሚለውን ዓረፍተነገር ሊያሟላ የሚችለው ቃል የትኛው ነው?

A. ይህ ልጅ C. አበበ

B. ጎበዙ D.የክፍል ጓደኛ

52. “ሰካራሞች ሞልተው” የሚለው ሐረግ ፍቺ ------------ነው?

A. ሁሉም ሰካራሞች ናቸው

B. መጠጫቸውን ሞልተው ይጠጣሉ

C. ስካርና ሰዎች አይነጣጠሉም

D. ሰካራሞች በብዛት ይገኛሉ

56. አቀላጥፎ ሲል ምን ማለቱ ነው?

A. አቆራርጦ

B. ድካም ሳይኖር

C. በአግባቡ

D. በአጭሩ

5. 2002 ዓ.ም

**I. ከታች ለቀረቡ ቃላት ትክክለኛን ፍቺ ምረጥ/ጪ**

1. ገሰፀ

   A. ሰረፀ C. ገረሰሰ

   B. ተቆጣ D. አባረረ

2. ሰጋ

   A. በሬ C. ደገፈ

   B. ወፈረ D. ፈራ

3. ቁብ

   A. እንቁላል ያልጣለች ዶሮ C. የእንጀራ መሶብ ክዳን

   B. የመነኩሴ ባርኔጣ D. ባልንጀራ

4. ጢሻ

   A. የእርጥብ እንጨት ጢስ B. ለጥ ያለ ሜዳ

   C. ጫካ D. እህል በብዛት የሚገኝበት

5. አጨ

   A. አገባ C. በማጨድ አነሳ

   B. ቃል ገባ D. ተወ

**II. ከታች ላቀረቡት ቃላት ተቃራኒያቸውን ምረጥ/ጪ**

6. ትጉ

   A. ታታሪ C. አበያ

   B. ፈሪ D. ደፋር

7. በርካታ

A. ጥቂት C. አብዛኛው

B. አያሌ D. በአብላጫው

8. ቆላ

A. ወይናደጋ C. ደጋ

B. ሞቃታማ D. በረሃ

9. ገሃድ

A. ግልጽ C. ቅርብ

B. ድብቅ D. ሩቅ

10. ንፉግ

A. ክፉ C. መስጠት የማይወድ

B. ጨካኝ D. ቸር

**IV. ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ**

15. ቅጥያ የሌለው ቃል የትኛው ነው?

A. ቀማኝ C. ሰውነት

B. ቀናቸው D. መኪና

16. "ለውሻው" የሚለው ቃል ቅጥያዎች

A. ለ-- C. ለ----እና---ው

B. --ው D. ውሻ

17. ድርብ ቃል ያልሆነው የትኛው ነው

A. እንጀራ አባት C. መርፌ ቁልፍ

B. ዳቦ ቆሎ D. ተበላሽቶብናል

18. “የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰጠው ውሳኔ ስራ ላይ ዋለ” በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ ምህፃረ ቃል ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

A. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ---ተመድ

B. የሰጠው ውሳኔ---ሰ.ው.

C. ስራ ላይ ዋለ።----ሰ.ላ.ዋ

D. በምህፃረ ቃል ሊቀርብ የሚችል የለም

19. ሲጠብቅና ሲላላ ቃሉ የተለያዩ ፍቺዎች እንዲኖረው የሚያደርግ ድምዕ ያለው ቃል የትኛው ነው ?

A. ብር　　C. ካባ

B. ዱባ　　D. A እና C ትክክል ናቸው።

20 “ቅላጼ” በሚለው ቃል ውስጥ የሚጠበቀው ድምዕ የትኛው ነው?

A. ቅ　　C. ጼ

B. ላ　　D. ሁሉም ትክክል ናቸው።

30. “የመከላከያ ሰራዊቱ የስፖርት በአል በደማቅ ሁኔታ ተከፈተ” በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የግስ ገላጩ የትኛው ነው?

A. የመከላከያ ሰራዊቱ　　C. በደማቅ ሁኔታ

B. የስፖርት በዓል　　D. ተከፈተ

31. “የሀገር ልብሱን ለብሶ ወደ ሰርጉ ስፍራ ሄደ።” በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የስም ገላጩ የትኛው ነው?

A. የሀገር　　C. ወደ ሰርጉ ስፍራ

B. ልብሱን ለብሶ　　D. ሄደ

59. "ልምላሜ" የሚለው ቃል ፍች ምንድነው ?

A. ውብት    B. ምርት አልባ    C. ድርቅ    D. በተፈጥሮ ሀብት የበለፀገ

6. 2003 ዓ.ም

<u>መመሪያ አንድ፡</u> ከታች ለቀረቡ ቃላት በፍቺ የሚመሳሰሉትን ምረጡ።

1. ተጠናቀቀ

A. ተዘረዘረ    C. ተቆራረጠ

B. ተፈፀመ    D. ተሰነጠቀ

2. በገፍ

A. ሁሉንም    C. በብዛት

B. ጥቂቱን    D. በሳጥን

3. መቅረፍ

A. መርገፍ    C. ማምለጥ

B. መቆንጠር    D. ማስወገድ

4. የፀና

A. የጠላ    C. ድርቅ

B. የተጠናከረ    D. የሁሉም

5. አጋየ

A. ወረወረ    C. አቃጠለ

B. ዘለለ    D. በለጠ

<u>መመሪያ ሁለት፡</u> በፍች ተቃራኒ የሆነው የትኛው ነው

6. ተቃወመ

A. ነቀፈ    C. ቆመ

B. ደገፈ    D. ወቃ

7. ፈታ

A. ፈራ C. አሰረ

B. B. ተናገረ D. ወሰደ

8. በዛ

A. ተበራከተ C. አጎነበሰ

B. አነሰ D. ተኛ

9. ሰጠ

A. ነፈገ C. አስጠጋ

B. አስደሰተ D. አብላጫ

10. ተጠራቀመ

A. ተሰበሰበ C. ተዋሰደ

B. ተበተነ D. ተጠናከረ

<u>መመሪያ ሶስት</u> በትዕዛዙ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

11. የሚጠብቅ ድምፅ ያለው ቃል የትኛው ነው ?

A. መንፈስ C. ውስጥ

B. ዘመን D. ነባር

12. ደነቆረ ብሎ ድንቁርና ካለ ፈለሰፈ ብሎ ------- ይላል

A. ፍልስፍና C. ይፈላሰፋል

B. ተፈላሰፈ D. ተፈላስፏል

13. በቃሉ መነሻ ላይ "የሚ--" የማይጨመርበት ቃል የትኛው ነው?

A. መጣ C. ቆሻሻ

B. ፈላ D. በላ

14. ቅጥያ የሌለው ቃል የትኛው ነው?

A. ቅርስ C. ዘማቾች

B. ቀጥተኛ D. ሲመጣ

15. ድርብ ቃል ያልሆነው የትኛው ነው?

A. አመለ-ወርቅ C. ከነመፍትሔው

B. መልክዐ -ምድር D. መሠረተ-ትምህርት

16. <u>በሀገራችን</u>፣ <u>በአገራችን</u> እና <u>ባገራችን</u> የተሰኙት ቃላት

A. የቅርፅ እንጂ የትርጉም ለውጥ የላቸውም።

B. የቅርፅም የትርጉምም ለውጥ አላቸው።

C. የትርጉም እንጂ የቅርፅ ለውጥ የላቸውም።

D. የቅርፅም የትርጉምም ለውጥ የላቸውም።

17. "እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር" የተሰኘውን ሐረግ እ.ኤ.አ ብሎ መፃፍ ለምን አስፈለገ?

A. ጊዜና ቦታ ለመቆጠብ

B. ዘርዝሮ መፃፍ አስፈላጊ ባለመሆኑ።

C. በተሻለ ሁኔታ ግልጽ የሚሆነው አጥሮ ሲፃፍ በመሆኑ።

D. ምክንያቱ አይታወቅም

20. የተለየ የቃል እርባታ ስርዓት የተከተለው ቃል የትኛው ነው ?

A. ቀላዋጭ C. ይመጣል

B. በጥባጭ D. ረባሽ

21 በአወቃቀሩ የተለየው የትኛው ነው?

A. ደብዳቤ ፃፈ--- ደብዳቤ አፃፃፍ

B. እርሻ አረሰ ---- እርሻ አስተራረስ ።

C. በር ዘጋ ----- በር አዘጋግ ።

D. ልብስ ለበሰ---- ልብስ አስለበሰ

22. አረፍተነገር ያልሆነው የትኛው ነው?

A. ጋቢውን ለበሰ　　C. ልብሱን አጥቦ

B. ቁልቁል ወረዳ　　D. ፀጉሩን አበጠረ

23 "አዲሱን ሹራብ ለብሶ ት/ቤት እየሮጠ ሄደ::" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የስም ገላጭ የሆነው ቃል የትኛው ነው ?

A. አዲሱን　　B. ለብሶ

C. እየሮጠ　　D. ወደ ት/ቤት

25. "እነዚህን ሁለት <u>ስልቶች</u> በተናጠል እንመልከት" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበትን ቃል በፍች የሚተካው ቃል------ ነው?

A. ሥርዓቶች　　C. አረፍተ ነገሮች

B. ዘዴዎች　　D. አስተያየቶች

27. ሊካሄድ ታስቦ የነበረው ስብሰባ ተደናቀፈ:: የተሰመረበት ቃል በ----------------ሊተካ ይችላል

A. ተሳካ　　C. ተካሄደ

B. ተሰናከለ　　D. ተቋረጠ

32. የአረፍተ ነገር አወቃቀር ሥርዓትን የተከተለው የትኛው ነው?

A. የተተከሉት አበቦች ስላደገ አካባቢው አሸበረቀ::

B. ዝናብ ስለዘነበ አካባቢው ጨቀየ::

C. ስፖርት ስለምትሠራ ሰውነቱ ጠንክሯል::

D. ፍላጎቷ ስለተሳካለት በጣም አዝናለች::

42. "እንደ ባለጋራ ቆጥሮት" የሚለው ሐረግ ፍች ------ነው::

A. እንደታታሪ ሰው ቆጥሮት ::

B. እንደ ዘመድ ቆጥሮት ::

C. እንደ ጠላት ቆጥሮት

D. እንደ ጎረቤት ቆጥሮት

43. “ትክ ብሎ” የሚለው ሐረግ ፍች-----ነው።

A. ፍንክንክ ብሎ

B. ተደስቶ

C. አልቅሶ

D. በሃሳብ ተይዞ

44. “አይን ያስፈራው ይመስል” የሚለው ሐረግ ፍች------ ነው

A. አይን አውጣ ሆኖ

B. የሚያፍር ሆኖ

C. ተንቀዠቀዠ

D. ዘገምተኛ ሆኖ

59. “ያሟጥጣል” የሚለው ቃል ፍች ምንድን ነው?

A.ይጨርሳል

B. ይጨምራል

C. ያበዛል

D. ይቀንሳል

## አባሪ ሁለት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

**ቃለ መጠይቅ**

**ለፈተና ዝግጅት ክፍል ተወካይ የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ**

መግቢያ፡- የዚህ ቃለ መጠይቅ ዋና ዓላማ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅተው በቀርቡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን የይዘት ተገቢነት ለመመርመር ለሚደረገው ጥናት አጋዥ የሚሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ጥናቱ ውጤታማ የሚሆነው የእርሶ ቀና ትብብር ሲታከልበት በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቅንነት ተመልክተው ትክክኛ ምላሽ እንዲሰጡኝ ስጠይቅ የሚገኘው መረጃ ለታቀደው ጥናትና ምርምር ጉዳይ ብቻ የሚውል መሆኑን በትህትና አረጋግጣለሁ፡፡

ጥያቄዎቹን ለመመለስ በመፍቀድዎ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

1. በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች ተዘጋጅተው የሚቀርቡት የአማርኛ ፈተናዎች ይዘቶች ከየት ይመረጣሉ? ለምን?
2. የፈተና አውጪዎች የትምህርቱን ይዘቶች እንደየትኩረት ደረጃቸው እንዲወከሉ ለማድረግ የፈተና ንድፍ ያዘጋጃሉ? እንዴት?
3. ፈተና አውጪዎች ፈተና በሚያዘጋጁበት ጊዜ የፈተና አዘገጃጀት መርሆችን መሠረት ያደርጋሉ ብለው ያምናሉ? እንዴት?
4. ለፈተና አዘጋጆች ፈተና አወጣጥን በተመለከተ የሚሠጣቸው ስልጠና አለ? ለምን?
5. ተጨማሪ አስተያየት ካልዎት?

በድጋሚ አመሠግናለሁ

አበበች ገብሩ

# አባሪ ሦስት

## የጥያቄ መገምገሚያ መስፈርቶች

(Callahan እና Clark፣1988፤ Gronland፣ 1981) እንደገለጹት

### 1. ባለ ብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች (multiple choice Items)

1.1. ጥያቄዎች አጭርና ግልፅ ናቸው?

1.2. አንድን ሐሳብ በሁሉም ጥያቄዎች ከመደጋገም ሀሳቡ በጥያቄው ግንድ ላይ እንዲሰፍር ተደርጓል?

1.3. ምርጫዎች በፊደል ተራ ወይም በርዝመት ስልታዊ በሆነ መንገድ በቅደም ተከተል ተሰድረዋል?

1.4. እያንዳንዱ ጥያቄ አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ ይዟል?

1.5. መልስ የያዙ ፊደሎች ተዘበራርቀው ተቀምጠዋል?

1.6. መልስ የያዙ ፊደሎች በቁጥር ተመጣጣኝ ናቸው?

1.7. ሁሉም መልስ ነው የሚሉ ምርጫዎች የሉም?

1.8. መልስ የለም የሚሉ አማራጮች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ብቻ አልፎ አልፎ ገብተዋል?

1.9. አሉታዊ ቃላትና ሐረጋት የሉም ካሉስ ከስራቸው ተሰምሮባቸዋል ወይም ጎላ ብለው ተፅፈዋል?

### 2. አጠቃላይ መርሆች

2.1. ተማሪች ያላቸውን ዕውቀት በከፍተኛ ደረጃ አውጥተው ማሳየት እንዲችሉ በፈተናዎች የተካተቱ ጥያቄዎች በርከት ያሉ ናቸው?

2.2. ፈተናው በቀረበው ትምህርት ዓላማና ይዘት ላይ ተመስርቷል?

2.3. ሁሉም (አብዛኞቹ) የጥያቄ አቀራረብ (አጠያየቅ) ስልቶች ተካተዋል?

2.4. እያንዳንዱ ጥያቄ እራሱን ችሎ ተቀርጿል?

2.5. መመሪያዎች ወይም ትዕዛዞች በግልፅና በማያደናግር ቋንቋ ቀርበዋል?

2.6. ጥያቄዎች ከቀላል ወደ ከባድ ተደራጅተዋል?

2.7. ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ ዋጋ ተሰጥቷል?

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የራሴ መሆኑን እና በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ከበደ ገብሩ ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አዲስ አበባ

ግንቦት 2004 ዓ.ም

# ከ1998-2003 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተዘጋጅተው የቀረቡ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተናዎች ውስጥ የሰዋስው ጥያቄዎች ግምገማ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


ለተግባራዊ ሥነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር

ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

አበበች ገብሩ



ግንቦት 2004 ዓ.ም

ይገባል። እነዚህን ፈተናዎች ከዚህ መስፈርት አኳያ ስንገመግማቸው የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ ከቀረቡት 154 ጥያቄዎች በ2000 ዓ.ም ሁለት ባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ይህንን አሟልተው አልተገኙም። እነሱም፡-

13. የቡድናችን አንጋፋ ተጫዋች ተብሎ የሚታወቀው እርሱ ነው።

A. ገዘኛ ተጫዋች

B. አጥቂ ተጫዋች

C. አስጠቂ ተጫዋች

D. ያለእድሜው ተጫዋች

56."ተፈናጥሮ ወጣ" የሚለው ዐ.ነገር ፍቺ ምንድን ነው?

A. በፍጥነት ወጣ

B. ዘሎ ወጣ

C. ቀልጠፍ ብሎ ወጣ

D. ሁሉም

እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች በጥያቄ ግንዱ ላይ ያለውን በቅደም ተከተል "ተጫዋች" እና "ወጣ" በሁሉም ምርጫዎች መደጋገም ይታይባቸዋል። ይህ ደግሞ የተማሪዎቹን የፈተና መስሪያ ጊዜ ከመሻማቱም ባሻገር አላስፈላጊ ድግግሞሽን ይፈጥራል። በመሆኑም ከ154 የሰዋስው ጥያቄዎች 2 ጥያቄዎች ይህንን መስፈርት አሟልተው አልተገኙም።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፍንጭ ላለመስጠትና ተማሪዎች አማራጮች የያዙትን ሀሳብ በማወዳደር ተረድተው በቀላሉ ተስማሚ የሚሆነውን መምረጥ እንዲችሉ አማራጮችን በፊደል ተራ ወይም በርዝመት ወዘተ... በቅደም ተከተል ስልታዊ በሆነ መንገድ ማደራጀት ጠቃሚ ነው። ከዚህ መስፈርት አኳያ በ6ቱ ዓመታት ተዘጋጅተው በቀረቡት ማጠቃለያ ፈተናዎች የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች በተወሰኑ ዓመተ ምህረት ጥያቄዎች ላይ ይህ ችግር ይስተዋላል። በመሆኑም በተወሰኑ ፈተናዎች ውስጥ አማራጮች አንድ ጊዜ ወደ ጎን ሌላ ጊዜ ቁልቁል ተሰድረዋል። ይህም ተማሪዎቹ በተሰጠው ጊዜ በቀላሉ አማራጮችን ተረድተው ትክክለኛውን ምላሽ ለመምረጥ እገዛ አያደርግላቸውም።

ለምሳሌ በ2002 ዓ.ም በቀረበው የማጠቃለያ ፈተና ውስጥ በቅደም ተከተል 18፣ 19ኛና 20ኛው ጥያቄዎች ላይ የሚገኙትን እንመልከት

18.“የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰጠው ውሳኔ ስራ ላይ ዋለ ” በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ ምህፃረ ቃል ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው

A. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ----ተመድ

B. የተሰጠው ውሳኔ-------ሰ.ው

C. ስራ ላይ ዋለ------- ስ.ላ.ዋ

D. በምህፃረ ቃልነት ሊቀርብ የሚችል የለም

19.ሲጠብቅና ሲላላ ቃሉ የተለያዩ ፍቺዎች እንዲኖረው የሚያደርግ ድምፅ ያለው የትኛው ነው?

A. ብር B. ዱባ C. ካባ D. A እና C ትክክል ናቸው።

20.“ቅላፄ” በሚለው ቃል ውስጥ የሚጠብቀው ድምጽ የትኛው ነው?

A. ቅ C. ፄ

B. ላ D. ሁሉም ትክክል ናቸው።

እነዚህ በተከታታይ የቀረቡት ጥያቄዎች አማራጮች አቀራረብ ስንመለከት ስልታዊ በሆነ መልኩ የቀረቡ አይደሉም፤ የመጀመሪያው ጥያቄ አማራጮች ሁሉም ቁልቁል ወደታች የተደረደሩ ሲሆኑ የ19ኛው ጥያቄ አማራጮች ደግሞ ወደ ጎን የተደረደሩ ናቸው። እንዲሁም የ20ኛው ጥያቄ ደግሞ በሁለት በመክፈል ወደ ጎን እና ወደታች ተደርድረው እናገኛለን። እንዲህ ያሉ ችግሮች በፈተናዎቹ አልፎ አልፎ የሚታዩ ቢሆኑም በዚህ ረገድ ጥንቃቄ ተደርጎበት መሰራት እንዳለበት የሚጠቁም ነው።

ከዚሁ ፍንጭ ሰጪ ነገሮችን ከማስወገድ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ትክክለኛ መልሶችን የያዙ አማራጮችና አሳሳች አማራጮችን በርዝመትም ሆነ በቅርጽ ተመጣጣኝ ማድረግ የሚገባ መሆኑን ነው። እንደ Madsen (1983) ገለፃ በምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች የአሳሳች መልስ ተአማኒነት መጠበቅ ዋናው ስራ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ፈተና አውጪው አሳሳቾችን በቅርፅ ተመሳሳይ፣ በርዝማኔና በክብደት ደረጃ ተመጣጣኝ እንዲሆኑ መጣር ይጠበቅበታል። ለምሳሌ ዋናው መልስ በቅርጽ ግስ ከሆነ አሳሳቾቹን በሙሉ ግስ ማድረግ ይጠበቃል። የአንድን ፈተና አሳሳቾች ተአማኒነት ለመመርመር የሚደረገው ጥናት ሰፊ ጊዜን የሚጠይቅ

ነው። ይህም የበርካታ ተማሪዎችን ውጤት በመልስ ትንተና በመስራት የትኞቹ አሳሳቾች ይበልጥ መልስ የመምሰል ባህሪይ እንዳላቸው ነቅሶ ማውጣትን ይጠይቃል።

ይህ ደግሞ እራሱን የቻለ የጥናት ርዕስ ሊሆን ይችላል። በመሆኑም አጥኚዋ ይዛው ከተነሳቸው ጥያቄዎችና ካለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት አንፃር ርዕሰ ጉዳዩን በጥልቀት ለመመርመር አልተቻለም ።

ያም ሆኖ ግን ወደፊት ሌሎች ተመራማሪዎች በርዕሰ ጉዳዩ ጥልቅ ጥናት እስኪያደርጉበት ድረስ በውጫዊ መልኩ የአሳሳቾችን ተአማኒ መሆን ወይም አለመሆን ለመመርመር ተሞክሯል። የአሳሳቾች ውጫዊ መልክ ሲባል አሳሳቾቹ ከዋናው መልስ ጋር በቅርፅ ተመሳሳይ፣ በርዝማኔና በክብደት ደረጃ ተመጣጣኝ መሆናቸውን መመርመር ማለታችን ነው።

በማጠቃለያ ፈተናዎቹ የቀረቡ የሰዋስው ጥያቄዎችን በመመርመር የተገኘው ውጤት እንደሚያመላክተው አሳሳቾች ከዋናው መልስ ጋር በቅርጽ ተመሳሳይ፣ በርዝማኔና በክብደት ደረጃ ተመጣጣኝ ሆነው ተገኝተዋል። በመሆኑም አሳሳቾቹ ተአማኒነት ያላቸው ይመስላሉ።

ለአብነት ያክል የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንመልከት

**ምሳሌ** 1፡- በ1999 ዓ.ም ጥያቄ ቁጥር 46

- አላገኘሁትም በተሰኘው ሀሳብ (አባባል) ተሳቢ ሊሆን የሚችለው -----------ነው።

  A. እሱን B. እኔን C. አንተን D. እሷን

**ምሳሌ** 2፡- በ2001 ዓ.ም ጥያቄ ቁጥር 36

- የአማርኛን ቋንቋ ስርዓት ተከትሎ ያልተዋቀረው ዐ.ነገር የትኛው ነው?
  A. ተማሪዎቹ ወደ ቤታቸው ሄዱ።
  B. ሙዚቀኛው ክራር መምታት ይችላል።
  C. መምህራኖቹ ክፍል ገብተው አስተማሩ።
  D. ነጋዴው ከፍተኛ ትርፍ አገኘ።

ምሳሌ3፡- በ2003 ዓ.ም ጥያቄ ቁጥር 16

- በሀገራችን፣ በአገራችን እና ባገራችን የተሰኙት ቃላት፡-
  A. የቅርፅ እንጂ የትርጉም ለውጥ የላቸውም፡፡
  B. የቅርፅም የትርጉምም ለውጥ አላቸው፡፡
  C. የትርጉም እንጂ የቅርፅ ለውጥ የላቸውም፡፡
  D. የቅርፅም የትርጉምም ለውጥ የላቸውም፡፡

ምሳሌ አንድ ላይ የቀረበውን ጥያቄ ብንመለከት ትክክለኛው መልስ "A" ነው፡፡ የቀረቡትን አሳሳቾች ስንመለከት ደግሞ ሁሉም ከትክክለኛው መልስ ጋር በቅርጽ ይመሳሰላሉ፡፡ ሁሉም ስሞች ናቸው፡፡ በርዝማኔም ሁሉም አማራጮች ተመጣጣኝ ናቸው፡፡ በክብደት ደረጃም ሲታይ ትክክለኛው መልስ ከበድ ብሎ አይታይም፡፡ ስለሆነም አሳሳቾቹ ተአማኒ ናቸው ማለት እንችላለን፡፡ በተጨማሪም በምሳሌ ሁለትና ሶስት ላይ የሚታዩት አሳሳቾች በርዝመትም ሆነ በቅርጽ ከዋናው መልስ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ አሳሳቾች የቀረቡበት መንገድ ጥሩ በመሆኑ ማጠቃለያ ፈተናዎቹ በዚህ ረገድ ጠንካራ ጎናቸው የጎላ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- ጥያቄዎች አስተማማኝነት እንዲኖራቸው አንድ ትክክለኛ መልስ ብቻ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ በክልሉ ተዘጋጅቶ የቀረበውን የመልስ ቁልፍ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በዚህ መሠረት ከ154 ባለብዙ ምርጫ የሰዋስው ጥያቄዎች ሶስቱ (1.9%) የሚሆኑ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት የሚያስቸግሩ በመሆናቸው ለሁሉም ተማሪዎች በችሮታ ተሰጥተዋል፡፡ ለምሳሌ በ1998 ዓ.ም በጥያቄ ቁጥር 14

  14. ብዙ መክሬው <u>ስለታከተኝ</u> ተውኩት፡፡
     A.ስላልሰማኝ B. ስላቃተኝ C. ስለደከመኝ D. ስለሰለቸኝ

  የሚለው አንድ ትክክለኛ ምላሽ ለመምረጥ የሚያስችል አይደለም፡፡

- ባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ መልስ የያዙ ፊደሎችን በማዘበራረቅና መልስ የያዙ ፊደሎችን ብዛት ተመጣጣኝ በማድረግ ፍንጭ እንዳይሰጡ ማድረግ ይገባል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ሁሉም የማጠቃለያ ፈተናዎች የቀረቡ ጥያቄዎች ይህንን የሚያሟሉ ሆነው መገኘታቸው ለፈተናው በቂ ዝግጅት ያላደረጉ ተማሪዎች የመልሶቹን ቅደም ተከተል በማየትም ሆነ የበለጠ በተደጋጋሚ የመጣውን መልስ በማየት የማያውቁትን

ጥያቄ በግምት እንዲመልሱ እድል የማይሰጣቸው መሆኑን ከመልስ ቁልፍ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ በአብዛኛዎቹ የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙት የሰዋስው ጥያቄዎች ተከታትለው የሚገኙ በመሆናቸው ይህንን ጉዳይ በቀላሉ ለማመሳከር ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ለክልሉ ለፈተና አዘጋጆች በተዘጋጀው መመሪያ ላይ "መልስ የያዙ ፊደሎች በተከታታይ አንድ አይነት A,A,A,A, ወይም B,B,B,B መሆን የለበትም" የሚል መመሪያ መኖሩ ይህ ችግር እንዳይፈጠር አስተዋፅኦ ያበረከተ ይመስላል፡፡

- በምዕራፍ ሁለት በ2.3.4.3 እንደተጠቀሰው የባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ "ሁሉም መልስ ነው" የሚሉ ምርጫዎችን አለመጠቀም ይመከራል፡፡ ይህ አማራጭ ያለበት ጥያቄ በእጅጉ በቀለለ መልኩ መልሱ ሊገኝ ይችላል፡፡ ተማሪው አንዱ አማራጭ ትክክል እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ካወቀ "ሁሉም" የሚለውን መልስ ሊመርጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ጥያቄው ባለ አራት አማራጭ ቢሆን ተማሪው ሁለቱን አማራጮች ብቻ ማወቁ "ሁሉም" የሚለውን አማራጭ ለመምረጥ በቂው ሲሆን ሶስተኛውን አማራጭ ማወቅ ላይጠየቅበት ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር በስድስቱ ተከታታይ ዓ.ም በቀረቡ የማጠቃለያ ፈተናዎች ሲገመገሙ "ሁሉም" መልስ ነው የሚሉ አማራጮችን የያዙ የሰዋስው ጥያቄዎች ከ154 ጥያቄዎች 6 ጥያቄዎች ናቸው ይህም በመቶኛ ሲሰላ 4% የሚሆኑት ናቸው፡፡

እነሱም፡- በ2000 ዓ.ም በቀረበው የማጠቃለያ ፈተና ውስጥ ጥያቄ ቁጥር 17፣ 56 እና 59፣ በ2001 ዓ.ም በቀረበው የማጠቃለያ ፈተና ውስጥ ጥያቄ ቁጥር 11 እና 32 እንዲሁም በ2002 ዓ.ም በቀረበው የማጠቃለያ ፈተና ጥያቄ ቁጥር 20 "ሁሉም መልስ ነው" የሚል አማራጮችን የያዙ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ጥቂት ቢሆኑም ፈተናዎቹ መመዘን ያለባቸውን በትክክል ይመዝኑ ዘንድ ተማሪዎች በግምት መልስ እንዲሰጡ ከሚያበረታቷቸው አማራጮች ነፃ መሆን ይገባቸዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ "መልስ የለም" የሚሉ አማራጮችን ሳለመጠቀም መሞከር ወይም እጅግ አስፈላጊ ከሆነ አልፎ አልፎ ብቻ መጠቀም እንደሚገባ በዚያው በምዕራፍ ሁለት በ2.3.4.3 ላይ ተገልጿል፡፡ ተማሪዎች መልሱን የማያውቁት ወይም የተወሰኑትን አማራጮች አውቀው ሌሎቹን ስላወቁ ወደዚሁ ምርጫ ያዘነብላሉ፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ፈተናዎች ውስጥ "መልስ የለም" የሚሉ አማራጮች በብዛት አይገኙም፡፡ ከዚህ መስፈርት አኳያ ፈተናዎቹ ክፍተት አይታይባቸውም፡፡

- ብዙውን ጊዜ በባለብዙ ምርጫ ሰጪ ጥያቄዎች ውስጥ አሉታዊ ቃላትና ሐረጋት ሲገቡ ተማሪዎች ትኩረት ስለማያደርጓቸው ጥያቄውን ቢያውቁት እንኳ በእነዚህ አሉታዊ ቃላትና ሐረጋት ምክንያት ትክክለኛውን መልስ ሳይመልሱ ይቀራሉ፡፡ ነገር ግን ፈተናዎች ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል ተረድተዋል የሚለውን ለማወቅ ዓላማ አድርገው ከመዘጋጀታቸው አንጻር ተማሪዎቹ በእነዚህ አሉታዊ ቃላትና ሐረጋት አማካይነት ሊመዘኑ አይገባም፡፡ ስለሆነም በተቻለ መጠን ፈተና አዘጋጆች እነዚህን ነገሮች አለመጠቀም፤ መጠቀም ካለብን እንኳ ለተማሪዎች በግልጽ እንዲታዩ አድርጎ ጎላ ብለው እንዲፃፉ ማድረግ አልያም በስራቸው ማስመር እንደሚገባ Alderson and et al. (2001) ይገልፃሉ፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ ከሆኑት በአራት ዓመት የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ ይህ ችግር ይታያል፡፡ እነዚህ ችግሮች የሚታዩባቸው፤ በ1998 ጥያቄ ቁጥር 40፣ በ2001 ዓ.ም ጥያቄ ቁጥር 33፣ 36 እና 38፣ በ2002 ዓ.ም ጥያቄ ቁጥር 15 እና 17 እንዲሁም በ2003 ዓ.ም ጥያቄ ቁጥር 13፣14፣15 እና 22 በአጠቃላይ 10 ጥያቄዎች አሉታዊ ቃላትና ሐረጋት በውስጣቸው ቢገኝባቸውም አንዳቸውም በተለየ መልኩ ለተማሪዎች በግልጽ እንዲታዩ ተደርገው ጎላ ብለው አልተፃፉም ወይም ከስራቸው አልተሰመረባቸውም፡፡ በማጠቃለያ ፈተና ውስጥ እንዲህ ያሉ አሉታዊ ቃላትና ሐረጋትን በአግባቡ አለመጠቀም ከላይ እንደተገለፀው ተማሪዎችን ሊያደናግርና ጥያቄዎቹን እያወቁ በእነዚህ አሉታዊ ቃላትና ሐረጋት ምክንያት ብቻ ችሎታቸውን በትክክል እንዲያሳዩ ላያደርጋቸው ይችላል፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ መስፈርት አኳያ የማጠቃለያ ፈተናዎቹ ተመርምረው በተገኘው ውጤት ከአጠቃላይ 154 ጥያቄዎች 10 ማለትም 6.5 % አሉታዊ ቃላትና ሐረጋትን በአግባቡ አልተጠቀሙም፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች እንመልከት፤

**ምሳሌ** 1 በ2001 ዓ.ም ጥያቄ ቁጥር 33

33. ቅጥያ የሌለው ቃል የትኛው ነው

A. ቤቱ C. ምስር

B. ለእርሱ D. ትናንሽ

**ምሳሌ** 2. በ2002 ዓ.ም ጥያቄ ቁጥር 17

17. ድርብ ቃል ያልሆነው የትኛው ነው?

A. እንጀራ አባት C. መርፌ ቁልፍ

B. ዳቦ ቆሎ D. ተበላሽቶብናል

በምሳሌዎቹ የቀረቡትን ጥያቄዎች ስንመለከት በቅደም ተከተል "የሌለው" እና "ያልሆነው" የሚሉ አሉታዊ ቃላት ይገኙባቸዋል፤ ነገር ግን በጉልህ ለተማሪዎች እንዲታዩ ተደርገው አልተፃፉም ወይም ከስራቸው አልተሰራባቸውም፡፡

- በግምት የመመለስ እድልን ለማጥበብ አማራጮችን ሶስት ከተቻለም አራት ማድረግ ይመከራል፡፡ ይህን በተመለከተ በማጠቃለያ ፈተናዎቹ በተደረገው ምርመራ መሰረት ሁሉም የማጠቃለያ ፈተናዎች አራት አራት አማራጮችን የያዙ ናቸው፡፡ ይህም በተሻለ መልኩ ግመታን ስለሚቀንስ ይበል የሚያስብል ነው፡፡

በአጠቃላይ በስድስት ዓመት የማጠቃለያ ፈተናዎች በቀረቡ 154 የሰዋስው ጥያቄዎች የተለያዩ ጠንካራ ጎኖችን ለማየት ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሠረት በሁሉም የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ጥያቄዎች የግልፅነት ችግር አለመኖሩ፣ ትክክለኛና አሳሳች አማራጮች በቅርፅም በርዝመትም ተመጣጣኝ መሆን፣ መልስ የያዙ ፊደሎቹን በማመጣጠንና አዘበራርቆ በማስቀመጥ የሁሉም ፈተናዎች ጠንካራ ጎኖች ናቸው፡፡ ከዚህ ሌላ አንድን ሐሳብ በምርጫዎች ላይ መደጋገም ሁለት ጥያቄዎች፣ "ሁሉም መልስ ነው" የሚሉ ምርጫዎችን በመያዝ 6 ጥያቄዎች፣ አማራጮችን ስልታዊ በሆነ መንገድ ያለማደራጀት ለተማሪዎች አመቺ ሁኔታን ባለመፍጠር በአንዳንድ ጥያቄዎች እንዲሁም አሉታዊ ቃላትና ሐረጋትን በአግባቡ ባለመጠቀም 10 ጥያቄዎች ላይ ድክመት ይታያል፡፡ እነዚህን ችግሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ፈተናዎች የታለመላቸውን ዓላማ በትክክል ያሳኩ ዘንድ የማጠቃለያ ፈተናዎች ዝግጅት ወቅት የፈተና አዘገጃጀት መርሆችን በጥንቃቄ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ የቋንቋ ፈተና ምሁራን የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ የማጠቃለያ ፈተናዎች በተወሰነ መልኩ ድክመት ሲታይባቸው በጠንካራ ጎን ሊነሱ የሚችሉ ነገሮችም እንዳሉት ከግምገማው የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡

### 4.2.2 አጠቃላይ መርሆች

በዚህ ክፍል ጥያቄዎቹን በተመለከተ አጠቃላይ የአዘገጃጀት መርሆችን በማንሳት ጥያቄዎቹን ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው ተማሪዎች ያላቸውን ዕውቀት አውጥተው ማሳየት እንዲችሉ በርከት ያሉ ጥያቄዎችን ማቅረብ ይገባል፡፡ ይህም ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ወካይ ናሙና እንዲያገኙ ይረዳል፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ ለሰዋስው ጥያቄዎች የተሰጠው የጥያቄ መጠን ከሌሎች የቋንቋ ይዘቶች

ሲነፃፀር በርከት ያለውን የጥያቄ መጠን የያዘው የሰዋስው ይዘት ነው፡፡ ይኸውም የፈተናዎቹ አጠቃላይ ጥያቄ 60 ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ1998 ዓ.ም 32፣ በ1999 ዓ.ም 21፣ በ2000 ዓ.ም 27፣ በ2001 ዓ.ም 26፣ በ2002 ዓ.ም 19 እንዲሁም በ2003 ዓ.ም 29 ያህሉ የሰዋስው ጥያቄዎች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ይህም በአማካይ 25 ማለት ነው፡፡ በማጠቃለያ ፈተናዎቹ ውስጥ የሚታየው ችግር ብዙ ጥያቄዎችን የማቅረብ ችግር ሳይሆን የሰዋስው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ እንደየትኩረት ደረጃቸው ተመጣጣኝ የሆነ ወካይ ናሙና እንዲያገኙ የማድረግ ችግር እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ተማሪዎች ለረጅም ጊዜ ሲማሩ የቆዩት ይዘቶች ላይ ያላቸውን ችሎታ በበቂ ሁኔታ ሊያሳዩ እንዲችሉ ሊረዳቸው አይችልም፤ በመሆኑም በእነዚህ የማጠቃለያ ፈተናዎች በርካታ ጥያቄዎችን የማቅረብ ችግር ሳይሆን ይዘቶች በፈተናው ውስጥ በበቂ ሁኔታ እንዲሸፈኑ የማድረግ ችግር እንደሆነ በተደረገው ምርመራ ተረጋግጧል፡፡

ለተማሪዎች የሚቀርብ ፈተና ተማሪዎች ይማሩታል ተብሎ በተነደፈው ይዘትና ዓላማ ላይ መመስረት እንዳለበት በክለሳ ድርሳኑ ተጠቅሷል፡፡ በትምህርቱ ዓላማና ይዘት ላይ ያልተመሠረተ ፈተና የይዘት ተገቢነት አይኖረውም፤ የፈተናዎቹን የይዘት ተገቢነት በመመርመር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው አንዳንድ የሰውስው ይዘቶች በፈተናው ውስጥ ውክልና ባያገኙም በማጠቃለያ ፈተናዎቹ ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ጥያቄዎች ከአንድ ጥያቄ በስተቀር ሁሉም ጥያቄዎች ለደረጃው በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ላይ መመስረታቸው ተረጋግጧል፡፡ በሌላ አገላለጽ በእነዚህ የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡት ሁሉም የሰዋስው ጥያቄዎች ለደረጃው ከተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ጋር ግንኙነት አላቸው፡፡ ይህም በበጎ ጎኑ የሚነሣ ነው፡፡ ምክንያቱም የማጠቃለያ ፈተናዎች የሚዘጋጁት ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱት ለመገምገም እስከሆነ ድረስ እነዚህ ፈተናዎች በመርሃ ትምህርቱ ላይ መሠረት ማድረጋቸው በጠንካራ ጎን የሚነሳ ነው፡፡

በሌላ በኩል መመሪያዎችና ትዕዛዞችን ስንመለከት በክለሣ ድርሳኑ እንደተገለፀው መመሪያዎች (ትዕዛዞች) የሚቀርቡበት ቋንቋ ጥያቄዎች ከሚቀርቡበት ይልቅ እጅግ የቀለለ እና ግልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡ ተማሪዎች በመመሪያ ግልፅነት ጉድለት ምክንያት ጥያቄዎችን ማጣት የለባቸውም፤ በዚህ ረገድ በማጠቃለያ ፈተናዎቹ የቀረቡትን መመሪያዎችና ትዕዛዞች ለማየት እንደተሞከረው በስድስቱም ዓ.ም የቀረቡት የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ የመመሪያ ግልፅነት

ችግር የሚታይባቸው አልተገኙም፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች መመሪያዎቹን በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉ ይመስላል፡፡

ፈተናዎች የተማሪዎችን የተለያየ ችሎታ መለካት እንዲችሉ ቢቻል ሁሉንም የጥያቄ አቀራረብ ስልቶች መጠቀም ይመከራል፡፡ ይሁን እንጂ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የማጠቃለያ ፈተናዎች ይህንን አሟልተው አልተገኙም፡፡ በሁሉም የማጠቃለያ ፈተናዎች የቀረቡት የጥያቄ አቀራረብ ስልቶች በባለብዙ ምርጫ ሰጪ (multiple choice item) ጥያቄ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ በትምህርት ቢሮው የፈተና ክፍል ተወካይ ለሆኑት ለምን ሁሉንም የጥያቄ አቀራረብ ስልቶች በማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ አልተጠቀማችሁም የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሲመልሱ፣

> *ችግሩ የተፈጠረው ይህንን የማጠቃለያ ፈተና የሚወስዱ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት ነው፡፡ ሁሉንም የጥያቄ ማቅረቢያ ስልቶች እንጠቀም ብንል በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ፈተናዎቹ የሚታረሙት በሰው በመሆኑ ከፍተኛ ወጪ ከመጠየቁም ባሻገር በተማሪዎች ውጤት ላይ ልዩነት ሊፈጥር ይችላል የሚል ስጋት አለ፡፡ ለምሳሌ አታች ጥያቄዎችን በነዚህ የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ መጠቀም እርግጠና ሆኜ የምናገረው በተማሪዎች ውጤት ላይ ልዩነት ይፈጥራል፣ ከዚህም በተጨማሪ ይህንን ልምድ ከፈተናዎች ድርጅት እንዳየነው "የማትሪክ" ፈተናዎች ሁሉም በባለብዙ ምርጫ ሰጪ የጥያቄ ስልት ነው የሚቀርቡት በክልላችንም ይኸው ነው ተግባራዊ የሆነው፡፡*

በማለት የመለሱ ሲሆን ከቃለ መጠይቁ ምላሽ መረዳት የተቻለው የማጠቃለያ ፈተናዎቹ የሚዘጋጁት ለክልሉ በጠቅላላ በመሆኑ ፈተናውን የሚወስዱ ተማሪዎች በቁጥር በርካታ መሆን ሁሉንም የጥያቄ ማቅረቢያ ስልቶች መጠቀም አስቸጋሪ እንደሆነ ነው፡፡

- ተማሪዎች ከተሰጣቸው ጊዜ አንጻር ጥያቄዎቹ እንደያዙት ዋጋ መጠን የበለጠ ትኩረት መስጠት ለሚገባቸው ጊዜ ሰጥተው መስራት እንዲችሉ ለጥያቄዎች የተሰጠው ዋጋ መጠቀስ ይኖርበታል፡፡ ይህንን በተመለከተ የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት የማጠቃለያ ፈተናዎች ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች ያላቸው ዋጋ እኩል ነው፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የማጠቃለያ ፈተናዎች እያንዳንዱ 60 ጥያቄዎችን የያዙ ሲሆን ሁሉም ጥያቄዎች ዋጋቸው ተመጣጣኝ ነው፡፡ በመሆኑም በእነዚህ